# የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ

# Ethiopian Cities Association

# በከተሞች የህዝብ ተሳትፎ እና የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ የተሞክሮ ሰነድ

ህዳር 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**ማውጫ**

ክፍል አንድ ........ 4
ምዕራፍ አንድ፡- የህዝብ ተሳትፎ ጽንሰሃሳብ ........ 4
1. መግቢያ ........ 4
2. መነሻ ሁኔታ፡ የህዝብ ተሳትፎና የከተሞች መልካም አስተዳደር ........ 4
3. የህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ምንነት ........ 5
4. በልማት ውስጥ የህብረተሰብ ተሳትፎ ምክኒያታዊ አስፈላጊነት ........ 7
5. የህዝብ ተሳትፎ አይነቶችና ደረጃዎች ........ 12
6. የከተማ ህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄን ለመምራት የምንከተላቸው ስልቶች ........ 14
7. የህዝብ ተሳትፎ መተግበሪያ መሳሪያዎች (Tool box) ........ 15
8. የከተማ ህብረተሰብ ተሳትፎ ስራ ተግዳሮቶች (Challenges) ........ 16
ምዕራፍ ሁለት፡- የሃላባ ቁሊቶ ከተማ አስተዳደር በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የተሰሩ የአካባቢ ልማት ስራዎች መልካም ተሞክሮ ........ 17
1. መግቢያ፣ ዓላማ፣ አስፈላጊነትና መነሻ ሁኔታ ........ 17
2. የዝግጅት ምዕራፍ ........ 21
3. የትግበራ ምዕራፍ ........ 27
4. የማጠቃለያ ምዕራፍ ........ 49
ክፍል ሁለት ........ 55
ምዕራፍ አንድ፡- የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዳይዜሽን አስፈላጊነት እና ........ 55
የአገልግሎት አቅርቦት የማሻሻል ተግዳሮቶች ........ 55
1. መግቢያ ........ 55
2. የስታንዳርዳይዜሽን እና የስታንዳርድጽንሰ ሀሳብ /ምንነት/ ........ 56
3. የዜጎች የስምምነት ሠነድ /Citizene charter/ ፅንሰ ሐሳብና አስፈላጊነት፤ ........ 58
4. የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አቅርቦትን ለማሻሻል የተወሰዱ እርምጃዎች ........ 59
5. በከተሞች የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አቅርቦትን የማሻሻል ተግዳሮቶች ........ 61
6. የዜጎች እርካታ ፅንሰ ሐሳብ /ምንነት /concept of citizen satisfaction/ እና የመለካት አስፈላጊነት ........ 63
7. በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ........ 66
8. ማጠቃለያ ........ 69
ምዕራፍ ሁለት፡- የከሚሴ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት የአገልግሎት አቅርቦት መልካም ተሞክሮ ........ 70
1. መግቢያ ........ 70

2. የመሬት ልማት ማኔጅመንት የስራ ሂደት የአገልግሎት አቅርቦት ነባራዊ ሁኔታ ..................... 71
3. የአገልግሎት አቅርቦቱን ለማዘመን /ለማሻሻል/ መነሻ የሆኑ ምክንያቶች ..................... 71
4. የአገልግሎት አቅርቦቱን ለማዘመን በተደረገው ሂደት ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ..................... 72
5. ተግዳሮቶቹን ለመቅረፍ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ..................... 73
6. አገልግሎት አቅርቦቱ አሁን ያለበት ደረጃ/ሁኔታ ..................... 74
7. የለማበት ሁኔታ ..................... 75
8. የአገልግሎት አሰጣጡ ከማዋል ወደ ሶፍተዌር ኔትዎርኪንግ /አውቶሜሽን/ የተሸጋገረበት ሁኔታ 76
9. የአገልግሎት የግዜ ስታንዳርድ አመዘጋገብን በተመለከተ ..................... 76
10. የአገልግሎት አሰጣጡ ከማንዋል ወደ አውቶሜሽን በመሸጋገሩ የሚጠበቁ ውጤቶች ..................... 76
11. የአገልግሎት አሰጣጡ ከማንዋል ወደ ሶፍትዌር ኔትዎርኪነግ/አውቶሜሽን በመሸጋገሩ በመጡ ለውጦች ያሉ አስተያየቶች ..................... 77
12. የለማው ሶፍትዌር በቀጣይ የአገልግሎት አቅርቦቱን እና የመረጃ አያያዙን ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ግልጽ ከማገረግ አንጻር ለከተሞች የሚኖረው ፋይዳ ..................... 79
13. ማጠቃለያ ..................... 79
ምዕራፍ ሶስት፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር አገልግሎቶች ስታንዳርድ ትግበራ ተሞክሮ ..................... 92
1. መግቢያ /Introduction/ ..................... 92
2. የእሳት እና አደጋ ስጋት ስራ አመራር የቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ ..................... 95
3. የእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ስታንዳርድ ትግበራ ምዕራፍ ..................... 105
4. የማጠቃለያ ምእራፍ ..................... 128

# ክፍል አንድ

## ምዕራፍ አንድ፡- የህዝብ ተሳትፎ ጽንሰ ሃሳብ

### 1. መግቢያ

የህዝብ ተሳትፎ ለልማና መልካም አስተዳደር ግንባታ ያለው ጠቀሜታ ወሳኝ ስለመሆኑ በርካታ የአለም አቀፍና አገር አቀፍ ተሞክሮዎች ያስረዳሉ፡፡ በአገራችንም ይህንን በመገንዘብ በከተሞች ልማትንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት የህብረተሰቡ ሚና የጎላ እንዲሆን ለማድረግ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ከእነዚህም መካከል አሰራሩን ተቋማዊና መዋቅራዊ እንዲሆን ማድረግ፣ የአሰራር ማእቀፎች ማዘጋጀት፣ ለባለሙያዎችና አመራሮች እንዲሁም የሚመለታቸው አካላት የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ በዚህም በርካታ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራ በተፈጥሮው ውስብስብና የተለያዩ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግን የሚጠይቅ በመሆኑም በአንድ ጊዜ ጥረት ብቻ የሚወሰን አይደለም፡፡ በመሆኑም አሰራሩ የተጠናከረና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የክትትል ስራዎችን በማካሄድ በአተገባበሩ ዙሪያ ያሉትን ወቅታዊ ችግሮች መለየትና ድጋፍ ማድረግአስፈላጊ ነው፡፡ይህ የንቅናቄ መድረክም የዚህ አካል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ አመራሩ እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትም በዚህ ረገድ ያላቸውን ግንዛቤ በማሳደግ የአካባቢን ሁኔታ (context) ግምት ውስጥ ያስገባና ፈጠራ የታከለበት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ከተማን በማልማትና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት የነቃ ተሳትፎ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታ ማማቻቸት ይጠበቅባቸዋል፡፡ አሰራሩም የበርካታ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጥረት የሚጠይቅ በመሆኑም የትስስር (networking) አሰራሮችን ማጎልበትና በተደራጀ አቅም ወደ ስራ መግባት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በታች በሚገኙት የተወሰኑ ገፆች የተሸፈነው ፅንሰ ሀሳብም ይህንን ለማድረግ ያግዝ ዘንድ የቀረበ ሲሆን በውይይት እንደሚዳብር ይጠበቃል፡፡

### 2. መነሻ ሁኔታ፡ የህዝብ ተሳትፎና የከተሞች መልካም አስተዳደር

ከተሞችን የማስተዳደር ስልጣንና የማልማት ኃላፊነት የሁሉም የከተማው ነዋሪ ህዝብ ጉዳይ ጭምር በመሆኑ በመንግስት እና በህዝቡ መካከል ያለውን ርቀት ለማጥበብና በጋራ ለአንድ አላማ ለማሰለፍ የህዝብ ተሳትፎ ወሳኝ አማራጭ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም በውሳኔ

አሰጣጥ ሂደት ውስጥ  ትክክለኛነትን (balanced) ለማረጋገጥ፣ ችግሮችን በተሻለ መንገድ ለመረዳት እና ከህዝብ ጋር በቅርበት በመተባባር ለችግሮቹ መፍትሄ ለመሻት እድል ይፈጥራል፡፡ በከተሞች የመልካም አስተዳደርን የማስፈንና ዴሞክራሲን በተጨባጭ ተግባራዊ የማድረግ ሂደት የነዋሪ ዜጎችን ህይወት በሚነኩ ማናቸውም አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ የአካባቢውን ነዋሪዎች ቀጣይነት ባለው መንገድ በማሳተፍ ውሳኔዎች እንዲተላለፉ ከሚደረጉበት ሁኔታ ጋር በቀጥታ ተያያዥ ነው፡፡

ዴሞክራሲን በተሻለና ዘመናዊ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የዜጎችን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ በአንፃሩ አሳታፊ ዴሞክራሲ (participatory democracy) ለመገንባት ደግሞ ህዝባዊ በሆኑ የከተማ ልማት ጉዳዮች ዜጎች በብቃት መሳተፍ የሚያስችላቸው ተቋማዊ ማእቀፍ ሊበጅላቸው ያስፈልጋል፡፡ የዜጎችን የተሳታፊነት አጋጣሚዎችን ማጥበብ የዲሞክራሲ ባህልን ማቀጨጭ ነው፡፡ ዴሞክራሲ እውን ከሚደረግባቸው ስልቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው በአካባቢያዊ አስተዳደር ውስጥ ነዋሪዎች በሚመለከታቸው ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ የውሳኔ ሰጪነት ድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ በመሆኑ የዜጎች ተሳትፎ ለዲሞክራሲ መጎልበት የማአዘን ድንጋይ ነው፡፡

ቀጣይነት ያለው የከተሞች ልማትን ማረጋገጥ ጠንካራና ተግባራዊ የአካባቢያዊ ዴሞክራሲ በመገንባት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ህዝብ የተሻለ መረጃና ግንዛቤ ኖሮት ልማትን ሊያፋጥን በሚችሉ ውሳኔዎች ላይ በትክክል የሚሳተፍባቸውን እድሎች ከመፍጠር ውጭ የሚመጣ አይደለም፡፡

የህዝብ ተሳትፎ በመንግስት ውስጥ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት እንዲጎለብት ስለሚያደርግ ሙስናን ለመከላከል አይነተኛ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በከተሞች የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚኖሩ ክፍተቶችን ለማሳየትና የማስተካከያ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ አጋጣሚዎችን ስለሚፈጥር በከተሞች የመልካም አስተዳደር በመገንባት ረገድ ጉልህ ሚናን ይጫወታል፡፡

## 3. የህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ምንነት

በልማት ተግባራት ውስጥ ተሳትፎ አዲስ ፅንሰ ሀሳብ አይደለም፡፡ በልማት ፕሮግራሞች ውስጥ የህዝብ ተሳትፎ ወሳኝ ስለ መሆኑ በብዛት ስምምነት ላይ የተደረሰበት ጉዳይ ቢሆንም በፅንሰ ሀሳቡ ምንነት ላይ ግን ወጥ የሆነ አረዳድ አይስተዋልም፡፡ ተሳትፎ የሚለው ቃል የጉዳዩን ሁኔታ (context) መሰረት በማድረግ በተለያዩ መንገዶች ሊተረጎም የሚችል ሲሆን በነገሮችና ድርጊቶች

ላይ ዝም ብሎ ተባባሪ ከመሆን (passive collaboration) በንቃት ሚናዎችን እስከ መጫዎት (active role) ድረስ የሚዘልቅ ነው፡፡

ተሳትፎ ማለት አንድን ፕሮግራም በማቀድ፣ በመወሰን፣ በመተግበርና በመገምገም መሳተፍና ከጥቅሙም ተጋሪ መሆንን የሚያሳይ ሂደት ሲሆን ባጠቃላይ **የህዝብ/ የህብረተሰብ ተሳትፎ** ተመሳሳይ ፍላጎትና ግብ ያላቸው ሰዎች ህይወታቸው ላይ ተፅእኖ በሚያሳድሩ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ በማሳለፍ ሂደት ተሳታፊ የሚሆኑበት ሁኔታ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የመንግስት አካላትና ህብረተሰቡ በአጋርነት የልማት ፕሮግራሞችንና እቅዶችን የሚነድፉበትና የሚተገብሩበት ሂደት ሆኖ ህብረተሰቡን ከማማከር አልፎ በጉዳዩቹ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥና ችግሮቹን ለማስወገድ የበኩሉን ድርሻና ኃላፊነት እንዲወጣ የሚያደርግበት ሂደት ነው፡፡

**Community participation** is a process through which people influence and share control over development initiatives and the decisions and resources which affect them (World Bank, 1996).

**የህዝብ ንቅናቄ** ማለት ደግሞ በአንድ ፕሮግራም ትግበራ ላይ ለመሳተፍ ህዝብ የሚነሳሳበትና የሚበረታታበት ሁኔታነው፡፡ ህዝብን በተሳካ መልኩ ለማነቃነቅ ህዝብ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች እና ምን እንደሚያነሳሳቸው መለየት ያስፈልጋል፡፡ በሌላ አገላለፅ የህዝብ ንቅናቄ ማለት የህዝብ ተሳትፎን በማጠናከር ህብረተሰቡ በራሱ ጥረት የተቀመጡ የልማት ግቦችን ለማሳካት የሚያደርገው ሰፋ ያለ የለውጥ እንቅስቃሴ እንደሆነ የሚወሰድ ሲሆን በተመሳሳይ ህብረተሰቡ በራስ ተነሳሽነትና ጥረት ያለውን ሃብት ጉልበትና ጊዜ በማቀናጀት የጋራ ችግሮቹን በጋራ ለመፍታት ብሎም የጋራ ብልፅግና ለማምጣት የሚጠቅም መሳሪያና ዘዴም ነው፡፡

በአጠቃላይ የከተማ ልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎችን በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ መፈጸም ሲባል በከተማ ልማት አጀንዳዎች ላይ ህዝቡ መረጃ ኖሮት (informed) ሀሳብ ከመስጠትና በጉዳዩ ላይ በስፋት መክሮ እንዲወስን በማብቃት አቅዶ እንዲተገብር ብሎም አፈፃፀሙን ክትትል በማድረግ እንዲገመግም በማነሳሳትና በማበረታታት በተደራጀና ሰፋ ባለ ሁኔታ ወደ ስራ ማስገባት ነው፡፡

የህዝብ ተሳትፎ ስራ እምነትንና ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ እና በተለይም የዴሞክራሲ መርህ ተደርጎ የሚቆጠር፣ ከመደራጀትና ከመሰብሰብ መብት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ተግባር በመሆኑ የከተማ ልማትና የመልካም አሰተዳደር ሥራዎችን የምንመራበትና የምንፈጽምበት ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ በዚህም አመራሩና ባለሙያው በጉዳዩ ላይ እውቀት ኖሮት ዋነኛ ስራው አድርጎ ሙያዊ በሆነ አግባብ ሊፈጽመዉ የሚገባ የዘወትር ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡

## 4. በልማት ውስጥ የህብረተሰብ ተሳትፎ ምክኒያታዊ አስፈላጊነት

በህዝብ ተሳትፎ ላይ የተፃፉት ሰነዶች እንደሚያመለክቱት የህብረተሰብ ተሳትፎን የሚያካትት የልማት ተግባር ግቡ ልማትን ለማፋጠንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ሲሆን ይህንን እውን ለማድረግ በአካባቢ ልማት ጉዳዮች ላይ የተጠናከረ የህዝቦች ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑን ከሚያስረዱ ምክንያቶች መካከል፡ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

### 4.1. ህዝብ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ለመለየት

በአንድ ከተማ ውስጥ በአካባቢያዊ አስተዳደር ላይ የተሰማሩ አመራሮችና መሰል አካላት በእያንዳንዱ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ በተመሳሳይ ጊዜ የመጠመድ እድላቸው የሰፋ ስለሆነ የከተማው ህዝብ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ለይቶ ቅድሚያ ሰጥቶ በመስራት በኩል የሚፈለገውን ያህል አርኪ ላይሆን ይችላል፡፡ ይህ እንዳይከሰትና ህዝብ ቅድሚያ የሚሠጣቸውን ጉዳዮች በሚገባ ለይቶና በእቅድ ውስጥ በማካተት በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ለማከናወን እንዲቻል በአንድ አካባቢያዊ የልማት ጉዳዮች ላይ ህዝብ ሀሳብ ከማመንጨት ጀምሮ ተሳታፊ መሆን የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸትና በሚመለከተው ጉዳይ ላይ ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የህብረሰብ ተሳትፎ ህዝብ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ለይቶ ከአማራጮች መካከል የሚፈልገውን እንዲመርጥ ያስችላል፡፡ ይህን ለማድረግም አመራሩ ወይም ባለሙያዎች ከህዝቡ ጋር በጋራ በመሆን የቀረቡት አማራጮች አንዱ ከሌላው የሚኖረውን ጠቀሜታዊ ክብደትና አማራጩ ሊያስከትለው የሚችለውን ተጓዳኝ ችግር ግምት ውስጥ አስገብቶ ለመወሰን ያግዛል፡፡
አንድ ማህበረሰብ በውስጡ የሚኖረው የልማት ፍላጎት፣ ችግሮችና ለችግሮቹ መፍትሄ ይሆናሉ ብሎ የሚያስቀምጣቸው ጉዳዮች ትርጉም (definitions) ሌሎች በጉዳዩ ላይ የሚሰሩ አካላት ከሚኖራቸው ጋር የተለየሊሆን ስለሚችልና ለአፈፃፀም ይህንን ልዩነት አጣጥሞ ለማስኬድ የህዝብ ተሳትፎ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ይህም የሚሆነው የማህበረሰብ ተሳትፎ በባለሙያዎችና በህዝቡ መካከል ማህበራዊ መማማርን ('social learning') ለማምጣት የሚያግዝ በመሆኑ ነው፡፡ ማህበራዊ መማማር ማለት ጉዳዩን አስመልክቶ አንዳቸው ከሌላኛው የሚማሩበት በአካባቢው ማህበረሰብና በባለሙያዎች መካከል የሚኃለብት የርስ በርስ ትስስር ነው (WorldBank, 1966)፡፡ በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ የማህበረሰብ እውቀት በቦታው ላይ ልማትን በማፋጠን ችግሮችን ለመቅረፍ ጠቃሚ ሀብት በመሆን የትግበራ ልምዶችን የማኃልበት አቅምን ይፈጥራል፡፡

## 4.2. ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ እና ተጠያቂነትን ለማጎልበት

በከተሞች የዲሞክራሲ ትግበራ በአካባቢያዊ ጉዳዮች ተከታታይነት ያለው የነዋሪዎች ተሳትፎ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው፡፡ ሁሉም የከተማ ነዋሪ የየእለት እንቅስቃሴና ህይወቱን በሚነኩ አካባቢያዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ በሚተላለፉ ውሳኔዎች ላይ የመሳተፍ መብትና ኃላፊነት አለበት፡፡ የከተማ ነዋሪዎች ለአካባቢያቸው ልማት ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ቁሳቁስና ገንዘብ አስተዋፅኦ በማድረጋቸው የባለቤትነት ስሜት እያጎለበቱ ስለሚመጡ አካባቢያዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የበለጠ ተሳታፊ የመሆን አዝማሚያ ያሳያሉ፡፡ በዚህም ጉዳዩን አስመልክቶ በሚካሄዱ ስብሰባዎች ላይ በንቃት ከመሳተፍ ጀምሮ የልማቱን አፈፃፀም ክትትል እንዲያደርጉ ያስችላል፡፡ ይህም ተጠያቂነት ያለውና ምላሽ ሰጪ አካባቢያዊ አስተዳደር እንዲጠናከር ያደርጋል፤ የአሰራር ተጠያቂነት ማእቀፍና ባህል እንዲሻሻል በማድረግ የተሻለ አገልግሎት አሰጣጥና መብት ያጎናፅፋል፡፡

በከተሞች የህዝብ ተሳትፎን ማጠናከር ብዝሃነትን (pluralistic) የሚያከብርና ሁሉን አቀፍ (inclusive) ማህበረሰብ እንዲፈጠር በማስቻል የሁሉንም ነዋሪ ፍላጎት በማጣጣም ህዝባዊ የሆኑ የጋራ ጉዳዮች በእኩልነት በተባበረ ጥረት ተፈፃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል አጋጣሚዎችን ያሰፋል፡፡ የህዝብ ተሳትፎ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስና ህዝቡን የስልጣን ባለቤት ከምናደርግባቸዉ መንገዶች አንዱ ሥልጣንን ለዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ማውረድና ያልተማከለ አሰተዳደሩን ማጠናከር ነው፡፡

የህዝብ ተሳትፎ መንግስት ምን እና እንዴት እየሰራ እንደሆነ ነዋሪዎች ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ እና መንግስታዊ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን ተደራሽ ለመሆን አቅም የሚፈጥሩበት መንገድ በመሆኑ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት እንዲጎለብት ስለሚያደርግ ሙስናን ለመከላከል አይነተኛ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በከተሞች የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚኖሩ ክፍተቶችን ለማሳየትና የማስተካከያ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ ያግዛል፡፡

## 4.3. ሀብት ለማሰባሰብ

አገራችንን ጨምሮ በአለም ላይ የሚገኙ የአብዛኞቹ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች መንግስታት በዘመኑ የሚስተዋለውን የከተሜነት በፍጥነት መስፋፋት መሰረት በማድረግ የከተሞችን ልማት በማፋጠን ለኑሮ ተስማሚና ምቹ በማድረግ የህዝቡን ተጠቃሚነትና እርካታ ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ መንግስታት በሀብት እጥረትና አቅም ማነስ የተነሳ ይህንን ለማድረግ ብቁ እንዳልሆኑ ራሳቸውን ማየት ችለዋል፡፡ በከተሞች ልማትን በማረጋገጥ በፍላጎትና አቅርቦት መካከል ያለውን ክፍተት በሚፈለገው ፍጥነት ለማጥበብ የሚያስችል ሀብት ውስንነት

በመኖሩ ያለውን ውስን ሀብት መለየትና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስችሉ ዘዴዎችን መተግበር ያስፈልጋል፡፡

በከተሞች ሁሉንም የከተማ ልማት ጥያቄዎችና የህዝብ ችግሮች ወይም ፍላጎቶች በመንግስት ብቻ በቂ በሆነ ሁኔታ መፍታት ስለማይቻል ህዝቦች በሚመለከታቸው አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ በንቃት ተሳታፊ የመሆን ሚናቸውን እንዲወጡ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ የህዝብ ተሳትፎን አስፈላጊነት ከሚያረጋግጡት ምክኒያቶች ውስጥ አንዱ በአግባቡ ማንቀሳቀስና ስራ ላይ ማዋል ከተቻለ በከተማ ልማትን በማረጋገጥ ዘላቂነት ባለው መልኩ የከተማ ዜጎችን ህይወትና አኗኗር ሊያጎለብትና ሊያሻሽል የሚችል የፋይናንስ፣ የቁሳቁስ እና የሰው ኃይል (የእውቀት) በማህበረሰቡ ውስጥ ያለ መሆኑን የሚያሳየው ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ ነው፡፡

## 4.4. ችግሮችን ለመለየትና ምላሽ ለመስጠት (Identifying and Addressing Problems)

በአካባቢው ለሚካሄዱ ማናቸውም ጉዳዮች የአከባቢው ማህበረሰብ ምን መስራት እንደሚቻልና እንደማይቻል እንዲሁም ለምን መስራት እንደሚያስፈልግ ከማንም በላይ ብዙ ልምድና ግንዛቤ/ አረዳድ አለው፡፡ ይህም በአካባቢው ያለውን የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች የበለጠ ለመለየትና መፍትሄ ለማስቀመጥ አይነተኛ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

በአንድ ከተማ ወይም አካባቢ ለሚፈጠሩ የአካባቢያዊ ልማት ችግሮች እልባት ለማፈላለግ በመጀመሪያ በችግሩ ምንነትና ችግሩ እንዲፈጠር አስተዋፅኦ ስለሚኖራቸው ነገሮች ላይ በጋራ መግባባት ሊደረስበት ያስፈልጋል፡፡ ለችግሮች በመፍትሄነት የሚቀመጡ ተግባራት አዋጭነት የሚወሰነው በአካባቢው ስለ ችግሩ ምንነት በሚኖረው አረዳድ (ግንዛቤ) ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ ስለሚኖር በአካባቢው ያለውን ችግር ከምንጩ ለመረዳት የአካባቢውን ህዝብ ማሳተፍ ያስፈልጋል፡፡ ባለሙያዎች (experts) አካባቢያዊ ስለሆኑ ችግሮች ያላቸው እውቀት አናሳ ሊሆን ይችላል፡፡

በአንድ አካባቢ በሚፈጠር ችግር በቀጥታ ህይወታቸው የሚነካ የህብረተሰብ ክፍሎች ችግሩን ለመቅረፍ ስለሚያስችሉ ተግባራት የተሻለ ሀሳብ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በተለይ በጉዳዩ ላይ አዳዲስ ፈጠራዎችን ለማመንጨት በህዝቡ መካከል እምቅ አቅም ስለሚኖር ይህንን መገንዘብና ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡

ህዝብን በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ማሳተፍ ማህበረሰብ አቀፍ የሆኑ ጉዳዮችን መረጃ ለህዝቡ ተደራሽ በማድረግ ከህዝቡ ጥራት ያለው አስተያየት እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡ የህዝብ ተሳትፎ አንዱ

ግብ በአንድ ጉዳይ ላይ ከህዝቡ ትርጉም ያለው ምላሽ መቀበልና አስተያየቶችም ዋጋ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡

የነዋሪዎች ተሳትፎ ሁሉን አቀፍ በሆኑ የከተሞች ልማትና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች የተሻሉ አማራጮችን ሊያቀርቡ የሚያስችሉ ሀሳባዊ ፈጠራዎችን ማመንጨት ያስችላል፡፡ ህዝብ በአካባቢው ስላለው ሁኔታ ወይም የተላለፉ ውሳኔዎች እንዴት መተግበር እንዳለባቸው የሚያሳይ ወሳኝ የሆነ መረጃዎች ባለቤት ነው (ክሪግተን፡ 2005)፡፡ ህዝብን በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ማሳተፍ ግንዛቤ እንዲሰፋ እና የተለያዩ አማራጮች ግምት ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ የልማት ፕሮግራሞችና የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቶች እንዲሻሻሉ ያደርጋል፡፡

## 4.5. ህዝባዊ መንፈስ እና ተሳትፎን ለማጎልበት

በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የህዝቦች ተሳትፎ መኖር በነዋሪዎች ዘንድ ህዝባዊ መንፈስን ለማጎልበት ያስችላል፡፡ የህዝብ ተሳትፎ ከሚያበረክታቸው በርካታ ጠቀሜታዎች ውስጥ አንዱ ችግሮች ላይ በጋራ እንደ ቡድን በመስራት የአመራር ክህሎት መማማሪያ መሆኑ ነው፡፡ ማህበረሰብ አቀፍ በሆኑ የጋራ ጉዳዮች ላይ ነዋሪዎች በተሳተፉ ቁጥር እንዱ ሌላውን እንዴት እንደሚደግፈው ወይም እንደሚያበረታታው እና ጠንካራ ህብረት እንደሚገነቡ መገንዘብ ያስችላል፡፡ በጋራ አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ የበለጠ ተሳታፊ መሆን፣ ለነዋሪዎች ተስማሚ የሆነ አመለካከት የበለጠ ለማዳበር ያስችላል፡፡

በአካባቢያዊ ልማት ጉዳዮች ላይ የአካባቢውን ማህበረሰብ ፕሮጀክቶችን በማቀድና ትግበራ ላይ እንዲሳተፍ ማስቻል ለስራው ተፈፃሚነት ህዝቡ የሚኖረውን ትጋት እንዲጨምር ከማድረጉም በላይ ጉዳዩን አስመልክቶ እንደ ሁኔታው የቴክኒካልና ስራ አመራር ክህሎት፣ እውቀትና ልምድ እንዲያዳብሩ እድል የሚፈጥር በመሆኑ ለወደፊት ህይወታቸው ወሳኝ መሰረትን ይጥላል፡፡

ንቁ ማህበረሰብ የለማና ደህንነቱ የተረጋገጠ አካባቢን ለመፍጠር መሰረት ነው፡፡ ለህዝብ ጥራት ያለውና ትክክል የሆነ መረጃ መስጠትና በጋራ ጉዳዮች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ማስቻል ነዋሪዎች ያላቸው በራስ መተማመን እንዲጨምርና በማህበረሰብ ውስጥም ድርሻ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ የነዋሪዎች ተሳትፎ በተፈጥሮው መልካም ነው፡፡ ምክንያቱም በከፍተኛ ሁኔታ የሰዎችን አቅም ያጎለብታል፡፡ ነዋሪዎች አካባቢያዊ በሆኑ አስተዳደራዊ ጉዳይ ውሳኔዎች ላይ ተቀባይ ብቻ ከሚሆኑ በንቃት ተሳትፈው የራሳቸውን ተፅእኖ የማሳረፍ ብቃት እንዳላቸው ራሳቸውን ማየት (perceive) ከቻሉ ከአካባቢው አስተዳደር ጋር በጋራ በመሆን በአካባቢው ልማትና መልካም አስተዳደር ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ፡፡ በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ የህዝብ ተሳትፎን ማጠናከር ማህበራዊነትን በማጎልበት ህዝባዊ መንፈስ እንዲጎለብትና በውስጡም ያሉት

ግለሰቦች አስተዋፅኦ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ግንዛቤው የዳበረና በልማት ላይ የሚሳተፍ ዜጋ በዙሪያው ያሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ስትራቴጂካዊ በሆነ መንገድ የሚረዳና ሁሉን አቀፍ ማህበረሰባዊ እልባቶችን ማስቀመጥ የሚችል ይሆናል፡፡

## 4.6. የተሻሉ የልማት ውጤቶችን ለማስመዝገብ

እንደ ሚታወቀው በማደግ ላይ ባሉት አገሮች የከተሜነት መስፋፋት ፍጥነትና ይህም በመሰረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦት ላይ የሚያሳድረውን የፍላጎት ጫና ምላሽ ለመስጠት መንግስት ብቻውን ሊወጣው የማይችለው ዳገት መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ በመሆኑም መሰረተ ልማትን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎቶችን ለማቅረብ የህብረተሰብ ተሳትፎ አይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ ለዚህም በማስረጃነት ከሚቀርቡት ውስጥ በሁሉም ከተሞች የኮብል ስቶን መንገድ ሌሎችም መሰረተ ልማቶች አቅርቦት በተጨባጭ በስፋት መቅረባቸው ነው፡፡

## 4.7. የማህበራዊ ሀብትን (Social Capital) ለመገንባት

በአካባቢያዊ ጉዳዮች የነዋሪዎች ተሳትፎ መጠናከር የማህበራዊ ሀብት (social capital) መኖር አመላካች ነው፡፡ ማህበረሰቡ የሚኖረው የማህበራዊ ሀብት ደረጃ ከፍ ማለት የአካባቢው አስተዳደራዊ ጉዳዮች ጥራት እና አጠቃላይ ማህበራዊ ስኬት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ ማህበራዊ ሀብትየአንድን ማህበረሰብ የጋራ ጥቅም ለማስገኘት በመካከላቸው ያለውን ቅንጅትንና ትብብር ያሚያፋጥኑ በእርስበርስ ትስስር (networks)፣ በጋራ ህግጋቶች (norms)፣ እና ማህበራዊ መተማመን (social trust) የሚገለፅ ማህበራዊ አደረጃጀት ነው (ፑትናም፡ 2007)፡፡ አካባቢያዊ በሆኑ የጋራ ጉዳዮች ላይ ህዝቡን ማሳተፍ በህዝብ እና መንግስት መካከል ማህበራዊ ሀብትንለማጠናከር እድል ይሰጣል፡፡ ይህም አጠቃላይ የማህበረሰቡን ሁኔታ ያሻሽላል፡፡

የእርስ በርስ መረዳዳትን መርህ ተግባራዊ የሚያደርግ ማህበረሰብ በተሻለ ሁኔታ ልማትን ማረጋገጥ ይችላል፡፡ ተሳትፎ ሰዎች እርስ በርሳቸው በመቀራረብ በተደራጀ አኳኋን በጋራ የመስራትን ዋጋ እንዲገነዘቡ ስለሚያደርግ ማህበራዊ ትስስርን (social cohesion) ያጎለብታል፡፡

## 4.8. በአካባቢያዊ ልማት ቀጣይነት ያለው ድጋፍን ለማረጋገጥ

በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ነዋሪዎችን ማካተት ለአካባቢያዊ ልማት ፕሮጀክቶች የረጅም ጊዜ ድጋፍ መሰረት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ተሳታፊነትን ማጠናከር ለተላለፈው ውሳኔ የባለቤትንነት ስሜትን ይፈጥራል፡ በተጨማሪም ውሳኔው አንዴ ከተላለፈ በኋላ ተግባር ላይ ውሎ የማየት ፍላጎትን ያሳድራል፡፡ እንዲሁም በአካባቢው የሚካሄዱ እቅዶችና ፕሮጀክቶች ትግበራ ድጋፍ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ውሳኔዎች የጋራ ሲሆኑ በአካባቢው ነዋሪ በቀላሉ ተቀባይነት

ማግኘት ይችላሉ በተጨማሪም በማህበረሰቡ ውስጥ የኄነት ስሜትንያጎለብታሉ፡፡ ውጤታማ የህዝብ ተሳትፎ የረጅም ጊዜ የማህበረሰብ ድጋፍን በማስገኘት የአካባቢ ልማት እቅዶች ወይም ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ያሻሽል፡፡

ችግሮችን በመገንዘብና መፍትሄ በማፈላለግ ረገድ የህዝቡን ተሳተፎ ማጠናከር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን የህዝብን ድጋፍ መሰረት ለመገንባት ያግዛል፡፡ ቀጣይነት ያለው የህዝብ ተሳትፎ በአካባቢው የተለየውን ችግር ለመቅርፍ የሚወሰዱ የተግባር እርምጃዎች ሊያመጡት የሚችሉትን አዳዲስ ተያያዥ ችግሮች አስቀድሞ በወቅቱ ትኩረት ማግኘት እንዲችሉ ከማድረጉም በላይ የማህበረሰብ አባላት በጉዳዩ ላይ የባለቤትነትስሜትና በራስ መተማመን እንዲያዳብሩ ስለሚያስችላቸው ልማቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ያግዛል፡፡

## 5. የህዝብ ተሳትፎ አይነቶችና ደረጃዎች

የህብረተሰብ ተሳትፎን እውን ለማድረግ በርካታ አቀራረቦች (approaches)፣ ሂደቶችና መሳሪያዎች (process and tools) ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆን እንድና ብቸኛ መንገድ ግን የለም፡፡በአንድ አካባቢ ስኬታማ የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራን ለመተግበርየአካባቢውን ሁኔታ መሰረት በማድረግ ለሁኔታዎች ተስማሚ ለማድረግ የፈጠራ አካሄዶችን መተግበር አስፈላጊ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በከተሞች የህዝብ ተሳትፎን ለማጠናከር መነሻ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ የሼሪ አርንስቲን የህዝብ ተሳትፎ ሞዴል (1969) ፅንሰ ሃሳብ እና ይህንን መሰረት አድርገው ተሻሽለው የቀረቡ ሌሎች ሞዴሎችን በመነሻነት መውሰድ አስፈላጊ ሲሆን ለአረዳድና ትግበራ ቀላል እንዲሆን የሚከተለውን አምስት ደረጃዎች ያሉት የአለም አቀፍ የህዝብ ተሳትፎ ማህበር ሞዴል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**Five stages of people's participation as proposed by The International Association for Public Participation (IAP2 2003)**

1. **Inform:** one way communication,
2. **Consult:** two-way communication,
3. **Involve:** Deciding together,
4. **Collaborate:** Acting together, and
5. **Empower:** developing the capacity of people to come with their decisions and resources to implement development programs

የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራ ነጠላ ክስተት (single event) ባለመሆኑ ስራውን ለማከናወን የሚያስችል አንድና ብቸኛ የሆነ ትክክለኛ ዘዴ የለም፡፡ በመሆኑም የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራ በአካባቢው ለሚኖረው ሁኔታና በጉዳዩ ላይ ተሳታፊ ለሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች ተስማሚ የሆኑ በርካታ ዘዴዎችን የሚጠቀም በጥንቃቄ የሚታቀድ ሂደት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ጠንካራ የህብረተሰብ ተሳትፎን እውን በማድረግ ውጤታማ ለመሆን የሚያስችሉ ማናቸውም ስልቶች የአካባቢውን ነዋሪ ህብረተሰብ በጥንቃቄ መዳሰስና መገምገም ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል የተለየና በባህሪው ውስብስብ ስለሆነ ነው፡፡ ለምሳሌ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ህዝቦች ተመሳሳይ ላይሆኑ ይችላሉ በመሆኑም ማንነታቸውንና በመካከላቸው ያለውን የሃይል ሚዛን (power balance) ጨምሮ ህብረተሰባዊ ሁነታቸውን (Community context) ማጥናትና መረዳት ወሳኝ ነው፡፡ በተጨማሪም በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ከዚህ በፊት የነበራቸውን የተሳታፊነት ደረጃ ወይም መጠን፣ ተቋማዊ፣ ቴክኒካዊ፣ ፋይናንሻልና ፖለቲካዊ አቅም የመሳሰሉትን መዳሰስ አስፈላጊ ነው፡፡

የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራ በጥንቃቄ ማቀድንና ለምን ተግባራዊ ማድረግ እንደተፈለገ መረዳትን ይጠይቃል፡፡ የህብረተሰብ ተሳትፎን ተግባራዊ ከማድረጋችን በፊት የሚከተሉትን የመወሰኛ ጥያቄዎች (framing questions) መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡

- **ለምን?** ተሳትፎው ያስፈለገበት መክንያት
- **ምን?** አላማው/ እንዲመጣ የሚፈለገው ውጤት
- **ማን?** ተሳታፊው ማን ነው፣ ፍላጎታቸው፣ ልምዳቸው፣ እሴቶቻቸው
- **እንዴት?** የተሳትፎው አቀራረብ (approach)፣ ስልት፣ መሳሪያዎች
- **መቼ?** የጊዜ ገደብ
- **የት?** ቦታ/ አካባቢ

ሌላው መታየት የሚገባው ጠቃሚ ነጥብ የህብረተሰብ ተሳትፎ በየትኞቹ ተግባሮች ላይ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል የሚለው ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የህብረተሰብ ተሳትፎ በማንኛውም ቦታ፣ በየትኛውም ጊዜና ሁኔታ ተፈፃሚ የሚሆንበት መንገድ ተመሳሳይ ሊሆን ስለማይችል፤ ይህም የሚወሰነው የተለያዩ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ በማስገባት በመሆኑ ሁሉንም ሊሸፍን (exhaustive) በሚችል መልኩ በዚህ ጊዜ ተግባራዊ ይደረጋል ብሎ መደምደም አይቻልም፡፡ ይሁን እንጂ የጋራ (common) የሆኑና በአካባቢ ልማት ጉዳዮችም በስፋት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልባቸውን የተወሰኑ ተግባራት በመለየት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **የፍላጎት ዳሰሳ (need assessement)፡** ሰለሚፈለገው ለውጥ ሃሳብን መግለፅ፣ ግቦችን በማመዛዘን ቅድሚያ መስጠት (prioritizing)፣ የመንግስት አካላት ጋር መደራደር፣

- **ማቀድ** (planning)፡ አላማዎችንና ግቦችን መቅረፅ፣ እቅድ መተቸት፣
- **ንቅናቄ** (mobilizing)፡ የማህበረሰቡን ግንዛቤን ማሳደግ፣ በህበረተሰቡ ውስጥ አደረጃጀታዊ መዋቅር መፍጠርና መደገፍ፣
- **ሀብት ማሰባሰብ፡** በጥንቃቄና በስርዓት ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ ህብረተሰብ ለልማት የሚውሉ የተለያዩ ሀብቶች ባለቤት ነው
- **ስልጠና** (training)፡ የህብረተሰቡን ተግባቦት፣ የመሰረተ ልማት ግንባታ፣ ጥገና፣ እና የገንዘብ አስተዳደር ክህሎትን ለማጎልበት መደበኛና መደበኛ ባለሆነ የስልጠና ተግባር ላይ መሳተፍ፣
- **ትግበራ** (implementation)፡ አስተዳደራዊ በሆኑ ተግባራት መሳተፍ፣ በገንዘብ፣ በጉልበት፣ በቁሳቁስ በግንባታና ጥገና ቀጥተኛ አስተዋፅኦ ማድረግ፣
- **ክትትልና ግምገማ** (monitoring & Evaluation)፡ የተከናወኑ ስራዎችን መገምገም፣ ሊመጡ የሚችሉ ለውጦችን ማወቅና ፍላጎቶችን ማጣጣም ውስጥ መሳተፍ፣

በተጨማሪም የጉዳዩን አይነት መሰረት በማድረግ ልዩነትን የሚያስተናግድ ሆኖ አንዳንድ ጊዜ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉም በጉዳዩ ላይ እኩል ተሳትፎና አስተዋፅኦ ማድረግ ማይችሉ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ በንቃት ሊሳተፉ የሚችሉትን ወሳኝ የህብረተሰብ ክፍሎችን (ግለሰቦችና ቡድኖች) ለመለየት ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ለመገምገም የሚያስችል ጠቃሚ መሳሪያየባለድርሻ አካላት ትንታኔ (stakeholder analysis) መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

## 6. የከተማ ህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄን ለመምራት የምንከተላቸው ስልቶች

በከተማ ልማት ስራዎች ትርጉም ያለውና ውጤታማ የሆነ የህዝቦች ተሳትፎን እውን ለማድረግ በከተሞች ያለውን ተጨባጭ ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ አዋጪነት ያላቸውና ዘርፍ ተኮር የሆኑ አካሄዶችንና ስልቶችን ለይቶ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ እነዚህም፡

- አጀንዳ መቅረጽና የኮሚኒኬሽን ስራዎችን ማጎልበት፣
- የከተሞችን አቅም መገንባትና የህዝቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣
- የአሳታፊ ፕሮጀክት ዝግጅትና ትግበራ ስራዎችን ማጠናከር፣
- የተሳትፎ አደረጃጀቶችን ማጠናከር፣
- የሀብት አሰባሰብና አስተዳደር ስርዓትን ማጎልበት፣
- ዝቅተኛ የከተማ አስተዳደር እርከንን የህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ማእከል እንዲሆን ማጠናከር፣

- የግሉን ዘርፍ ተሳትፎና አጋርነት ማሳደግ ናቸው፤

## 7. የህዝብ ተሳትፎ መተግበሪያ መሳሪያዎች (Tool box)

በከተማ አካባቢያዊ ልማት ፕሮጀክቶችና አገልግሎቶች አተገባበርና አስተዳደር ውስጥ የህዝብ ተሳትፎ ለዜጎች በቀላሉ መረጃ ከመስጠት እስከ በንቃት ተሳታፊ ማድረግ ድረስ የተለያዩ የተሳታፊነት ደረጃዎች ተግባራዊ የሚደረጉበት በመሆኑ እነዚህን ግልፅና ቀጥተኛ በሆነ አሰራር በተግባር መተርጎም የሚያስችሉ መሳሪያዎችን (tools) መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በከተማ ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች በሚመለከታቸው ጉዳዮች ላይ ያላቸው አረዳድና አተያይን መሰረት በማድረግ የሚሰነዝሩት ሀሳብ መደመጥ ብቻ ሳይሆን በአካባቢያዊ ልማት ውሳኔዎች ላይም እንዲንፀባረቅ በማድረግ መንግስት ለህዝቡ ተጠያቂነትና ምላሽ ሰጪ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡

በከተሞች በሚወጡ እቅዶችና መሰል አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ በሚካሄዱ ስብሰባዎች ላይ የአከባቢው ነዋሪ ግለሰቦች ተገኝተው አስተያየታቸውን እንዲሰጡ የሚደረግበት የህዝብ መድረክ (public hearing) በተለምዶ ሲተገበር መቆየቱ አበረታች ቢሆንም በከተሞች እንደ ሁኔታው የሚያዙ ልማታዊ አጀንዳዎችን መሰረት በማድረግ በአካባቢያዊ ልማት ጉዳዮች ላይ የህዝብ ተሳትፎን በተለያዩ ደረጃዎች የበለጠ ለማጠናከር ሌሎች በዚህ ውጤታማ የሆኑ ስልቶችን መተግበር ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች ከዚህ በፊት የከተማ ህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄን ለማስፈፀም የተቀመጡ ስልቶችን የሚተኩ ሳይሆን ስልቶቹ ወደ ተግባር ተቀይረው የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያግዙና (complementary) እንደሆኑ መገንዘብና አጣጥሞ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

**Tools to build different types of participation፡**

- Information Publication
- Public meetings
- public hearings
- study circles,
- citizen advisory groups
- Survey
- Public watch dog  groups

**መቼ እና እንዴት?**

**ለተሳትፎ ትክክለኛ የሆነውን መተግበሪያ መሳሪያ** (tool) **መምረጥ ተሳትፎው እንዳስፈለገበት ምክንያት ይወሰናል፡፡ የሚከተሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ አመራረጣችን የተለያየ ሊሆን ይችላል፡**

- **የተሳትፎው አላማ/ የሚፈለገው ውጤት፣**
- **የማህበረሰቡ ፕሮፋይል** (social-political context)
- **የፕሮጀክት መጠን፣ ጊዜ፣ ሀብት**
- **ተሳትፎውን የሚያስተገብረው አካል ክህሎት፣**

## 8. የከተማ ህብረተሰብ ተሳትፎ ስራ ተግዳሮቶች (Challenges)

- Institutional Structure (EX. Addis Ababa, Tigray)
- The extent of awareness on the part of the residents, experts, higher officials
- The level of cooperation on the part of city government- political passivity Resource

## ምዕራፍ ሁለት፡- የሃላባ ቁሊቶ ከተማ አስተዳደር በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የተሰሩ የአካባቢ ልማት ስራዎች መልካም ተሞክሮ

### 1. መግቢያ፣ ዓላማ፣ አስፈላጊነትና መነሻ ሁኔታ

#### 1.1. መግቢያ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሀላባ ከተማ አስተዳደር በህብረተሰብ ተሳትፎና ንቅናቄ ያስመዘገበውን ውጤት በመልካም ተሞክሮነት በመቀመር ለሀገራችን ከተሞች በማስፋት ከተሞች የሀላባን ከተማ ተሞክሮ የሚያገኙበትን እድል ማመቻቸትን አላማ በማድረግ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን መቆየቱ ይታወሳል፡፡ በዚሁም መሰረት ይህ የተሞክሮ ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን ሰነዱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጀው የለውጥ ትግበራና የልማት ሥራዎች አፈፃፀም ምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት ማንዋልን መሰረት በማድረግ በቅድሚያ በከተማ አስተዳደሩ በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የተሰሩ የልማት ስራዎችን ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎችና የልማት ኮሚቴዎች ጋር በጋራ በመሆን በማንዋሉ በቀረበው የመልካም ተሞክሮ መለያ ቼክ ሊስት መሰረት በመለየት ለመልካም ተሞክሮ በሚሆን መልኩ በመቀመር የተዘጋጀ ነው፡፡

በዚሁም መሰረት የሀላባ ከተማ በቼክ ሊስቱ ከቀረቡ መመዘኛዎች አንጻር በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ስራዎች በመልካም ተሞክሮነት ለሌሎች የሀገራችን ከተሞች ሊሰፋ የሚችል ስራ በማከናወኑ ተሞክሮው ከዚህ እንደሚከተለው ተቀምሮ ቀርቧል፡፡

#### 1.2. ተሞክሮውን የመቀመሩ አላማ

በሀላባ ከተማ አስተዳደር በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የተሰሩ የአካባቢ ልማት ስራዎች በህብረተሰቡ ዘንድ ባመጡት ፋይዳ መሰረት ተሞክሮው የሚቀመርበትና ለሌሎች የሀገራችን ከተሞች የሚሰፋበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡

#### 1.3. ተሞክሮውን የመቀመሩ አስፈላጊነት

ይህ መልካም ተሞክሮ በሀላባ ከተማ አስተዳደር በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የተሰሩ የአካባቢ ልማት ስራዎች ውጤታማ በመሆናቸው ወደ ሌሎች የሀገራችን ከተሞች ቢስፋፉ ውጤት ማስመዝገብ የሚቻል በመሆኑና በተጨማሪም እነዚህ በተግባር ተፈትሸው ጎልተው የወጡ የአካባቢ ልማት ሥራዎች ነጥረው እንዲወጡ በማድረግ እና በህብረተሰቡ የተገኙ አዳዲስ የፈጠራ ግኝቶችን ወደ ሌሎች ከተሞች በማስፋት የስራ ድግግሞሽን በመቀነስ ጊዜን፣ ወጪንና የሰው ኃይልን በአግባቡ እንድንጠቀም ለማስቻልና በሌሎች ከተሞች ማስፋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

## 1.4. የተሞክሮው ቅመራ ሂደት

በሀላባ ከተማ በከተማ ስራዎች ላይ ከዚህ በፊት የነበረው የህዝብ ተሳትፎ አነስተኛ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከአደረጃጀት ጀምሮ አመርቂ ስራዎችን በመስራትና የህዝብ ንቅናቄን በማቀጣጠል አበረታች ስራ ተሰርቷል፡፡ በመሆኑም ተሞክሮው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አግባብ የተቀመረ ነው፡፡

- ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ከህዝብ ተሳትፎ አስተዳደር ማጠናከሪያና ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት የተውጣጣ የባለሙያ ቡድን በማሰማራት፣
- የከተማውን ህዝብ ለማደራጀት የነበሩ እንቅስቃሴዎችን በመዳሰስ፣
- የህዝቡን በየደረጃው ያለውን የአደረጃጀት ግምገማ ሪፖርቶችን በመዳሰስ፣
- ከዚህ በፊት በከተማው የተሰሩትን ስራዎች በዚህ ዓመት ከተሰሩት ጋር በማነጻጸር እንዲሁም የአካባቢውን ህብረተሰብ እርካታን መሰረት በማድረግ፣
- በመስክ ምልከታ በተጨባጭ መሬት ላይ የተሰሩ ስራዎችን በማየት፣ በውይይት፣ በቃለ መጠይቅና ፎቶ/በምስል/ በማንሳት ነው፡፡

### 1.4.1. የመረጃዎች ዕውነታነት

- የተሞክሮውን እውነታ ለማረጋገጥ በተሞክሮው ውስጥ ህብረተሰቡን በማነጋገር፣ በከተማ አስተዳደሩ በህብረተሰብ ተሳትፎ ዙሪያ የተዘጋጁ የተሞክሮ ሰነዶችን በመፈተሽ እና በቂ የሆኑ የፎቶግራፍና የቪዲዮ መረጃዎችን በማጠናከር የተቀመረ በመሆኑ አንዳችም ጥርጣሬ ሳይኖር በቂ መረጃዎችን በመጠቀም የተቀመረ ተሞክሮ ነው፡፡

## 1.5. የሀላባ ከተማ ነባራዊ ሁኔታ

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሀላባ ልዩ ዞን ስር የምትገኝ ከተማ ስትሆን ከአዲስ አበባ ከተማ በስተደቡብ አቅጣጫ የምትገኝና ከአዲስ አበባ ቡታጅራ ባለው መንገድ 245 ኪ.ሜ የምትርቅ ሲሆን ከአዲስ አበባ በዝዋይ በኩል በሚወስደው መንገድ ደግሞ በ320 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ከክልሉ መዲና ሀዋሳ ደግሞ በ90 ኪ.ሜ ላይ ትገኛለች፡፡

ከተማዋ 5 ቀበሌዎችና 2 ክፍለ ከተማ ያሉዋት ሲሆን በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በ1887 አካባቢ የተቆረቆረችና ከ1,700 እስከ 2200 ሜትር ከባህር ወለል በላይ የምትገኝ የአየር ጸባይዋም ወይናደጋ የሆነ ከ994.66 ስኩዌር ኪ.ሜ በላይ ስፋት ያላት ለኑሮ ምቹ የሆነች ከተማ ስትሆን

ነዋሪውም በታታሪነቱና በስራ ተምሳሌትነቱ የሚጠቀስ፣ የጋራ ችግሮችን በቅንጅትና በነቃ የህዝብ ተሳትፎ ለመፍታት የሚረባረብ፣ በከተማዋ በሚከናወኑ ዘርፈ ብዙ የልማትና መልካም አስተዳደር ስራዎች ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ የሚገኝ ህዝብ ባለቤት ናት፡፡

የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በ1999 ዓ.ም ባካሄደው የህዝብ ቆጠራ መሰረት በሀባባ ቂሊቶ ከተማ ከ232,325 በላይ ነዋሪዎች ሲኖሩ ከእነዚህ ውስጥ ወንድ 117,291 ሴት 115,034 የሚሆነውን ቁጥር ይይዛሉ፡፡ ከተማዋ ወደተለያዩ ከተሞች መተላለፍያ መስመር ላይ የምትገኝ እንደመሆኗ ሰፊ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴ የሚስተዋልባትና በዛላ በርበሬ ምርቷ ታዋቂ ከተማ ስትሆን እንደ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ማሽላ እና ስንዴ የመሳሰሉ ሰብሎችንም ታበቅላለች፡፡ ሀላብኛ የስራ ቋንቋዋ ሲሆን ስልጢኛ፣ ከምባትኛ፣ አማርኛ እና ሀድይኛ ቋንቋዎችም በከተማዋ ይነገራሉ፡፡

በከተማዋ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተመዘገበ ባለው ፈጣንና ተከታታይ እድገት መሰረት መላው የከተማውን ነዋሪ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ብሎም ከተማዋን በኢንቨስትመንት፣ በጽዳትና ውበት እንዲሁም የቱሪዝም ማዕከል የማድረግ ራዕይ በመያዝ የከተማ አስተዳደሩ ሰፊ የህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

## 1.6. መነሻ ሁኔታዎች /ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች/

ቀደም ሲል በከተማዋ የህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ስራዎችን የሚመራና የሚያስተባብር ከከተማ እስከ ልማት በድን የወረደ ጠንካራ አደረጃጀት ባለመኖሩ ነዋሪው ለተለያዩ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ተጋላጭ ነበር፡፡ ለአብነትም በከተማዋ ዋና ችግር የነበረው ከፍተኛ የሆነ የጎርፍ አደጋ ሲሆን በመሰረተ ልማት፣ በደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ እንዲሁም በአረንጓዴ ልማት ረገድም ከፍተኛ ችግር ይስተዋል ነበር፡፡

ነዋሪውም ከአመለካከት ችግሮች የተነሳ ቀደም ሲል በልማት ስራዎች ላይ የነበረው ተሳትፎ ዝቅተኛና በተደጋጋሚ ቅስቀሳዎችና በልመና የሚሳተፍ የነበረ ሲሆን በከተማዋ የነበሩ መንገዶችም አቧራ ከመሆናቸውም በላይ በዝናብ ወቅት ውሃ በማቆር ህብረተሰቡን ለተላላፊ በሽታዎችና ለወባ በሽታ ተገላጭ ያደርጉት ነበር፡፡ ለአብነትም ያህል በከተማዋ ከሚገኙ መንደሮች አንዱ በሆነው መንደር 39 እና 07 መንደሮች በከፍተኛ ደረጃ ህብረተሰቡ ለመኖር የማይፈልግባቸውና ለከፍተኛ የጎርፍ አደጋ ተጋላጭ መንደሮች ነበሩ፡፡ የከተማዋን ሰላምና ጸጥታ በማስጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ችግር የነበረበትና የተለያዩ ወንጀሎችም ይስተዋሉ የነበረበት ከተማ ነበር፡፡









**የሀላባ ቁሊቶ ከተማ ከፊል ገጽታ**

## 2. የዝግጅት ምዕራፍ

### 2.1. የከተማ የህዝብ ተሳትፎ ልማት ስራዎች አላማ

የከተማ ህዝብ ተሳትፎ ስራዎች ዋነኛ አላማ የከተማውን ነዋሪዎች ጥቅም፣ ምኞትና ፍላጎት መሰረት በማድረግ ህብረተሰቡ ለከተማው እድገት የሚረዳ ሃሳብ ከማመንጨት ጀምሮ ችግሮችን እስከመለየትና የመፍትሄ አካል በመሆን በአካባቢ የልማት ስራዎች እቅድና ትግበራ ላይ በመሳተፍ እንዲሁም በመገምገምና በመከታተል ወሳኝ ተሳትፎ የሚያደርግበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡ በመሆኑም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ከተያዙ ግቦች መካከል በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ረገድ መልካም ተሞክሮ ያላቸው ከተሞች ተለይተው ተሞክሮአቸው የሚቀመርበትና ለሌሎች ከተሞች የሚሰፋበት ግብ አንዱ ሲሆን በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ 5 ተሞክሮዎችን ለመቀመርና ለማስፋት በህዝብ ተሳትፎ አስተዳደር ማሻሻያና ማጠናከሪያ ዳይሬክቶሬት የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በዚሁም መሰረት ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ስራዎች ዙሪያ ለተሞክሮ የሚሆን የተሻለ ተግባር ያከናወኑ ክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን በየአመቱ በመለየት የተሻለውን ከተማ ተሞክሮ ለመቀመር በተደረገው እንቅስቃሴ መሰረት የሀላባ ቁሊቶ ከተማ መልካም ተሞክሮ አንዱ ሆኖ በመገኘቱ ተሞክሮው ሊቀመር ችሏል፡፡

በሀላባ ቁሊቶ ከተማ በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የተሰሩ ስራዎች መልካም ተሞክሮን ለመቀመር በዝግጅት ምዕራፍ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ተሞክሮው መልካም ተሞክሮ መሆኑን በተመለከተ ልየታ ማከናወን/መለየት አንዱና ዋነኛው ተግባር ነበር፡፡ በዚሁም መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጀው የተሞክሮ መለያና መቀመሪያ ማንዋል መሰረት የልየታ ቼክ ሊስት በማዘጋጀትና ቡድን አደራጅቶ ወደ ስፍራው በመላክ የመስክ ምልከታ እና መረጃዎችን የማሰባሰብ ስራን ማከናወን ተችሏል፡፡

በመቀጠልም ተሞክሮውን ለመቀመር አንድ ቡድን ወደ ስፍራው በማቅናት በቀረበው የልየታ ሪፖርትና በማንዋሉ መሰረት በከተማ አስተዳደሩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር በመሆን በህብረተሰብ ተሳትፎ የተሰሩ የአካባቢ ልማት ስራዎችን ተዘዋውሮ በመመልከትና በቼክ ሊስቱ መሰረት የተከናወነ መሆኑን በማረጋገጥ፣ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ የከተማ አስተዳደሩ የስራ ኃላፊዎችንና የስራው ባለቤትና ተጠቃሚ የሆነውን የህብረተሰብ ክፍል ቃለ መጠይቅና ውይይት በማድረግ እንዲሁም ተዛማጅነት ያላቸው የፅሁፍ፣ የተንቀሳቃሽ ምስልና የፎቶ ግራፍ መረጃዎችን በማሰባሰብ ተሞክሮውን የመቀመር ተግባር ተከናውኗል፡፡

## 2.2. የሀላባ ቁሊቶ ከተማ የህዝብ ተሳትፎ ልማት ስራዎች ዓላማ

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ የህዝብ ተሳትፎ ስራዎች ዋነኛ አላማ የከተማውን ነዋሪ ጥቅም፣ ምኞትና ፍላጎት መሰረት በማድረግ ህብረተሰቡ ለከተማው እድገት የሚረዳ ሃሳብ ከማመንጨት ጀምሮ ችግሮችን እስከመለየትና የመፍትሄ አካል በመሆን በአካባቢ የልማት ስራዎች እቅድና ትግበራ ላይ በመሳተፍ እንዲሁም በመገምገምና በመከታተል ወሳኝ ተሳትፎ የሚያደርግበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡

## 2.3. የከተማውን ችግር ለመፍታት የተሰሩ ስራዎች

የሀላባ ቁሊቶ ከተማን ችግር ለመፍታት በቅድሚያ ትኩረት የተሰጠው **የህዝቡ ተሳትፎና ንቅናቄ የሚካሄድበት የልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅድ** በህብረተሰቡ ዘንድ በቂ ግንዛቤ ተይዞበት በመተማመንና የጋራ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ እንዲሆን መከተል ነበር። በከተማዋ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ሃሳባቸው የሚደመጥበት ነፃና ግልፅ መድረክ በመፍጠር ጥቅሞችና ፍላጎታቸው እንዲካተቱ ተደርጎ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተገብቷል፡፡ የከተማዋን የህዝብ ተሳትፎ ተግባራዊ ማድረግ የተለያዩ የሙያ ማህበራትን በመጠቀም ተጠያቂነት፣ ግልፅነትና ዘላቂነት ባለው መልኩ ተግባራዊ የማድረግ መርህን በመከተል ነበር፡፡ በተጨማሪም በልማት ቡድን፣ በቀበሌ አመራሮችና በቀበሌ ሲቪል ሰርቫንት የሚካሄዱ የክትትልና ግምገማ መድረኮች አጀንዳቸው በዋነኛነት በሁሉም ፕሮጀክቶች የህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ማዕከል ያደረገ እንዲሆን የማድረግ አቅጣጫን በመከተል ነበር።

### 2.3.1. የጋራ የሆኑ ችግሮችን መፍታት

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ የህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የአካባቢ ልማት ስራዎች ተሞክሮ **የጋራ የሆኑ ችግሮችን በመፍታት** ረገድ የህብረተሰቡን የመሰረተ ልማት ጥያቄና ችግር በመንግስትና በህዝቡ መሀከል ሊፈጥር የሚችለውን ክፍተት በመሙላት ከፍተኛ ሚና መጫወቱ እና የህዝብ ተሳትፎ ሂደቱ ውጤታማነትም ወጣቶች ተደራጅተው የገቢ ምንጭ ማግኘት መቻላቸው፣ የከተማዋ ነዋሪ ነፋሻማ አየር ማግኘት መቻሉ፣ ወጣቶች አልባሌ ቦታዎች ከመዋል ይልቅ በአረንጓዴና ነፋሻማ ስፍራዎች ማሳለፍ መቻላቸው፣ የአፈር መሸርሸር መቀነሱና ብሎም በጎርፍ ይጠቁ የነበሩ አካባቢዎችን መታደግ መቻሉን በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

### 2.3.2. ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ ስልቶች

#### 2.3.2.1. ህብረተሰቡን ማወያየት

በከተማው የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት አመራሩ በቅድሚያ ከተከተላቸው ስልቶች መካከል የከተማውን ነዋሪ በህብረተሰቡ ተሳትፎ ሊሰሩ በሚችሉ የአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ ማወያየትና ችግሩን ለማቃለል የህብረተሰቡ ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑ ላይ የጋራ መግባባት መፍጠር ነበር፡፡ በዚህም የተለያዩ የህብረተሰብ አደረጃጀቶችን በመጠቀም የከተማዋን ነዋሪ በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ በማወያየትና በባለቤትነት እንዲሳተፉ የጋራ መግባባት በመፍጠር ችግሮችን ለማቃለል ጥረት ተደርጓል፡፡







**ህብረተሰቡን የማወያየት ስራዎች**

### 2.3.2.2. አመራሩና ፈጻሚው ቁልፍ ማነቆዎችን የፈቱበት አግባብ

በህብረተሰቡ የላቀ ተሳትፎና ንቅናቄ የሚሰሩ የአካባቢ ልማት ስራዎችን ለመደገፍ፣ ለመምራትና ለማስተባበር የአመራሩ ሚና ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በሀላባ ቁሊቶ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎና ንቅናቄ የአካባቢ ልማት ስራዎችን ለመደገፍ፣ ለመምራትና ለማስተባበር የከተማዋ አመራር **ከዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ ከአመለካከት፣ ከክህሎትና ከግብአት አንጻር የነበሩበትን ቁልፍ ማነቆዎች በቁርጠኛነትና በይቻላል መንፈስ በመረባረብ፣ ተገቢውን የአቅም ግንባታ ስልጠና በመውሰድና ተግባራዊ በማድረግ** እንዲሁም **ለልማት ስራ የሚያስፈልጉ ገቢዎችን ከክልሉ፣ ከከተማው ነዋሪና ባለሃብቶች በማሰባሰብና** በመሳሰሉት አግባቦች ተስተውሎ የነበረውን ማነቆ ለመፍታት ተችሏል፡፡

የከተማዋ አመራርና ፈጻሚ **የኪራይ ሰብሳቢነትንና የጠባቂነትን ተግባርና አስተሳሰብ ከመጸየፍና ከመታገል አንፃር** የነበረው አቋም/ቁመናን በተመለከተም ችግሩ በአስተሳሰብ ደረጃ የለም ባይባልም በየጊዜው ከላይ እስከታች ባሉ አደረጃጀቶች በሚደረጉ የግማገም ስልቶች አማካኝነት የኪራይ ሰብሳቢነትንና የጠባቂነትን ተግባርና አስተሳሰብ መጸየፍና መታገል የሚችልበት ቁመናን መፍጠር ተችሏል፡፡ ሥራውን በእምነትና **በከፍተኛ የባለቤትነት መንፈስ ከመያዝ አኳያም አንድ አይነት የማይናወጥ አስተሳሰብ በአመራሩና ፈጻሚው መካከል መፍጠር** በመቻሉና ያለውን ሙሉ አቅም ለልማት በማዋሉ ቁርጠኛነቱን ያሳያል፡፡

አመራሩና ፈጻሚው የልማት ዕቅድን ከማሳካት አኳያ የተለወጠና ልማታዊ አስተሳሰብ ያለው የልማት ሠራዊት ለመገንባት ካደረገው ጥረት መካከልም **እንደ መልካም ተሞክሮ የሚገለጸው የልማት ቡድኖች እና ኔትዎርኮችን ማደራጀትና መዘርጋት ነው፡፡** የልማት ቡድኖቹን የስራ እንቅስቃሴን ውጤት በመስጠት የልማት ቡድንን ከልማት ቡድን፣ ሰፈርን ከሰፈር ውድድር ውስጥ በማስገባት የተሻለ የፈጸመውን በማበረታታት የደከመውን ደግሞ የመደገፍ ስራ ይጠቀሳል፡፡ ከሠራተኛው ጋር ባለው ግንኙነትም ግልጽ የሆነ የእርስ በእርስ መተማመንና መግባባት እንዲሁም ቀናና ጠንካራ የቡድን መንፈስ በመፍጠር ይንቀሳቀስ የነበረ ሲሆን የግል ጥቅምን የማስቀደም ዝንባሌ በፈጻሚው ዘንድ እንዳይፈጠር ጠንካራ የግምገማ ስርአት በመዘርጋትና በየቀኑ ተግባራዊ በማድረግ በዚህ ረገድ ክፍተት እንዳይፈጠር ማድረግ ተችሏል፡፡ በመሆኑም አመራሩና ፈጻሚው በጠራ አመለካከት የተቀበሉትና በተደራጀና በተቀናጀ ሁኔታ ያስገኙት ተሞክሮ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የከተማዋ አመራርና ፈጻሚ ከውስጥና ከውጪ ደንበኞች የሚቀርቡለትን ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ተቀብሎ በማስተናገድ ረገድም ቅሬታ አቅራቢው በየደረጃው ላሉ አካላት የሚቀርቡ ሲሆን አቤቱታ

የሚሰማበት ራሱን የቻለ ቀን ያለው መሆኑና ቅሬታዎችን ዲሞክራሲያዊ በሆነ አግባቡ የሚፈቱ መሆናቸው እንዲሁም መድረክ በመፍጠር አቤቱታ የሚሰማበት ስርአት ተዘርግቷል፡፡

### 2.3.2.3. አመራሩ የክህሎት ማነቆዎችን የፈታበት አግባብ

አመራሩና ፈጻሚው ወደ ተግባር ከመግባቱ በፊት **ሀገራዊ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን** መሠረት ያደረገ ግልጽና ትክክለኛ ግቦች ያሉት እንዲሁም ነባራዊ ሁኔታዎችንና የአፈፃፀም አቅጣጫን በሚተነትን ሁኔታ የተዘጋጀ **አሳታፊና ሊተገበር የሚችል ዕቅድ በማቀድ** ረገድ **የህብረተሰቡን ጊዜ፣ ጉልበትና የገንዘብ አቅም በማገናዘብ፤** በከተማዋ ያሉ ባለሃብቶች ብዛትና የሃብት ደረጃ በማገናዘብ ሊፈፀም የሚችል እቅድ በየአመቱ በማውጣት ለተግባራዊነቱ ተንቀሳቅሷል፡፡ የተዘጋጀውን ዕቅድ በልማቱ ላይ የተሻለ ስራ ለሰሩ ባለሃብቶች፣ ተቋማት፣ ግለሰቦች፣ የልማት ቡድኖች **ሰፊ የህዝብ መድረክ በመፍጠር ለማስተዋወቅና የጋራ መግባባት** ላይ ለመድረስ ጥረት ተደርጓል፡፡

### 2.3.2.4. አመራሩና ፈጻሚው የግብዓት ማነቆዎችን የፈቱበት አግባብ

**ከቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም አንፃር**

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ ተሞክሮ በአንድ የልማት ሠራዊት ተዘጋጅቶና የጋራ ግንዛቤ ተፈጥሮበት በዕምነትና በዕውቀት በመመራት ላይ የታዩ ውስንነቶችን በመቅረፍ ረገድ የግምገማዎችን ውጤት በማሳየትና እምነት እንዲኖረው በማድረግና ተሞክሮ በመቅሰምና በአቅም ግንባታ ስልጠና አማካኝነት የሚቀረፍበት ስርአት ተፈጥሮለታል፡፡ ግብዓትን እንደየትኩረት መስኩ ቅድሚያ በመስጠት ለቁልፍ ተግባራት በማዋል፣ ከብክነት በማዳን፣ በቁጠባ ለታለመለት ዓላማ ብቻ በመጠቀም ውጤቱን በማስገኘት ሂደት በተለይ በችግኝ ማፍላት ሂደት የቴክኖሎጂ አቅምን በማጎልበት በአካባቢው የሚገኙ ቁሳቁሶችንና ከተፈጥሮ የሚገኙ የግብርና ግብአቶችን በመጠቀም ችግኙ ሊባክን በማይችልና ለከተማው በሚመጥን መልኩ እንዲፈላና እንዲተከል የማድረግ ስልት እንዲሁም የፍሳሽ ቆሻሻ ማስረጊያ ሴፍቲ ታንክ በነዋሪው በራሱ ፈጠራ የተሰራ ስራ በአብነት ይጠቀሳል፡፡





**የፍሳሽ ቆሻሻ ማስረጊያ ሴፍቲ ታንክ**

### 2.3.2.5. አመራሩና ፈጻሚው ከክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ግብረመልስ ጋር የተያያዙ ማነቆዎችን የፈቱበት አግባብ

የታቀዱ ተግባራት በጠንካራ የክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ግብረ-መልስ አግባብ እየተፈተሹ የሂዱበትና ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልጋቸው የነበሩ ከሆነም የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎችን በተመለከተም በቂ ክትትልና ድጋፍ እንደዚሁም ግብረ መልሶች ሲሰጡ የቆዩና በተግባቡበት አግባብ መፈፀም ያልቻሉትንም በቂ ጊዜ በመስጠት መሻሻል ያልታየባቸውን እርምጃ እየተወሰደ የነበረ መሆኑን መግለፅ ይቻላል፡፡

የውጤቱ ዘላቂነት ይረጋገጥ ዘንድ የክትትልና ድጋፍ አግባቡ **ከተቆጣጣሪነት መንፈስ ተላቆ** የታዩ **የአመለካከት፣ የክህሎትና የግብዓት ችግሮችን የመፍታት አቅም በመፍጠር** ላይ ያተኮረ እና የዘርፉን ልማት መፋጠንን ያለመ ስለመሆኑም ክትትልና ድጋፍ በየቀኑ በስራ ላይ የገጠሙ ችግሮችን በመለየት በየደረጃው በመፍታትና ፈፃሚውን እውቅና በመስጠት የሚደረግ ሲሆን ከዛም አልፎ የቁርጠኝነት ችግር ያለበትን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የሚፈጸም ነው፡፡

ከውጤቱ ጋር ወይም ውጤቱ ከመጣበት ሂደት ጋር በተያያዘ ሲካሄድ የነበረው ግምገማና ሲሰጥ የነበረው ግብረ-መልስ አግባብና ሁኔታን በተመለከተም በአጠቃላይ ይሰጥ የነበረው ግምገማና ግብረመልስ ለለውጡ ከፍተኛ ድርሻ ያለውና የማይቀራረጥ እንደነበር መግለጽ ይቻላል፡፡ በተለያዩ የክትትልና ድጋፍ አግባቦች፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ስለመሰጠቱ **በየቀኑ ከሚደረጉ የውሎ ግምገማዎች እስከ ሳምንታዊ ግምገማና ወርሃዊ ግምገማ** ድረስ ያለው የግምገማ ሂደት በየደረጃው

በቃለ ጉባኤ የተያዘና በተሞክሮ ቅመራው ወቅትም ይህንኑ የሚገልፅ እንቅስቃሴዎችን ለማየት ተችሏል፡፡

## 3. የትግበራ ምዕራፍ

### 3.1. የተገኙ ውጤቶች /ተሞክሮዎች/

#### 3.1.1. ተሞክሮው ያመጣው ተጽዕኖ/ፋይዳ፣ አዎንታዊ ፋይዳ

መልካም ተሞክሮ እንዲቀመር በተፈለገው የስራ መስክ ተጨባጭ የሆነ ፋይዳ ወይም ጥቅም ተገኘ የሚባለው የህብረተሰቡን ኑሮ በማሻሻል በተለይም ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃና ተጎጂ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመድረስ እንዲሁም የመኖሪያ አካባቢያቸው ላይ ዕድገት፣ ለዉጥና መሻሻል በማስከተል ውጤት ያስመዘገበ መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚሁም መሰረት የሀላባ ቁሊቶ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ልማት ስራዎች በህብረተሰብ ተሳትፎ ለመስራት ወደ ስራ ሲጋባ በከተማው ከፍተኛ **የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች የሚስተዋሉባቸው አካባቢዎችን ማዕከል ያደረገ** መሆኑ በተግባር የተረጋገጠ ሲሆን በማሳያነትም በመሀል አራዳ ቀበሌ መንደር 39 የመጣው አወንታዊ ፋይዳ በአብነት ይጠቀሳል፡፡ ይህ አካባቢ በከተማው ከሚገኙ መንደሮች አንዱ ሲሆን ለረዥም ጊዜያት በተፈጥሮ አደጋና በሰው ሰራሽ ችግሮች ማለትም በከፍተኛ የጎርፍ አደጋ የሚጠቃና በርካታ ነዋሪዎች የሚኖሩበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የንፅህና መጓደሎችም የሚስተዋሉበት ነበር፡፡ በመሆኑም የከተማ አስተዳደሩ በዚህ አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎችንና ነጋዴዎችን በማስተባበር በጉልበት፣ በገንዘብና በቁሳቁስ ተሳትፎ በማድረግ ችግኞችን በመተከላቸው፣ የጎርፍ መውረጃ ዲሾች/ቱቦዎችን በመገንባታቸው እንዲሁም የአካባቢውን ፅዳትና ውበት ከመጠበቅ አኳያም እያንዳንዱ የአካባቢው ነዋሪ አካባቢውን የሚያጸዳበት ስርአት በመፈጠሩ ተሞክሮው በዚህ አካባቢ አወንታዊ ፋይዳ ማምጣት ችሏል፡፡



 

**የድሬኔጅና ድልድይ ግንባታዎች በመንደር 39**

ከዚህ በተጨማሪም ተሞክሮው ካመጣቸው አወንታዊ ፋይዳዎች መካከል ህብረተሰቡ ‹‹**ሁሉንም ነገር መንግስት ይስራልን**›› ከሚል አመለካከት ተላቆ በፍላጎቱ የድርሻውን በመሳተፍ የመንግስትን ድርሻ የሚጠባበቅበት ደረጃ ላይ መድረሱ፣ **የህብረተሰቡ የልማት ፍላጎትና የተሳትፎ መጠኑ በመጨመሩ** እንደዚሁም **ጥያቄው በሙሉ የስታንዳርድ ጥያቄ** ላይ በመድረሱ በከተማ ደረጃ የተለጠጡ ዕቅዶች እንዲዘጋጁ በጎ ተፅዕኖ መፍጠር ችሏል፡፡

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ ተሞክሮ **በተቋማት ላይ ያመጣውን ውጤት** በተመለከተ የህዝቡ የመሠረተ ልማት ጥያቄና ተሳትፎ የተለያዩ ሴክተሮችን የሚዳስስ ከመሆኑ አንጻር ከአንድ ተቋም በላይ ያሉ ሴክተሮችን ውጤታማ ያደረገ ነበር፡፡ ለአብነትም **በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ የስራ እድል ከመፍጠር አኳያ** የከተማዋ ወጣቶች በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ በመደራጀት ቀደም ሲል የቆሻሻ መጣያ የነበሩ ቦታዎችን ከከተማ አስተዳደሩ ተረክቦ በማፅዳትና ውብ **የመዝናኛ ስፍራ/ ፓርክ** በማድረግና የተለያዩ አገልግሎቶችን ለተጠቃሚው በማቅረብ ገቢ እያገኙ ይገኛሉ። **በከተማ ግብርና ዘርፍም** የተለያዩ የከተማዋ የህብረተሰብ ክፍሎች መሰል ቦታዎችን በመረከብ የአትክልትና ፍራፍሬ ችግኞችን በማፍላትና በመሸጥ የገቢ ምንጫቸውን እያሳደጉ መገኘታቸው እንዲሁም ችግኞች በስፋት መተከላቸው የአፈር መቦርቦርን መቀነሱና በጎርፍ ይጠቁ የነበሩ አከባቢዎችን መታደግ መቻሉ የዘርፉን ውጤታማነት አመልካች ሆኗል፡፡ በአጠቃላይ የከተማዋ የህብረተሰብ ተሳትፎ እንቅስቃሴ **ለአብነት የጠቀስናቸውን ዘርፎች ውጤታማ ማድረግ መቻሉን** መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 3.1.2. የጋራ ችግሮችን በመፍታት ውጤታማ ከመሆን አንጻር

የህብረተሰቡ የልማት ተሳትፎ ሲጀመር የነዋሪውን ጥቅሞች፣ ፍላጎቶችና ምኞቶች የሚያጠናክርና ቅድሚያ የሚሰጥ ፕሮጀክት በማጥናትና በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ለመፈጸም ዝግጅት በማድረግ ነበር፡፡ በዚሁም መሰረት **በልማት ቡድን ኔት ዎርክ** የተደራጀውን **የከተማዋን ነዋሪና ተወላጆች፣ የመንግስት፣ የግል ድርጅት ሰራተኞችና አመራሮች** እንዲሁም **ልማታዊ ባለሃብቶችን** በማካተት በጽዳትና ውበት፣ በጎርፍ መውረጃ፣ በኮብልስቶን ንጣፍና በመሳሰሉ ፕሮጀክቶች አስፈላጊነትና አተገባበር ላይ ውይይት በማድረግ **በአመለካከት የነበረውን ማነቆ በመፍታት** ህብረተሰቡ ፕሮጀክቶችን በባለቤትነት ስሜት እንዲፈፅማቸው የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል። በመቀጠልም ከወረዳ አስተዳደር እስከታችኛው የኔትዎርክ አደረጃጀት በግላቸውና በከተማ ደረጃ በጋራ ተሳትፎ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን በጥናቱ መሰረት እቅድ ወጥቶላቸው እንዲተገበሩ በማስቻል ዋና ዋና የጋራ ችግሮችን ማለትም የጎርፍ፣ የጽዳትና የአረንጓዴ ልማት፣ የመንገድ እና የመሳሰሉ ችግሮችን የፈታ ተሞክሮ ነው፡፡

### 3.1.3. አስተማማኝ ውጤት አምጪነቱ በውጪ ባለሙያዎች መረጋገጡ

ተሞክሮው ከደቡብ ክልል ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ በመልካም ተሞክሮነት ውጤታማ መሆኑ በባለሙያዎች ተረጋግጦ በክልል ደረጃ ለሽልማት የበቃ መሆኑ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ በከተማዋ በህብረተሰብ ተሳትፎና ንቅናቄ የተሰሩ የአካባቢ የልማት ስራዎችን ለተሞክሮ በሚሆን መልኩ ለመለየት ባደረገው የመስክ ምልከታም ውጤታማነቱ የተመሠከረለት መሆኑን መግለጽ ይቻላል፡፡

### 3.1.4. ተሞክሮው የተሻለ አንጻራዊ የአፈጻጸም ደረጃ ማስመዝገቡ

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎ የልማት እንቅስቃሴ በክልል ደረጃ የተሻለ የአፈጻጸም ደረጃን በማስመዝገቡ ተሸላሚ ሲሆን በተጨማሪም የከተማው አስተዳደር የስራ ክፍሎች፣ በልማት ቡድን ውስጥ ግለሰቦችና ልማታዊ ባለሀብቶች በክልል ደረጃ ሽልማት ማግኘታቸው ተሞክሮው የተሻለ አፈጻጸም በክልል ደረጃ ለማስመዝገቡ ማሳያ ይሆናል፡፡

### ሀ/ ከአመራር አንጻር

የልዩ ወረዳው እና ከተማው ከፍተኛ አመራር ጀምሮ በየደረጃው ያለው አመራር ተግባሩን የራሱ አድርጎ መምራት መጀመሩና በከተሞች የልማት ተሳትፎ አደረጃጀት አማካኝነት ከሚከናወኑ አጀንዳዎች አንዱ በህብረተሰብ ተሳትፎ ጽዳትና የአረንጓዴ ልማት ጉዳይ ቢሆንም የዚህን አፈጻጸም ለውጥ ሊያመጣና የአፈጻጸም ማነቆ በለየ ሁኔታ በአመራር በጥልቀት የማይገመገምበት

ሁኔታ ነበር፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ግን እየተለወጠ ከልዩ ወረዳው ዋና አስተዳዳሪ እና ከከተማው ከንቲባ ጀምሮ በየጊዜው ተግባሩን ለይተው የሚገመግሙበትና በየእርከኑ ያሉ አመራሮችም በዚሁ አግባብ የሚፈጽሙበት በመሆኑ ትልቅ የአመለካከት ለውጥ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በተጨባጭ እያንዳንዱ ከዋና አስተዳደር እና ከከተማው ከንቲባ ጀምሮ ሁሉም አመራር ተግባሩን ወደ መምራት ደረጃ መጥቷል፡፡

ባለድርሻ አካላትና ተቋማት ደግሞ የስራው ባለቤትና ፈጻሚ ወደ መሆን ደረጃ መሸጋገራቸውና ከራሱ ተቋም ግቢና አካባቢ ጀምሮ ለጽዳትና ለአረንጓዴ ልማቱ የሚያስፈልግ በጀት በተለየ ሁኔታ መመደቡ የስኬቱ መገለጫ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ ለአብነት በልዩ ወረዳ ደረጃ ያሉ የመንግስት ተቋማት ወትሮ ባልተለመደ ሁኔታ ከንቅናቄው መነሻ ለግቢያቸውና አካባቢያቸው ጽዳትና አረንጓዴ ልማት በጀት መድበው ወደ ስራ እየገቡ ይገኛሉ፡፡ ይህ እምርታዊ የሆነ የአመለካከት ለውጥ ስለመምጣቱ ማሳያ ነው፡፡

በልዩ ወረዳው እንዲሁም በከተማ አስተዳደሩ ተግባሩ የፖለቲካ አመራር ትኩረት ማግኘቱና መንግስት ተግባሩን ለመምራት ቁርጠኛ መሆኑን ህዝቡና ባለድርሻ አካላት ደግሞ አጀንዳውን ለመፈጸም አምኖ መቀበሉን የሚያሳይ ነው፡፡ ሁሉም መንግስታዊ ተቋማት በተለየ ሁኔታ በጀት የያዙበትና ከማዘጋጃ ቤት ገቢ ከሚገኝ በጀት በተጨማሪ መደበኛ በጀት እንዲበጀት ያደረጉበት ደግሞ ሲታይ ጽዳትና አረንጓዴ ልማት አስተሳሰብ ጎልቶ እየወጣ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ቀደም ሲል ለመርሃ ግብር ማሟያ ሲባል ሲከናወን የነበረው ሙሉ በሙሉ የተቀየረበትና የሚታይና የሚጨበጥ ለውጥ ለማምጣት አጭር የጊዜ ገደብ አስቀምጠው መስራት መጀመራቸው ትምህርት የሚወሰድበት አንኳር ጉዳይ ነው፡፡

## ለ/ ከከተማ ነዋሪ አንጻር

በከተማ አቀፍ በተካሄደው የንቅናቄ መድረክ ላይ የከተሞች ጽዳት ውበትና አረንጓዴ ልማትን ለማሳካት የአመለካከት ግንባታ ላይ ትኩረት ተደርጎ መሰራት እንዳለበት እና በከተማ ደረጃ የልማት ተሳትፎ አደረጃጀት አማካኝነት የ15 ቀን የመንደር የውይይት መድረክን በመጠቀም የጽዳትና አረንጓዴ ልማት አስፈላጊነትን ከማስገንዘብ በተጨማሪ የአመለካከት ትግል እንዲደረግበት አቅጣጫ በማስቀመጥ በዚህ ሁኔታ የአመለካከት ለውጥ የመጣበትና ነዋሪው ወደ ተግባር በመግባት 17ቱን አጀንዳዎች ከመፈጸም አንጻር ከፍተኛ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ ለዚህም ማሳያ በመህል አራዳ መንደር 39 ህብረተሰቡ ገንዘብ በማዋጣት የኮብል ስቶን መንገድ መስራቱ፣ የጎርፍ መውረጃ ቦይ (ዲች) መገንባቱ፣ የአካባቢውን ሰላምና ጸጥታ ለማስጠበቅ ነዋሪው በራሱ የጥበቃ ሀይል መቅጠሩና እንዲሁም ማታ ማታ ከጥበቃዎች ጋር በመሆን ጥበቃ ማድረጉ፣ የመንደሩን ጽዳት ከማስጠበቅ አንጻር ጥቃቅን ቆሻሻዎችን ለማጠራቀም በየመንገዱ ዳር ዘመናዊ

የቆሻሻ ማስቀመጫ መዘጋጀታቸው፣ የአካባባውን ንጽህና በጋራ መጠበቅ፣ የፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ውጪ ከመውጣት ይልቅ በጊቢ ውስጥ ጉድጓድ በመቆፈር ማስረግ መቻሉ፣ ደረጃውን የጠበቀ ዲዛይን የወጣላቸው አረንጓዴ ልማቶች መከናወኑ፣ የፍራፍሬና የአትክልት ችግኞችን ማልማታቸው በበጎ ጎኑ የሚታዩ ናቸው፡፡ በተለያየ ጊዜ በመንግስትም በግለሰብም ለሚተከሉ ችግኞችና አጠቃላይ በአረንጓዴ ልማት እና በከተማው ጽዳት ላይ ከፍተኛ ችግር ተደርጎ ሲወሰድ የነበረው በዘፈቀደ የሚለቀቁ ከብቶች የነበሩ ሲሆን ከብቶችን በዘፈቀደ መልቀቅ ተገቢ አለመሆኑን ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር ከመግባባት ላይ መድረስ በመቻሉ በዚህ ደረጃ ለአረንጓዴ ልማት እና ለከተማው ጽዳትና ውበት ያለውን ኃላፊነትና ድርሻ በመወጣቱ የመጣ ውጤት ነው፡፡

## ሐ/ ከብዙሃን አደረጃጀቶች አንጻር

በከተማው የነዋሪው፣ የወጣትና ሴት አደረጃጀቶች በጽዳትና አረንጓዴ ልማት ዘርፍ ቀላል የማይባል ሚና አበርክተዋል፡፡ በተለይም ከክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ጋር በማስተሳሰርና የንቅናቄ መድረኮችን በመጠቀም በየደረጃው የነዋሪው፣ የወጣቱና ሴቶች አመለካከት ለውጥ እንዲመጣ የተለያዩ ጥቅሶችና መልዕክት አዘል ጽሁፎችን በመጠቀም አዎንታዊ ተጽዕኖ መፍጠር ተችሏል፡፡ ለምሳሌ በከተማው ወጣቶች አረንጓዴ ቦታ በስማቸው ለማልማት ለማዘጋጃ ቤት ጥያቄ አቅርበው የተሰጣቸውን ቦታ በራሳቸው ፈቃድ ጉልበታቸውና እውቀታቸውን በማፍሰስ ማልማት ችለዋል፡፡ በተጨማሪም በመንደር ደረጃ ህብረተሰቡ በጉልበትና በገንዘብ አስተዋጽኦ በማድረግ በመንገድ ግንባታ፣ ለአቅመ ደካሞች መኖሪያ ቤቶችን በመገንባት እና ድጋፍ ማድረግ እና የከተማውን ጽዳትና ውበት ለማስጠበቅ በየሳምንቱ ቅዳሜ በመውጣት የተተከሉ ችግኞችን መንከባከብና ጽዳት በማካሄድ እንዲሁም በችግሮቻቸው ዙሪያ ውይይት ማድረግ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ለዚህም ማሳያ በከተማዋ የለማ የወጣቶች መዝናኛ ማዕከላት /ቦታዎች፣ በተጨማሪም ማዘጋጃቤቶች እና የወጣቶች ፓርኮች ለምተዋል፡፡ በመንደር ደረጃም ኮብልስቶን በመገንባት፣ የጎርፍ መውረጃ ቦይ (ዲች) በመገንባት፣ አረጋዊያንን በመርዳትና አካባቢያቸውን ውብና ጽዱ በማድረግ የአረንጓዴ ተክሎችን በዲዛይን በመትከል፣ ለውይይት እና የተለያዩ መረጃዎችን ለማስቀመጥ በመንደር ደረጃ ጽ/ቤት በመክፈት ለክልሉም እንደ ምርጥ ተሞክሮ የሚታይ ተግባር ተከናውኗል፡፡

## መ/ ከግል ባለሀብቶች አንጻር

በከተማው ያሉ ባለሀብቶች የራሳቸውን ትርፍና ስራ ብቻ ከማየት ወጥተው ከተማውን ጽዱና ለኑሮ ምቹ ለማድረግ በሚደረገው ርብርብ ውስጥ የራሳቸውን ሚና ለማበርከት በአመላካከት ዝግጁ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡ በዚህ መነሻ ከራሳቸው ግቢና አካባቢ ጀምሮ ጽዱና ውብ ለማድረግ አረንጓዴ ተክሎችን በመትከል ማልማት የጀመሩበት አግባብ ሲታይ የአመለካከት ለውጥ ነጸብራቅ መሆኑን መረዳት

ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የደረቅ ቆሻሻ መጠንን ለመቀነስ ከምንጩ የመለየት ሥራ በመስራት ከዚያም አልፈው በከተማ ውስጥ ቦታዎችን ከማዘጋጃ ቤት ጠይቀው በመውሰድ በዘርፉ የተደራጁ ማህበራቶችን ከሌሎች ከተሞች ጭምር በማስመጣት ስታንዳርዱን የጠበቀ ዲዛይን እንዲዘጋጅ በማድረግ አልምተዋል፡፡ ለዚህም ለአብነት ሴራ ሎጅ ሆቴል፣ ሰላም ሆቴል፣ ናፍቆት ፔንስዮን፣ ግሪን ቪዉ ሆቴል እና ሀላባ ፖሊ መከከለኛ ክሊኒክ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

### 3.1.5. የተሞክሮው አሳታፊነት

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎ እንቅስቃሴ ከገቢ፣ ጾታ፣ ዕድሜና አካላዊ/ አይምሯዊ ሁኔታ/ ችሎታን እንዲሁም የሃይማኖት ተቋማትንም ጭምር ያሳተፈና ዋጋ የሰጠ ነው፡፡

#### ሀ/ ከገቢ አንጻር

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎ የልማት እንቅስቃሴ ዝቅተኛ ገቢ ካለው የህብረተሰብ ክፍል ጀምሮ እስከ ልማታዊ ባለሃብቱ ድረስ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ተሳታፊ ያደረገ ነው፡፡ ልማታዊ ባለሀብቱ ለልማት ስራዎቹ የገንዘብ መዋጮ በማድረግና የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለምሳሌ የተለያዩ ተሽከርካሪዎችን፣ በአረንጓዴ ልማት ስራዎችና በመሳሰሉት በመሳተፍ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ዝቅተኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍልም በአቅሙ ያለውን ገንዘብ በማዋጣት እና ከፍተኛ የጉልበት አስተዋጽኦ በተለይ በጎርፍ መውረጃ ዲቾች ግንባታ በቁፋሮ እና በመሳሰሉት ላይ በመሳተፍ የበኩሉን ሚና ተጫውቷል፡፡





#### ለ/ ከጾታ አንጻር

በከተማዋ ያለው የልማት እንቅስቃሴ ሁሉንም ጾታዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ ያደረገ ነው፡፡ በተለይም ሴቶች በልማት ቡድን እስከ 1ለ5 ድረስ በመደራጀት በፅዳትና ውበት ስራዎች

ችግኞችን በመረከብና ተንከባክቦ በማሳደግ፣ በየሳምንቱ ቅዳሜ በከተማው የሚካሄደውን የጽዳት ፕሮግራም ግንባር ቀደም ተሳታፊ ሆኖ በመምራትና በማስተባበር፣ ሰላምና ጸጥታን ከማረጋገጥ አኳያም በአደረጃጀቶቻቸው አማካኝነት በአካባቢያቸው ያለውን የሰላምና ጸጥታ ስራ በማስተባበር የከተማዋ ሴቶች ተሳትፎ በአርአያነት የሚጠቀስ ሆኖ ይገኛል፡፡

## ሐ/ ከዕድሜ አንጻር

የከተማዋ የህብረተሰብ ተሳትፎ የልማት እንቅስቃሴ ከልጅ እስከ አዋቂ ድረስ በነቂስ የተሳተፉበት በመሆኑ ሁሉንም የእድሜ ክፍል ያሳተፈ መሆኑን ያሳያል፡፡

## መ/ አካላዊ/ አይምሯዊ ሁኔታ

የከተማዋ የህብረተሰብ ተሳትፎ የልማት እንቅስቃሴ በጉልበት አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችለውን (ለምሳሌ የተለያዩ የወጣቶች፣ የሴት አደረጃጀቶችን) በማሳተፍ፤ በጉልበቱ አስተዋጽኦ ማድረግ የማይችለውን (የተለያዩ እንደ መምህራን ማህበር ያሉ የሙያ ማህበራትን፣ ሲቪል ሰርቫንቱን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን ወዘተ…) ደግሞ በሃሳብና በተለያዩ የተሳትፎ መንገዶች ያሳተፈ ነው፡፡

## ሠ/ ከሀይማኖት ተቋማት አንጻር

የሀይማት ተቋማት በተለይ የአመለካከት ቀረጻ ላይ ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንጻር በሀላባ ቁሊቶ ከተማ ያሉ የሀይማኖት ተቋማት ልማቱ የእነርሱም ጭምር እንደሆነ በአመለካከት መቀበል መጀመራቸውን በአርአያነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ለአብነት በከተማው ያሉት የሀይማኖት ተቋማት ከካዝናቸው ለግቢያቸውና አካባቢያቸው ጽዳትና ውበት እንዲሁም አረንጓዴ ልማት በጀት በመበጀት ዲዛይን እንዲዘጋጅለት ከማህበራት ጋራ በጋራ መስራታቸው ጠንካራ የሀይማኖት ተሳትፎ መኖሩን ያሳያል፡፡ በዚህ ረገድ የከተማው መልካም ተሞክሮ የሚያሳየው ለውጥ በተወሰኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች ብቻ የሚንጸባረቅ ሳይሆን ሁሉም አካላት እምርታዊ የሆነ የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ ያመጡበት መሆኑን ነው፡፡

## ረ/ ከጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት አንጻር

ቀደም ሲል በከተማዋ የጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት በጽዳትና ውበት እንዲሁም በአረንጓዴ ልማት ተግባራት በስፋት ሲሳተፉ አይስተዋልም ነበር፡፡ ምክንያቱም ስራው የገቢ ምንጭ መሆን እንደሚችል ከመረዳት አኳያ የአመለካከት ችግሮች የነበሩ በመሆኑ ነው፡፡ በከተማው ከሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ የተነሳ እና ከአመራሩ ቁርጠኝነት በሀላባ ቁሊቶ ከተማ ይህ አስተሳሰብን በመስበር የዩኒቨርስቲ ምሩቃንና ሰራተኞችን በማህበር እየተደራጁና አካባቢያቸውን ወደ ማልማትና ገቢ ወደ ማግኘት ማሸጋገር ተችሏል፡፡ ቀደም ሲል 5 ብቻ የነበሩት የአረንጓዴ ልማት ማህበራት

በአጭር ጊዜ ውስጥ 29 ማህበራት ተደራጅተዋል፡፡ በከተማው በችግኝ ማፍላትና ስርጭት መስክ የተሰማራ *"ሹክራላና ቤተሰቡ"* የሚባል ማህበር ውጤታማ መሆኑ በአብነት የሚጠቀስ ሲሆን ማህበሩ ከሚያፈላውና ከሚያሰራጨው ችግኝ በቀን ከፍተኛ ገቢ ያገኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሀላባ ቁሊቶ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ በአረንጓዴ ልማት ስልጠና መስጠት የተጀመረ ቢሆንም በዚህ ዘርፍ የሚሰለጥን ሰልጣኝ የማይቀርብበት ሁኔታ የነበረ ቢሆንም አመለካከት ላይ በተሰራው ስራ በአሁኑ ወቅት ሰልጣኞችን ተቀብሎ በማሰልጠን ላይ ይገኛል፡፡







**የጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት**

### ሰ/ ከእድሮች አንጻር

የመንደር እድሮችና ሌሎች ተመሳሳይ ህብረቶች ለዚህ ስራ ዓይነተኛ መሳሪያ መሆናቸው እሙን መሆኑ ግልጽ ሲሆን በከተማው የተስተዋለውም ይህንን ተሞክሮ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ለምሳሌ በከተማው ያለን አንድ እድር ብንወስድ የአረንጓዴ ቦታ አንዱ ኮምፖነንት የሆነው የዘላቂ ማረፊያ ቦታ አረንጓዴ ለማድረግ በጀት መድቦ በመስራቱ ውጤታማ ሆኗል፡፡

### ሸ/ ከመንግስት ተቋማት አንጻር

እያንዳንዱ የመንግስት ተቋም በ1ለ5 እና በለውጥ ቡድን ውይይት አጀንዳ እንዲያደርግና ለግቢውና አካባቢው ጽዳትና ውበት እንዲሁም አረንጓዴ ልማት በጀት በመያዝ ከአትክልተኛ ጋር እንዲያስተሳስር አቅጣጫ በማስቀመጥ የመንግስት ተቋማት የአካባቢ ጽዳትና ውበት እንዲሁም አረንጓዴ ልማት የውይይት አጀንዳ በማድረግ ለ2010 በጀት ዓመት ለግቢያቸውና አካባቢያቸው ጽዳት እና አረንጓዴ ልማት ስራ በድምሩ 2.5 "ሚሊዮን የሚጠጋ ብር" በመመደብ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ ለምሳሌ ሀላባ ጤና ጣቢያ፣ ቁሊቶ ሆስፒታል፣ ቁሊቶ ሀይስኩል፣ ወረዳና ከተማ አስተደደር የመሳሰሉትን በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ የሀላባ ቁሊቶ ከተማ አስተዳደር ለአካባቢ አረንጓዴ ልማት ከመደበኛ በጀት 1,248,500 (ከማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ 1 ሚልዮን ሁለት መቶ አርባ ስምንት ሺ አምስት መቶ ብር) በተለየ ሁኔታ መመደብ መቻሉ ከመንግስት ተቋማት አንጻር የተሰጠውን ትኩረት ያሳያል፡፡






**የተቋማት ገጽታ በከፊል**

### 3.1.6. ለፈጠራው ያለው ቅርበትና አካባቢያዊ ተዛማጅነት

በሀላባ ቁሊቶ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎ እንቅስቃሴ ወቅት የተስተዋሉ የፈጠራ ስራዎችና ከአካባቢው ጋር ያላቸው ቁርኝነት እንደሚከተለው ይገለጻል፡፡

### የፍሳሽ ቆሻሻ ማስረጊያ ሴፍቲ ታንክ

በሀላባ ቁሊቶ ከተማ በእያንዳንዱ ግቢ የፍሳሽ ቆሻሻን ለማስወገድ የሚረዳ የፍሳሽ ቆሻሻ ሴፍቲ ታንክ ተዘጋጅቶ አገልግሎት እየሰጠ ሲሆን በዚህም እያንዳንዱ መንደር አካባቢውን በፍሳሽ መልክ ከሚወገድ የቆሻሻ መጥፎ ሽታና ብክለት መታደግ ተችሏል፡፡





የፍሳሽ ቆሻሻ ማስረጊያ

## የገቢ ማስገኛ ዝግጅቶች

የባዛር ዝግጅት ዋነኛው የገቢ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን እያንዳንዱ በየቀበሌው ባሉ አደረጃጀቶች ተደራጅቶ የሚገኘው ነዋሪ ከከተማው አስተዳደር ጋር በመነጋገር የባዛር ዝግጅት በማድረግ ለልማት ስራ የሚውል ከፍተኛ ገቢ የሚሰበስብበት ነው፡፡ በባዛሩ ላይም የአካባቢው/የቀበሌው ነዋሪዎች፣ የከተማው አስተዳደር እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችና ተወላጆች ተሳታፊ የሚሆኑ ሲሆን በዝግጅቱ ላይ የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን በጨረታ በመግዛት ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ የገቢ አሰባሰቡም በህጋዊ ደረሰኝ መሰረት በልማት ቡድኑ ኮሚቴዎች አማካኝነት የሚከናወን ነው፡፡

## የሆስፒታል ግንባታ

በሀላባ ቁሊቶ ከተማ እና በልዩ ዞኑ የወባ በሽታ ከፍተኛ ጉዳት በህዝቡ ላይ ማድረሱን ተከትሎ ህብረተሰቡ በራሱ ተነሳሽነት ገንዘብ በማዋጣት ዘመናዊ ሆስፒታል መገንባት የቻለ ሲሆን ሆስፒታሉ በአሁኑ ሰአት ከልዩ ዞኑ ባሻገር ላሉ ወረዳዎችም ጭምር አገልግሎት እየሠጠ ይገኛል፡፡

## የስብሰባ አዳራሽ ግንባታ

በከተማው ደረጃውን የጠበቀ የስብሰባ አዳራሽ በመገንባት ረገድም ህብረተሰቡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ደረጃውን የጠበቀና ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውል የሚችል አዳራሽ መገንባት ተችሏል፡፡



**በህብረተሰቡ ተሳትፎ የተገነባው አዳራሽ**

## የአስፋልትና የመንገድ አካፋይ ስራ

**በከተማው በህብረተሰቡ ተሳትፎ ደረጃውን የጠበቀ የአስፋልት መንገድና የመንገድ አካፋይ የተሰራ ሲሆን በተለይ በህብረተሰብ ተሳትፎ የተሰራ የአስፋልት መንገድ ስራ በሌሎች አካባቢዎች እምብዛም የሚስተዋል ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ ልዩ ያደርገዋል፡፡ የመንገድ አካፋዩም በህብረተሰቡ ተሳትፎ የተሰሩ ሲሆን የግንባታ ስራውን ከዩኒቨርሲቲ ለወጡና ለተደራጁ ተማሪዎች በመስጠት ለወጣቶች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡**





**በህብረተሰብ ተሳትፎ የተሰራ አስፋልት መንገድና የመንገድ አካፋይ**

## የውሃ መውረጃ ግንባታ

**ሌላው በሀላባ ከተማ የተስተዋለው የፈጠራ ግኝት በኮብል ስቶን መንገድ ንጣፍ ላይ የተሰሩ የውሃ መውረጃ ቱቦዎች ላይ ያለው ፈጠራ ነው፡፡ ይኸውም ዲሽ መገንባት ከወጪ አንጻር ሲታይ ከፍተኛ በመሆኑ የውሃውን ተፋሰስ በጠበቀ መልኩ በኮብል ስቶኑ በመጠቀም የውሃ መውረጃ ቱቦ ለመስራት ተችሏል፡፡**





**በኮብል ስቶን የተሰራ የውሃ መውረጃ**

## የዲሽና የእግረኛ መንገድ /ቴራዞ/ ስራዎች

በሀላባ ቁሊቶ ከተማ በዋና ዋና የአስፋልትና የኮብል ስቶን መንገዶች እንዲሁም የውስጥ ለውስጥ መንገዶች በርከት ያሉና ደረጃቸውን የጠበቁ የውሃ መተላለፍያ ዲቾችና የእግረኛ መንገድ /ቴራዞ/ ንጣፍ መንገዶች በህብረተሰቡ ተሳትፎ ተገንብተዋል፡፡







**የቴራዞና የዲች ግንባታ**

## የዛፎች የህይወት ታሪክ መግለጫ

በከተማው በተለይ በዋና ዋና መንገዶች አካፋይ የሚተከሉ ችግኞች እያንዳንዳቸው የህይወት ታሪክ መግለጫ ያላቸው ሲሆን በመግለጫውም የዛፉ/ችግኙ ኮድ፣ የዝርያ ስም፣ ያስተከለው ተቋም ስም፣ የተተከለበት ቀን፣ የተገዛበት ዋጋ፣ የተንከባካቢ ስም እንዲሁም የአደጋ ጊዜ ተጠሪ ተገልጾ በዛፉ/ችግኙ ላይ የህይወት ታሪኩ ይንጠለጠላል፡፡









**የዛፎች የህይወት ታሪክ መግለጫ**

## የህብረተሰቡ የልማት ተነሳሽነት

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ ነዋሪዎች ለልማት ስራዎች ያላቸው ተነሳሽነትና ተሳትፎ በእጅጉ ሊበረታታ የሚገባውና ትምህርት ሊወሰድበት የሚገባ ነው፡፡ ለአብነትም ህብረተሰቡ ለመንገድ ስራዎች ቤትና አጥር እንዲያፈርስ ሲጠየቅ በፈቃደኝነትና ምንም አይነት የካሳ ክፍያ ከመንግስት ሳይጠይቅ መፈጸም መቻሉ በአርአያነት የሚጠቀስ ሲሆን በአካባቢ ልማት ሰራዎች ላይም ያለምንም ቅስቀሳ በራሱ ተነሳሽነት መሳተፉና የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራዎችን እንደ ባህል መያዙ አስደናቂ ያደርገዋል፡፡

## የነዋሪዎች የልማት ተሳትፎ አደረጃጀት

እያንዳንዱ ቤተሰብ በ1ለ5፣ በጣቢያ /ብሎክ/፣ በሠፈር /መንደር/ ደረጃ ተደራጅቶ ግቢውንና ደጃፉን ብሎም አካባቢውን የሚያጸዳበትና አረንጓዴ የሚያደርግበት ስርአት ተዘርግቷል፡፡ በከተማው 1,172 1ለ5፣ 369 ብሎክ፣ 46 መንደርና፣ 5 ቀበሌዎች የሚገኙ ሲሆን በተቀመጠው የአሰራር ስርዓት መሰረት በአካባቢ ጽዳትና አረንጓዴ ልማት ችግሮች ላይ ውይይት ያደርጋሉ፡፡ *ነዋሪውና ባለሀብቱ* የውበት፣ የጥላና የፍራፍሬ ችግኞችን ግዥ በመፈጸምና ዲዛይን በማውጣት ስታንዳርዱን በጠበቀ አግባብ ማልማት መቻሉና በዚህ መሰረትም በአካባቢ ጽዳትና አረንጓዴ ልማት ረገድ 34

መንደሮች የተመረቁ ሲሆን የከተማ አስተዳደሩም የነዋሪዎች አደረጃጀትን በመደገፍና በተቀመጠው የአሰራር ስርዓት መሰረት ወደ ስራ መግባታቸውን የመከታተል ስራ በመሰራቱ ውጤታማ ሆነዋል፡፡







## የአባወራ አረንጓዴ ልማት በከፊል

በከተማ አስተዳደሩ በጽዳትና ውበት ረገድ በሳምንት አንድ ቀን ዘወትር ቅዳሜ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊ የሆኑበት የጽዳት ፕሮግራም ያለ ሲሆን እያንዳንዱ ነዋሪ ከመኖሪያ ቤቱ በ20 ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ቆሻሻን የማፅዳት ኃላፊነትን በመውሰድ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡

የአረንጓዴ ልማት ስራዎች ለከተማዋ ንጹህና ነፋሻማ አየር የተፈጠረበት እንዲሁም በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ የተደራጁ አካላት የገቢ ምንጭ የፈጠሩበት በመሆኑ ውጤታማ የአረንጓዴ ልማት ተግባር ተከናውኗል፡፡



**ህብረተሰቡ በከተማው ጽዳት ላይ ሲሳተፍ**









### የቆሻሻ አወጋገድና የማህበራት ተሳትፎ

### የግሉ ዘርፉ በአረንጓዴ ልማት ተሳትፎ

የከተማ አስተዳደሩ ለግሉ ባለሀብት የንቅናቄ መድረክ በማመቻቸት ባለሀብቶችና የግል ንግድ ድርጅቶች ግቢያቸውንና አካባቢያቸውን ጽዱ፣ ውብና አረንጓዴ እንዲያደርጉና በባለቤትነት መንፈስ እንዲያከናውኑ ከጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ በዚሁም መሰረት በሀላባ ቁሊቶ ከተማ የሚገኙ የግል ባለሀብቶች እንዲሁም ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በከተማው ጽዳትና ውበት እንዲሁም አረንጓዴ ልማት ላይ በጀት በመመደብ ጭምር ሰፊ ተሳትፎ በማድረግ ለዘላቂ የአካባቢ

ጥበቃና እንክብካቤ ጉልህ ድርሻ እየተወጡ የሚገኙ ሲሆን በተለይ አምስት የግል ተቋማት ለጽዳትና አረንጓዴ ልማቱ በጀት የያዙበትና ወደ ልማቱ የገቡበት ሁኔታ ተስተውሏል፡፡

| ተ.ቁ | አገልግሎት ሰጭ ተቋማት | ለአረንጓዴ ልማቱ የተያዘ በጀት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ሴራ ሎጅ | 147,000ብር | |
| 2 | ግሪን ቪው | 156,000 ብር | |
| 3 | ሰላም ሆቴል | 90,000ብር | |
| 4 | ናፍቆት ፔንሲዮን | 45,000ብር | |
| | **ድምር** | **ብር 438,000** | |











**የከተማው አረንጓዴ ልማት ገጽታ በከፊል**

በአጠቃላይ በከተማው በህብረተሰብ ተሳትፎ የተሰሩና እየተሰሩ ያሉ ልማት ስራዎች ከላይ በጠቀስናቸው የፈጠራ ስራዎች የታጀቡና ከአካባቢው ማህበረሰብ እና ከግሉ ዘርፍ ጋር በመተባበር ትስስር ተፈጥሮ የተሰሩና እየተሰሩ የሚገኙ ናቸው፡፡

## የመፈጸም አቅም እና ሀብት

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ መልካም ተሞክሮ እንዲቀመር ሲለይ ተሞክሮው አቅምን ያገናዘበ (affordable) እና ተጨማሪ ወጪ የማያስወጣ ሆኖ ቀጣይነት ያለው (sustainable) እና መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጣ መሆኑ በመረጋገጡ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በከተማዋ የተስተዋለው ነገር ቢኖር አመራሩ የመፈጸም አቅም መገንባቱን፣ ከከተማው የሚሰበሰበውን ገቢና የሚመደበውን በጀት በተገቢው መልኩ ለልማት ስራዎች ለማዋል መቻሉ፣ ወጪ ቆጣቢ የሆኑ አሰራሮችንና ልምዶችን ማጎልበቱ፣ ከምንም በላይ ደግሞ ትልቅ ሀብት የሆነውን ህዝቡን መያዙ (ህብረተሰቡ በጉልበቱ (በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል)፣ በእውቀቱ (የተማረው የህብረተሰብ ክፍልን ያጠቃልላል፡- ምሁራን፣ የመንግስት ሰራተኛው፣ አመራሩ)፣ በቁሳቁስ (የግንባታ ጥሬ እቃዎችን እንደ ሲሚንቶ፣ አሸዋ ወዘተ.. ገዝቶ በማቅረብ፣ አካፋ፣ ዶማ፣ ጋሪ፣ ዲጂኖ ወዘተ... ከቤቱ ይዞ በመምጣት) እንዲሁም በፋይናንስ ረገድ ለአካባቢ ልማት ስራዎች የሚጠበቅበትን ድርሻ በጥሬ ገንዘብ በማዋጣት ከፍተኛ ተሳትፎ የማድረግ አቅምን መገንባቱ) ነው፡፡ በአጠቃላይ የከተማው ህብረተሰብ የልማት ስራዎችን በስፋት ማከናወን ከጀመረበት 2009 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ የጉልበት፣ የቁሳቁስና የዕውቀት አስተዋፅኦ በማድረግ 1,529,411 ሚሊዮን ብር ማዳን ተችሏል፡፡

በህብረተሰቡ የመፈጸም አቅም ከተከናወኑ ተግባራት መካከል የከተማው ሆስፒታል ተጠቃሽ ሲሆን የከተማው አስፓልት መንገድ ግንባታም የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ የከተማው አስፓልት ሲገነባ እና የኮብልስቶን መንገድ ሲሰራ ግለሰቦች የግንብ አጥር ከማፍረስ አንስቶ እስከ መኖሪያና ድርጅት እንዲሁም ለመኝታ አገልግሎት የሚውል ከአስር ክፍሎች በላይ ያለምንም የካሳ ክፍያ ማፍረስና ለልማቱ ተሳታፊ መሆን የቻሉበት ሁኔታ መኖሩ የከተማውን አቅም ያሳያል፡፡ ይህም በመሆኑ ተሞክሮው በአጭር ጊዜ ፈጣንና እመርታዊ ለውጥ አምጥቷል፡፡ በማሳያነት የሚጠቀሰውም ተሞክሮው በከተማዋ ውስጥ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በአካባቢ የህብረተሰብ ተሳትፎ የልማት ፕሮጀክቶችን ከማሳካት አኳያ ከአመለካከት፣ ከአደረጃጀት፣ ከአመራር እና ከተሳትፎ አንጻር በአጭር ጊዜ ፈጣንና እመርታዊ ለውጥ ማስመዝገቡ ነው፡፡

## 4. የማጠቃለያ ምዕራፍ

## 4.1. ስራው ቀጣይነት ያለው ስለመሆኑ

### 4.1.1 የመልካም ተሞክሮው የዕድገትና የልማት ቀጣይነት

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ መልካም ተሞክሮ የተቋማትን አቅም በመገንባትና ድርጅታዊ መዋቅርና የዉሳኔ አሠጣጥ ሂደቱ በግልጽ ሚናንና ተጠያቂነትን በተለያየ እርከን ላሉ ተገልጋዮች/ባለድርሻዎች ማስቀመጡ ይገኝበታል፡፡ ይህም የሚገለጸው አመራሩ ከላይ እስከ ታች ድረስ በመንቀሳቀስ ህብረተሰቡን በልማት ስራዎች ላይ በማወያየት እንዲሁም የልማቱ ባለቤትና ተጠቃሚ እንዲሆን በመስራት፣ ለእያንዳንዱ እንቅስቃሴም በየደረጃው ግልጽነትንና ተጠያቂነትን በማስፈን ሂደት የተሳካ ስራ በመሰራቱ ውጤት ሊመዘገብ ችሏል፡፡ በተጨማሪም ብቁ ግልጽና ተጠያቂነት ያለዉ የአስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት ያለውን የሰው ሀይል፣ ቴክኒክ፣ ገንዘብና የተፈጥሮ ሀብት ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ መጠቀሙ ዘለቄታዊ ለውጥን ከማስመዝገቡም ባሻገር ሌሎች በከተማዋ የሚገኙ ቀበሌዎች በሌሎች አካባቢዎች በተሰራው የህብረተሰብ ተሳትፎ የልማት ስራዎች በመሳተፍና በመነሳሳት ልማቱ የቀጠለበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

ተሞክሮው ሲቀመር የልማትና የዕድገት ቀጣይነቱን ለመመዘን የሚያስችለን እያንዳንዱ እንቅስቃሴ በህዝቡና በተወካዮቹ በመሆኑና ተሞክሮው ስራ ላይ በዋለበት ቦታ ላይ ያለውን ለውጥ ሌላው ህብረተሰቡ ሲያይ የውድድር ስሜት መፍጠር የሚችል በመሆኑ ቀጣይነት እንደሚኖረው ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

### 4.1.2. በተለያዩ ተቋማት ላይ የሚታየውን የጋራ ችግር መፍታቱ

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ የህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ የአካባቢ ልማት ስራዎች ተሞክሮ የከተማዋን ቁልፍ ችግሮችና የጋራ ችግሮች የፈታ መሆኑ በህዝቡ ላይ ያመጣውን አወንታዊ ፋይዳ በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ተሞክሮው ከአንድ ተቋም በላይ ለሆኑ እና በውስጣቸው ለሚገኙ ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ማስገኘቱን በተመለከተም ተሞክሮው በተለያዩ ተቋማት ውስጥ የሚተገበርና ውጤታማነቱ የተረጋገጠ ከዛም አልፎ ዘላቂ መፍትሄ የሚያስገኝ መሆኑን መግለፅ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ የከተማውን የፍሳሽ አወጋገድ ለማስተካከል በህብረተሰቡ ተሳትፎ በርካታ ድቾች የተገነቡ በመሆኑ በዘርፉ የነበረውን ችግር ያቃለለ ሲሆን ዘላቂነቱ አያሻማም፣ በተጨማሪም በአረንጓዴ ልማት ዘርፍ የከተማዋን ፅዳትና ውበት ከመጠበቅ አኳያ እየተተከሉና እንክብካቤ እየተደረገላቸው ያሉ ችግኞችና የፓርኮች ልማት እንደምሳሌነት ማንሳት ስለሚቻል ዘላቂ መፍትሄ የሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

### 4.1.3. ተስፋ ሰጪነቱ

ተሞክሮው ተስፋ ሰጪነቱ የሚረጋገጥበት በመጀመሪያ ደረጃ በከተማዋ እድገት ላይ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣ መሆኑ ሲሆን ከዚያም ባለፈ የተቀመረው በቂ መረጃዎችን በማሰባሰብ መሆኑና ለመተግበር ቀላልና ውስብስብ ባለመሆኑ ተሞክሮውን አምኖ ተቀብሎ ለመተግበር ቁርጠኛ የሆነ አመራር ካገኘ በቀላሉ መተግበር የሚቻል መሆኑ ተሞክሮው ተስፋ ሰጪ መሆኑን ያመለክታል፡፡

## 4.2. ተሞክሮውን ስለማስፋት

### ሀ/ ለመስፋት ያለው ዕምቅ አቅም /potential/

ዕጩ መልካም ተሞክሮዎችን በማወዳደርና የተሻለውን በመለየት ሂደት ውስጥ እጅግ መሠረታዊው መስፈርት ተሞክሮው ሰፊ የመስፋት ዕድል ያለው መሆኑ ነው፡፡ በዚሁም መሰረት በአዲግራት ከተማ የተከናወነው የህብረተሰብ ተሳትፎ የልማት ስራ ከአደረጃጀት፣ አሠራር፣ አመራርና የማነቃ አፈታት ዘዴ አኳያ ሲታይ ሊተገበር የሚችልባቸው ቦታዎች ወይም ሁኔታዎች ብዛት በተነፃፃሪ የላቀ ሆኖ ይገኛል፡፡ የከተማው የልማት እንቅስቃሴ በተሞክሮነት ሊመረጥ የታሰበው ያመጣው የለውጥ አድማስ ሰፊና በተወሰኑ ቦታዎች ወይም ጥቂት የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ብቻ ሳይሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያስከተለው አዎንታዊ ተፅዕኖው ሰፋ ወዳለ አካባቢ እና የህብረተሰብ ክፍል ሊደርስ የሚችል መሆኑ የሀላባ ቁሊቶ ከተማን ተሞክሮ ተመራጭ ከሚያደርጉት ዋና ዋና ባህሪያት መካከል አንዱ ነው፡፡

### ለ/ አስፋፍቶ መጠቀም

ተሞክሮው በአግባቡ የተቀመረ በመሆኑና አዳዲስ ፈጠራዎችን ያካተተና በቀላሉ ግንዛቤ ፈጥሮ አስፋፍቶ መጠቀም የሚቻል ነው፡፡ ለምሳሌ የህዝብ ተሳትፎ መንግስትና ህዝብ ተግባብተው የሚሰሩት ስራ ሲሆን ህዝቡ ከኪሱ ከሚያወጣው ተሳትፎ በተጨማሪ በተለይ የጎርፍ አደጋን ለመከላከል በሚካሄዱ የቁፋሮ ስራዎች ላይ በጉልበቱና በቁሳቁስ በሚያደርገው አስተዋፅኦ ውጤታማ የሚሆንበት ስልት መቀመሩ ይህም መስፋት የሚችል መሆኑ፤ ከግቢ የሚወጣ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ /ሴፍቲ ታንክ/ ሊተገበር የሚችል መሆኑ፣ በተጨማሪም የአረንጓዴ ልማቱን ከመደገፍ አኳያ ችግኞችን ተንከባክቦ ማሳደጉ በቀላሉ ሊተገበር የሚችል በመሆኑና በአጠቃላይ ተሞክሮው በከተማዋ ከፍተኛ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን የፈታ በመሆኑ በከፍተኛ ደረጃ አስፋፍቶ መጠቀም ይቻላል፡፡

### ሐ/ ወደ ሌሎች ለመስፋት ያለው ብቃት

ተሞክሮው በክልሉ ባሉ ከተሞች ተቀምሮ የሰፋ ሲሆን ወደ ሌሎች የሀገራችንም ከተሞች መስፋት የሚችል ነው፡፡

### መ/ አስተማሪና ተላላፊነቱ

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ የልማት ስራዎችና በህብረተሰቡ ላይ የመጣው ለውጥ በተሞክሮነት ለሌሎች የሀገራችን ከተሞች የሚተላለፍና በከተማውም እያደገ የመጣ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተለይም ከተማው ወደ ተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች መተላለፊያ እንደመሆኗ መጠን የተሰሩ የልማት ስራዎች በተለይም በጎርፍና ፍሳሽ አወጋገድ፣ በአረንጓዴ ልማት፣ በጽዳትና ውበት፣ በአስፋልትና ኮብል ስቶን መንገዶች ግንባታ እንዲሁም በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የስራ እድል ፈጠራ የተሰሩ ስራዎች ለሌሎች አስተማሪና ሊተላለፍ የሚችል ተሞክሮ ነው፡፡

### ሠ/ ተሞክሮው ከተለያዩ ተቋማት የተሰባሰቡ መረጃዎችም ሆነ በምርምር ከተገኙ የተሞክሮ ጥናቶች ጋር ሲወዳደር ተመሳሳይ ችግሮችን የመፍታት አቅሙ

የተሞክሮው መነሻ የህብረተሰቡ የልማት ፍላጎት መጨመርና ከከተማዋ አቅም ጋር ችግሮቹን መፍታት ባለመቻሉ በምርምር ሳይሆን በውይይትና ከተለያዩ ተቋማት በሚገኙ መጋቢ መረጃዎች በመሆኑ በትግበራ ወቅትም ውጤታማነቱ እየጨመረ መምጣቱ ከሌሎች ተሞክሮዎች ጋር ሲወዳደር ከፍተኛ አቅም የፈጠረ ነው፡፡

### ረ/ የተሞክሮው የዋጋ አዋጪነት

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ መልካም ተሞክሮ አጥጋቢና ውጤታማ የሆነ የገንዘብና የሰው ሀይል እንዲሁም የአካባቢ ሀብትንና እቃዎችን በትግበራና በአሰራር ሂደቱ መጠቀም ችሏል፡፡ ለምሳሌ ህብረተሰቡ በገንዘቡ ዝቅተኛ ገቢ ካለው እስከ ባለሀብቱ፣ በጉልበቱ የተለያዩ የጉልበት ስራዎችን በተለይም በአስፋልትና ኮብል ስቶን መንገድ ስራዎች ላይ በገንዘቡና በጉልበቱ አስተዋጽኦ ከማድረግ ጀምሮ ያለምንም ካሳ ክፍያ አጥሩንና ቤቱን በማፍረስ ለካሳ ክፍያ ይወጣ የነበረውን ከፍተኛ ግምት ያለውን ገንዘብ ማዳን መቻሉ፣ የጎርፍ ማስወገጃ የዲች ግንባታ ላይ በቁፋሮና ያለውን ቁሳቁስ ለልማቱ ተግባር በፍቃደኝነት በመስጠት አጥጋቢና ውጤታማ ስራ ሰርቷል፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ ስራ ሲሠራ ህብረተሰቡ የሚሳተፍበት ደረጃ እየጨመረ በመምጣቱ የከተማውን በጀት ከመቆጠብ አንጻር በጥቂት ዋጋ በርካታ ስራ መስራት ያስቻለ በመሆኑ አዋጪ ያደርገዋል፡፡

## 4.3. ትምህርት ሊወሰድባቸው የሚገቡ ጉዳዮች /Lesson Learnt/

### 4.3.1. አመለካከት ላይ በሚሰራው ስራ ልክ ውጤት ማግኘት እንደሚቻል

በከተማው አሁን የሚታየው ለውጥ ዋና መነሻ አስፈጻሚ አካላት በአመለካከት ስራውን ተቀብለው መምራት መጀመራቸውና ባለድርሻ አካላት እና ተቋማትም ፋይዳውን ወደ መረዳት ደረጃ በመድረሳቸው ነው፡፡ ቀደም ሲል የህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ስራዎች የፖለቲካ አመራሩን ትኩረት አላገኘም ተብሎ በየመድረኩ ሲነሳ የነበረ ችግር ሲሆን አሁን ላይ በሀላባ ቁሊቶ ከተማ ይህ ችግር

በመሰረታዊነት ተቀይሯል፡፡ ምክንያቱም በየደረጃው ያለው አመራር ስራውን እየገመገመ የሚመራበትና የአመለካከት ግንባታውም በተመሳሳይ የሚከናወንበት አግባብ የተፈጠረ ሲሆን በከተማውም የሚታይ ለውጥ መምጣት መጀመሩ በመለካከት ላይ የተሰራው ስራ ውጤታማ እንደነበር ማየት ይቻላል፡፡

### 4.3.2. ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማነቃነቅ የግብዓት ችግሮችን መፍታት እንደሚቻል

በከተማው ደረጃ ያሉ ተቋማት ለግቢያቸውና ለአካባቢያቸው ጽዳትና ለአረንጓዴ ልማት በሚሊየን የሚገመት በጀት መመደባቸውና ከዚህ በተጨማሪም ግለሰቦች በራሳቸው ለጽዳትና ውበት አስፈለጊውን ግብዓት በማሟላት ግቢአቸውንና አካባቢያቸውን መንከባከብ መጀመራቸውንና ለአረንጓዴ ልማት የሚጠቅሙ የውበትና የጥላ ችግኞችን በመግዛት መትከላቸው ከግብአት ባሻገር አጀንዳውን ህዝባዊ መሆኑን ያመለክታል፡፡

### 4.3.3. መረጃ መሰብሰብና ማደራጀት

በአጠቃላይ በከተማዋ በህብረተሰብ ተሳትፎ ደረጃ የሚተገበሩ ተግባራትንና ለከተማው ልማት አስተዋጽኦ የሚረዱ እና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን አስቀድሞ በመለየት፣ መረጃ በማሰበሰብና በማደራጀት ወደ ትግበራ መግባት የተቻለ ሲሆን ይህም የችግሩን ጥልቀት ለመረዳትና እቅድ ለማቀድ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

### 4.3.4. እንደአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ሊያሰራ የሚችል አሰራር መዘርጋት መቻሉ

በከተማው ከጽደትና ውበት እንዲሁም ከአረንጓዴ ልማት አንጻር ከፍተኛ ችግር ተደርጎ ሲነሳ የነበረው የስድ እንሰሳት ጉዳይ ነበር፡፡ ስድ የሚለቀቁ እንስሳት በከተማው የሚተከሉ ችግኞችን ጭምር የሚያወድሙበት ሁኔታ የነበረ በመሆኑ እና በከተማው መንገድ ላይም ጉዳት በማድረስ የህብረተሰቡን የልማት ተነሳሽነት ላይ አሉታዊ አስተዋጽኦ አድርጎ የነበረ ሲሆን ከተማው ይህን ችግር ለመፍታት የአካባቢ ደንብ በማዘጋጀትና በዚሁ አግባብ መፈጸም በመቻሉና ድርጊቱን ሲፈፅሙ የነበሩ ግለሰቦችም በልማቱ አስፈላጊነት ላይ እያመኑ በመምጣታቸው ከብቶች ስድ የማይለቀቁበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

## 4.4. ማጠቃለያ

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎና የአካባቢ ልማት ስራዎች በክልል ደረጃ እውቅና ያገኘ በመሆኑና በሚኒስቴር መ/ቤቱም በተሞክሮ ልየታ ወቅት ለተሞክሮ ብቁ መሆኑ በመረጋገጡ የሀገራችን ከተሞች ከተሞክሮው ሰፊ ልምድ እንደሚቀስሙበት ይታመናል፡፡ በተለይም በአካባቢ የልማት ስራዎች ላይ ህብረተሰቡን ተሳታፊ፣ ተጠቃሚና ባለቤት ማድረጉ፣ የአመለካከት

ማነቆዎችን መስበሩ፣ የአመራሩና ፈጻሚው ቁርጠኛነት በስፋት መስተዋሉ እንዲሁም ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል አሳታፊ ማድረግ መቻሉ በተሞክሮ ደረጃ ለሌሎች የሀገራችን ከተሞች ሊሰፉና ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

የከተማ አስተዳደሩ በልማት ስራዎች፣ በመልካም አስተዳደርና በሌሎችም ጉዳዮች ህዝቡን በነቂስ ማሳተፍ መቻሉ ውጤታማ እንዳደረገው ከተሰሩ ስራዎችና ከዚህ የተሞክሮ ሰነድ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በቀጣይም የህብረተሰቡ ተሳትፎ ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚመለከታቸው ከክልል እስከ ፌደራል ያሉ አካላት አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**ማጣቀሻዎች**


1. የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር የለውጥ ትግበራና የልማት ሥራዎች አፈፃፀም ምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት ማንዋል፤ የካቲት 2005 ዓ.ም አዲስ አበባ፣
2. https://en.m Wikipedia.org/wiki/Alaba
3. የሀላባ ቁሊቶ ከተማ አስተዳደር በከተማ ጽዳትና አረንጓዴ ልማት እንዲሁም በህብረተሰብ ተሳትፎ የተሰሩ ስራዎች ምርጥ ተሞክሮ ሰነድ፤ ግንቦት 2010 ዓ.ም ሀላባ ቁሊቶ፣
4. ከ2005 ዓ.ም እስከ 2008 ዓ.ም የተዘጋጁ የከተማው መጽሄቶችና ዶክመንተሪ ፊልሞች፣
5. የህዝብ ውይይቶች፣ የግምገማ መድረኮችና የመስክ ምልከታ ፎቶ ግራፎች፣

## ክፍል ሁለት

# ምዕራፍ አንድ፡- የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዳይዜሽን አስፈላጊነት እና የአገልግሎት አቅርቦት የማሻሻል ተግዳሮቶች

## 1. መግቢያ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በከተሞቻችን የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልፅ፣ ተደራሽና ስታንዳርዱን የጠበቀ እንዲሆን፣ እንዲሁም የዜጎች ተጠቃሚነትና እርካታ ከፍ እንዲል ለማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ ይህም የከተሞቻችንን የአገልግሎት አቅርቦት በማሻሻል፣ የዜጎችን የእርካታ ደረጃ ከፍ በማድረግ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ከፍተኛ ፋይዳ ስለሚኖረው ነው፡፡ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት ስታንዳርዱን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ሲሆን እስካሁን በተደረገው ጥረትም 7 የአገልግሎት ስታንዳርዶችን፣ እንዲሁም የማስፈፀሚያ ማኑዋሎችን በማዘጋጀትና በማፅደቅ በ155 ከተሞች እንዲተገበሩ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ የትግበራው ሽፋን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንዲሄድ በዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ እስካሁን በተደረገው ክትትልየአገልግሎት ስታንዳርዶቹ ትግበራ ሂደት አዝጋሚ እንደሆነና በቂ ትኩረት ያልተሰጠባቸው ክልሎችና ከተሞች እንዳሉም ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዜጎች ከማዘጋጃ ቤቶች የሚፈልጉትን አገልግሎቶች ለማግኘት ማሟላት የሚጠበቅባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ምን ምን እንደሆኑ ቀድሞ የማሳወቅ፣ በማዘጋጃ ቤቶቹ አገልግሎት ሰጪ የሥራ ክፍሎች አገልግሎቶቹን ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜና አገልግሎቱን ለማግኘት ተገልጋዩ እንዲከፍል የሚጠበቀው የአገልግሎት ክፍያ መጠን ለህዝቡ በሚፈለገው ልክ ግልፅ የማድረግና ዜጎችን የማስገንዘብ ሥራ፣ የመረጃ ግልፅነትና ተደራሽነት በአግባቡ ባለመሠራቱ ጉዳዩ ምላሽ ያላገኘ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ሆኖቆይቷል፣ አሁንም ይስተዋላል፡፡

በመሆኑም በከተሞች በማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት ህዝቡን በማርካት ረገድ የሚስተዋለውን ሰፊ ክፍተት ለመሙላትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄ በአግባቡ መመለስ ይቻል ዘንድ በየደረጃው ካለው የሴክተሩ አመራር ጋር ውይይት በማድረግ በቂ ግንዛቤ ለመፍጠርና መግባባት ላይ መድረስ በማስፈለጉ ይህ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሠነድ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. የስታንዳርዳይዜሽን እና የስታንዳርድ ጽንሰ ሀሳብ /ምንነት/

### 2.1. ስታንዳርዳይዜሽን /concept of standardization/

በአንድ ጉዳይ ላይ የተሻለ ውጤት ላይ ለመድረስ የጋራ የሆነ፣ ወጥነት ያለውና በተደጋጋሚ /repeatedly/ እና ቀጣይነት /consistently/ ባለው መልኩ መጠቀም የሚያስችለውን የአመራረት፣ የአሰራር፣ ወይም የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ለመከተል ሲባል ስታንዳርዶችን /ደረጃዎችን/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የማዘጋጀት፣የማሳተም እና የመተግበር /ጥቅም ላይ የማዋል/ ሂደትነው፤

የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዳይዜሽን የማዘጋጃ ቤቶችን የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም፣የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የህግ ማዕቀፎችን በማሻሻል የአገልግሎት አሰጣጥ ከጥራት፣ ከወጪ፣ ከጊዜና ከመጠን አንፃር ስታንዳርዱን /ደረጃውን/ የጠበቀ እንዲሆን የማድረግ ሂደት ነው፡፡ ዓላማውም፡-

- ማዘጋጃ ቤቶች ለነዋሪዎች ለሚያቀርቧቸው አገልግሎቶች ወጥ የሆነ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ለመዘርጋት፣
- በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚታዩ አላስፈላጊ ውጣ ውረዶችን፣ እንግልቶችን እና ወጪዎችን በማስቀረት አገልግሎቱን ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽ፣ ተደራሽ፣ ውጪ ቆጣቢ፤ በአጠቃላይ የተገልጋዮችን ፍላጎት የሚያረካ እንዲሆን ለማድረግ ነው፤
- በከተሞች የአገልግሎትአቅርቦት /አሰጣጥ/ ነባራዊ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ጥናት በማድረግ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶች የሚጠቡበትን ዘዴ በመቀየስ ለከተሞች አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ነው፡፡ ይኸውም የአገልግሎት አቅርቦት እንዲሻሻል ብሎምእንዲዘምን ለማድረግ ነው፡፡




### 2.2. የስታንዳርድ ጽንሰ ሐሳብ /concept of standard/

ስታንዳርድ /ደረጃ/ በስምምነት ላይ ተመስርቶ የሚዘጋጅ ሆኖ እውቅና ባለው አካል ጸድቆና በሁሉም ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ ምርትን ወይም አገልግሎትንወይም አሰራርን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ስምምነት ላይ በተደረሰው ልክ እንዲቀርብ የሚያደርግ ሰነድ ነው፡፡[1]

[1]A standard is a document, established by consensus and approved by a recognized body that provides, for common and repeated use, rules, guidelines or characteristics for activities or their results, aimed at the achievement of the optimum degree of order in a given context. (Ethiopian Standard Agency (ESA/ISO definition)

ከአገልግሎት አሰጣጥ አንፃር ሲታይ ‹‹ስታንዳርድ ለተገልጋዮች /ለደንበኞች/ የሚሰጠው አገልግሎት የደንበኞችንና የአገልግሎት ሰጪዎችን ጊዜ፣ ጉልበትና ወጪ በመቀነስ ቅልጥፍናን፣ ውጤታማነትን፣ ጥራትንና ግልፅነትን በሚጨምር መልኩ እንዲሰጥ /እንዲቀርብ/ ለማድረግ በስምምነት ላይ በመመስረት የሚዘጋጅ ሠነድ ነው፡፡››

ስታንዳርድ ለቁሳቁስ፣ ለምርት፣ ለአገልግሎት እና ለአሰራር ወጥ የሆኑ መስፈርቶችን /requirements/፣ ስፔሲፊኬሽኖችን (specifications)፣ መመሪያዎችን /guidelines/ ለተፈለገው ጉዳይ ወይም ዓላማ በሚመጥኑ ልክ የሚያስቀምጥ ሠነድ ነው፡፡

## 2.3. የስታንዳርድ ባህሪያት

ስታንዳርድ በተደጋጋሚና በቀጣይነት ጥቅም ላይ የሚውል፣አስፈለጊ ሆኖ ሲገኝ የሚከለስ /በተለያዩ ምክንያቶች ለምሳሌ፡-በቴክኖሎጂ መሻሻል ምክንያት፣ አምራቹን ወይም አገልግሎት ሰጪውንና ተጠቃሚውን የማያሠራ ሆኖ ሲገኝ/፣ ከጥቅም ውጭ እንዲሆን የሚደረግ/ የሚወገድ/፣ የተዘጋጀለትን ዓላማ የሚያሳካ፣ ሲዘጋጅ ከተገልጋዮችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር ውይይት ተደርጎበት /public consultation/ የብዙኃኑንይሁንታ ያገኘ፣ ሊፈጸም /ሊተገበር/ የሚችል፣ ለምዘና የሚያገለግል፣ እውቅና ባለው አካል የሚፀድቅ ፣ ከመተግበሩበፊትየሚመለከተው አካል /ፈፃሚው፣ ተገልጋዩ እና ሌለውም/ እንዲያውቀው መደረግ ያለበት ነው፡፡

## 2.4. የአገልግሎት ስታንዳርድ አስፈላጊነት

የአገልግሎት ስታንዳርድ አስፈላጊነት በከተሞቻችን ለዜጎች የሚቀርበው /የሚሰጠው/ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት፡-

- ✓ ወጥነት ያለው እንዲሆን፤
- ✓ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት በግልፅነትና በተጠያቂነት እንዲቀርብ ለማድረግ አጋዥ የሥራ መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል፤
- ✓ የተገልጋዮችን እንግልት ለመቀነስ፤
- ✓ በአገልግሎቱ አሰጣጥ ዙሪያ የሚንፀባረቀውን የኪራይ ሰብሳቢነትን አመለካከትና ተግባር በማስወገድ መልካምአስተዳደር እንዲሠፍን፤ እና
- ✓ የዜጎች ተጠቃሚነትና እርካታ ከፍ እንዲል ለማድረግ፤

የአገልግሎት አቅርቦት ስታንዳርዶችን በማዘጋጀት በአገሪቱ ከተሞች እንዲተገበሩ ማድረግ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

---

- A standard is a document that provides requirements, specifications, guidelines or characteristics that can be used consistently to ensure that materials, products, processes and services are fit for their purpose. (ISO Definition)

# 3. የዜጎች የስምምነት ሠነድ /Citizene charter/ ፅንሰ ሐሳብና አስፈላጊነት፤

## 3.1. የዜጎች የስምምነት ሠነድ /Citizene charter/ ፅንሰ ሐሳብ

የዜጎች የስምምነት ሠነድ ዜጎች ከመንግስታዊ ተቋማት ማግኘት ስለሚገባቸው አገልግሎትና የአገልግሎት ደረጃ ከጊዜ፣ ከጥራት፣ ከመጠን እና ወጪ አንጻር በግልጽነት መርህ ቀድሞ የሚያሳውቅ፤ ይኸው አገልግሎት በተጓደለ ጊዜም መብታቸውን ለማስከበር ቅሬታና አቤቱታ የሚያቀርቡበትን ሂደት በአጭር፣ ግልጽና ቀላል በሆነ ቋንቋ የሚገልጽ ሠነድ ነው፡፡ የዜጎች ቻርተር የአገልገሎት አሰጣጥን የተቃና እና የተሳለጠ የሚያደርግ እንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ኃላፊነትና ተጠያቂነት እዲረጋገጥ በማድረግ ለመልካም አስተዳደር መስፈን ቁልፍ ድረሻ ያለው ሠነድ ነው፡፡ በመሆኑም የዜጎች የስምምነት ሰነድ በተለያዩ መንገዶች /አማራጮች/ ለዜጎች ተደራሽ ሊሆን ይገባል፡፡ እነዚህም አማራጮች፡-

- ብሮሸር /በራሪ ወረቀት/ በማሳተምና በማሰራጨት፤
- በመረጃ ዴስክ /Information Desk/፤
- አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ወይም በባነር ለዜጎች በሚታይ ቦታ ላይ በመለጠፍ፤
- በህዝብ ስብሰባዎች፤
- በአገልግሎት መስጫ ቦታ ላይ አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት ለተገልጋዮች በአካል /ፊት ለፊት/ ገለፃ በማድረግ፤
- በተቋማቱ ድረ-ገጽና በማህራዊ ድረ-ገጾች፤
- በሚኒ ሚዲያና ቢቻል በብዙሃን መገናኛዎች እና በሌሎችም አማራጮች ሊሆን ይገባል፡፡

ከእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት አማራጮች ቢያንስ በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አማራጮች ለዜጎች ተደራሽ የማያደርግ የአገልግሎት ሰጪ ተቋም የዜጎች የስምምነት ሰነድ ቢያዘጋጅም ፋይዳና ትርጉም እንደሌለውና ከፍተኛ የግልፅነትና የመረጃ ተደራሽነት ችግር ያለበት እንደሆነተደርጎ ይወሰዳል፡፡

የዜጎች የስምምነት ሠነድ ይዘቱ በዋነኛነት የሚከተሉትን የያዘ መሆን አለበት፡-

- የሚሰጠውን የአገልግሎት ዓይነት፤
- አገልግሎት ሰጪውን የሥራ ክፍል/ዘርፍ/፤
- አገልግሎቱን ለመስጠት የሚፈጀውን የጊዜ ርዝማኔ፣ መጠን፣ ጥራት እና ለአገልግሎቱ ከዜጎች የሚጠበቀውን ወጪ /የአገልግሎት ክፍያ/፤
- አገልግሎቱን ለማግኘት ዜጎች ሊያሟሉ የሚገባቸውን ዝርዝር ቅድመ-ሁኔታዎች፤

## 3.2. የዜጎች የስምምነት ሠነድ /Citizene charter/ አስፈላጊነት

የዜጎች የስምምነት ሠነድ አስፈላጊነቱ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የዜጎችን አላስፈላጊ ውጣውረድና እንግልት፣ አላስፈላጊ እጅ መንሻ ጥያቄ ከመቀነሱም በላይ ዜጎች ቀድመው እንዲዘጋጁበት የሚያደርግና የአገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ በማድረግ ግልፅነትን የሚያሰፍን አሰራር በመሆኑ ነው፡፡ ይህንን ለዜጎች ተደራሽ ማድረግ፡-

- ዜጎች ከአገልግሎት ሰጪ የሥራ ክፍሎች /ማዘጋጃ ቤቶች/ ማግኘት ለሚፈልጉት አገልግሎት ማሟላት የሚገባቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች አስቀድመው እንዲገነዘቡና በቂ ዝግጅት አድርገው መቅረብ እንዲችሉ ያስችላቸዋል፤
- የተገልጋዮችን የጊዜ ብክነት እና ወጪን ይቀንሳል፤
- በተገልጋዮችና በአገልግሎት ሰጪ የሥራ ክፍሎች መካከል ተግባቦትን ያጠነክራል፤ መተማመንን ይፈጥራል፤
- ግልጽነትን ያሰፍናል፤
- አገልግሎት ሰጪው ተቋም በዜጎች የስምምነት ሠነድ /በዜጎች ቻርተር/ ላይ በተቀመጠውመሠረት አገልግሎት ማቅረብ ካልቻለ ዜጎች ቅሬታቸውንና አቤቱታቸውን እዚያው ተቋም ውስጥ አንድ እርከን ከፍ ብሎ ላለው የአስተዳደር እርከን ደረጃ በደረጃ አቅርበው ፈጣን ምላሽ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡

## 4. የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አቅርቦትን ለማሻሻል የተወሰዱ እርምጃዎች

በከተሞች የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አቅርቦትን ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልፅና ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የከተማ ልማት ፖሊሲ፤ የተሻሻለው የከተሞች ልማታዊ መልካም አስተዳደር ግንባታ ማዕቀፍና የማስፈፀሚያ ስልቶች እና የሲቪል ሰርቪስ የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም እንደመነሻ በመውሰድ ከክልል ክልል፤ እንዲሁም ከከተማ ከተማ ያለውን የአገልግሎት አሰጣጥ ልዩነት ለማስወገድና ወጥነት ያለውን የአገልግሎት አቅርቦት ለመከተል ለማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ስታንዳርዶችን የማዘጋጀት፤ ወደ ትግበራ የሚያስገባ ሥልጠና የመስጠት፤ አተገባበሩን ክትትልና ድጋፍ የማድረግ እና የአገልግሎት አቅርቦቱን አፈፃፀም በመመዘን ለከተሞች ግብረ-መልስ የመስጠት ሥራዎች ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡

በዚሁ መሠረት ለማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ስታንዳርዶች ሲዘጋጁ በከተሞች የህዝብ እሮሮ ለሚበዛባቸው ለ3 አገልግሎቶች (ለመሬት ልማትና ማኔጅመንት ዘርፍ ሥራዎች፣ ለግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ እና ለደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ አገልግሎት) ስታንዳርዶች ቅድሚያ

በመስጠት /የካቲት 20/2007 ዓ/ም በማጸደቅ/፤ በማስከተልም ለ4አገልግሎቶች/ለቄራ፣ ለህዝብ እና የጋራ መፀዳጃ እና የጋላ መታጠቢያ አገልግሎት፣ ለእሳት አደጋ መከላከል እና ለማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ/በድምሩ ለ7 አገልግሎቶች የአገልግሎት ስታንዳርዶችንበማዘጋጀትና በማፀደቅ ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ በከተሞች እንዲተገበሩ ጥረት ተደርጓል፡፡

የአገልግሎት ስታንዳርዶቹን አተገባበር በተመለከተም በ2008 ዓ/ም በ19 ከተሞች በመጀመር በሂደት እስከ 2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ 155 ከተሞች ወደ ትግበራ እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን ለተፈጻሚነቱም ከክልል ቢሮዎች፣ ከዞን መዋቅሮችና አደረጃጀቱን ከፈጠሩ ከተማ አስተዳደሮች ለተውጣጡ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዳይዜንና ምዘና አስተባባሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን በተከታታይ ለመስጠት የተቻለ ሲሆን ከ155 ከተሞች ለተውጣጡ የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና በመስጠት ለዜጎች የሚሰጠው አገልግሎት ከተለመደው የአገልግሎት አሰጣጥ ወጣ በማለት በስታንዳርዶቹ መሰረት ብቻ እንዲሰጣቸውና የአገልግሎት አቅርቦቱም እንዲሻሻል ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡

በከተሞች የአገልግሎት አሰጣጡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በጸደቁ የአገልግሎት ስታንዳርዶች መሠረት ስለመሆኑ፤ የአገልግሎት አቅርቦቱም ከጊዜ ወደ ጊዜ ስለመሻሻሉ/የአገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽና ተደራሽ ስለመሆኑ/ ወደ ትግበራ እንዲገቡ የተደረጉ 155 ከተሞችን መሸፈን ባይቻልም በየዓመቱ የክትትልን ድጋፍ መርሃ ግብር በመንደፍ የክልል ቢሮዎችንና ከተሞችን የመደገፍ ሥራ ሲሰራ ቋይቷል፤ የአገልግሎት አቅርቦት አፈጻጸማቸውንም በመመዘን ግብረ-መልስ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል፡፡

ይሁን እንጂ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን አፈፃፀም መመዘን ብቻውን ዜጎች በአገልግሎት አቅርቦቱ ስለመርካታቸውና መልካም አስተዳደር ስለመስፈኑ ማረጋገጫ ሊሆን ስለማይችል ዜጎች የሚሰጡት ምስክርነት ወይም መረጃ እጅግ በጣም ወሳኝ ጠቋሚ /አመላካች/ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት በከተሞች በማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አቅርቦት የዜጎች የእርካታ ደረጃ የመለካት የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት የዜጎች የእርካታ ደረጃ መለኪያ ማኑዋል በማዘጋጀት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተሰርቷል፡፡ በማኑዋሉ መሠረት የዜጎችን እርካታ ደረጃ ከየክልሉ በናሙናነት በተወሰዱ ከተሞች በጥናት የማረጋገጥ ሥራ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በውስጥ አቅም፤ እንዲሁም ለሦስተኛ ወገን /ለአማካሪ ድርጅት/ በመስጠት በጥናት የማረጋገጥ ሥራምተከናውኗል፤ በቀጣይም ከፍተኛ ትኩርት ተሰጥቶት የሚሠራ ቁልፍ ሥራ ይሆናል፡፡

## 5. በከተሞች የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አቅርቦትን የማሻሻል ተግዳሮቶች

በከተሞች የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አቅርቦት እንዲሻሻል /ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልፅ፣ ተደራሽ እንዲሆንና በተጠያቂነት እንዲቀርብ ለማድረግ/ በርካታ ጥረቶች የተደረጉቢሆንምበከተሞች መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ከሚደረገው ጥረት አንጻር በአገልግሎት አቅርቦቱ ላይ ይህ ነው የሚባል መሻሻል አልመጣም፡፡ የዜጎችም የእርካታ ደረጃ በጣም ዝቅተኛ ነው /ከ45 በመቶ ያላለፈ ነው/፡፡ በመሆኑም መሠረታዊ ተግዳሮቶቹንና ባለሚና አካሉን መለየት እና ዘላቂ መፍትሔ መሻት አስፈላጊ በመሆኑ በ10 በተመረጡ ከተሞች በውስጥ አቅም በዳሰሳ ጥናት ለማረጋገጥ በተሞከረውመሠረት በከተሞቻችን እየተስተዋሉ ያሉተግዳሮቶች በርካታ ናቸው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ከእነዚህም መካከል፡-

❖ **በአገልግሎት ስታንዳርዶቹ ላይ በቂ ግንዛቤ ከመጨበጥ /ከሥልጠና/ ጋር በተያያዘ፣**

- በየአገልግሎት ዘርፎች ያሉ ሠራተኞች በጸደቁ የአገልግሎት ስታንዳርዶች ላይ በቂ ሥልጠና አለማግኘታቸው /በአብዛኞቹን ከተሞች በፌዴራል ደረጃ የሚሰጠውን የአሰልጣኞች ሥልጠና የወሰዱ የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች ወደ ከተሞቻቸው ወርደው ሥልጠና የማይሰጡ መሆኑ/፤
- በፌዴራል ደረጃ የሚሰጠውም ሥልጠና በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት በሚያስችል ልክ አለመሆኑ፤ ተግባር ተኮር ሥልጠና አለመሆኑ፤
- ሥልጠናውን የወሰዱ ባለሙያዎችፍልሰትእና ግንዛቤ የተፈጠረላቸው አመራሮች በየጊዜው መቀያየር፤ ይህንን ታሳቢ ያደረገ ቀጣይነት ያለው ሥልጠና እና ክትትልና ድጋፍ አለመደረጉ፤
- በፌዴራል ደረጃ በሚሰጠው ሥልጠና የሚሳተፉ ከአንዳንድ ክልሎች የሚላኩ አካላት የዘርፉ ሥራ የማይመለከታቸው እግረመንገዳቸውን እንዲሳተፉ ማድረግ፤ ሥልጠናዎችን የኮታ ጉዳይ አድርጎ ማየት፤ የሥልጠና ተሳታፊዎች ፕሮፋይል /የተሟላ መረጃ/ አለመያዝ፤

❖ **ከአገልግሎት ስታንዳርዶች አተገባበር ጋር በተያያዘ፣**

- በየጊዜው የአመራር መቀያየር፤ ከአመራር መቀያየር ጋር ተያይዞ በየጊዜው የአሰራርም መቀያየር፤
- የመዋቅር ችግር መኖሩ /አንዳንዱ የተጠናበት አግባብ ባለሙያን የማይሸከም ወይም ባለሙያ ለቆ እንዲሄድ ምክንያት የሚሆን ነው /የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት፣ የቄራ አገልግሎት፣ የማዘጋጃ ቤታዊ ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት/፤ እንዳንዱ ግልጽ የሆነ አደረጃጀት /ባለቤት/ የሌለው መሆኑ /የበህዝብ መጸዳጃ አገልግሎት/፣
- የሰው ኃይል ማነስ /በተወሰኑ ከተሞች/፤

- በየደረጃው ያለው አመራር ስለአተገባበሩ በቂ ትኩረት አለመስጠትና ክትትል አለማድረግ፣
- የአመራር ቁርጠኝነት አለመኖር ፣በሚኒስቴር መ/ቤቱ ጸድቀው የወረዱ የአገለግሎት ስታንዳርዶች ስለመኖራቸው እንኳ የማያወቁ አመራሮች መኖራቸው፣
- ለስታንዳርዶቹ ትኩረት ያለ መስጠት፣ የተለመደውን አካሄድ መከተል /ከተለመደው የአገልግሎት አሰጣጥ አለመላቀቅ/፣
- በዘርፉ ያለው ባለሙያ ስለ ስታንዳርዱ እኩል ግንዛቤ አለመያዝ /የሰለጠኑና ያልሰለጠኑ ስላሉ/፣
- ሥራው የሚጠይቀው በቂ የግብዓት አቅርቦት እጥረት/አለመኖር /የቁሳቁስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የበጀት/ አቅርቦት አለመኖር፣ /61%/
- ተቋማዊ አደረጃጀት /ለአገልግሎቱ ባለቤት የሆነ የሥራ ዘርፍ/ አለመኖር፣
- በአገልግሎት አሰጣጡ የተሻለ ልምድ ካላቸው ከሌሎች ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳሮች በጥናት የተደገፈ ልምድ አለመወሰድ፣
- የህዝብ እና የጋራ መጸዳጃ ቤቶችን ለመገንባት በቂ የመሬት አቅርቦት አለመኖሩ፣
- የዜጎችን ቅሬታና አቤቱታ ለመፍታት ጥረት አለማድግ፣
- የአገልግሎት ስታንዳርዶቹ ባልተተገበሩበት ሁኔታ የ"UIIDP" የበጀት ድጋፍ ለማግኘት ሲባል የ3 አገልግሎቶች /የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ዘርፍ፣ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፣ እና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ/ ስታንዳርዶች እንደሚተገበሩ ማስመሰል/መሥፈርት ለማሟላት መሯሯጥ/ ፣ ሌሎች አገልግሎቶችን ዞር ብሎ አለማየት፣
- የአገልግሎት ስታንዳርዶች አገልግሎት ማቀላጠፊያ አጋዥ የሥራ መሣሪያዎች እንጂ ተጨማሪ አስገዳጅ ሸክም /extra ordinary burden/ አድርጎ ማየት፣

እነዚህ ከላይ የተገለጹት ተግዳሮቶች በከተሞቻችን የዜጎችንየእርካታ ደረጃ ከፍ ለማድረግና መልካም አስተዳደርንለማስፈን ለሚደረገው ጥረት ውጤታማ እንዳይሆን ጎታች እንቅፋቶች እንደሆኑ ለመለየት ተችሏል፡፡

## 6. የዜጎች እርካታ ፅንሰ ሐሳብ /ምንነት /concept of citizen satisfaction/ እና የመለካት አስፈላጊነት

### 6.1. የዜጎች እርካታ ፅንሰ ሐሳብ /ምንነት/

የዜጎች /የደንበኞች/ እርካታ ሲባል አንድ ተቋም /ድርጅት/ ምርትን ወይም አገልግሎትን ለደንበኞች /ለተገልጋዮች/ በማቅረብ ዕርካታን ለመፍጠር ካስቀመጠው ግብ በላይ በማቅረብ ከአጠቃላይ ደንበኞቹ /ተገልጋዮቹ/ መካከል የረኩት በመቶኛ ተሰልቶ የሚገኝ ውጤት ነው፡፡

ከመንግሥት ተቋማት አንጻር የዜጎች እርካታ ደረጃ መለካት ሲባል የአንድን የመንግሥት ተቋም አፈፃፀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ ዜጎች ከሚጠብቁት አንፃር ስለመሆኑ በዳሰሳ ወይም ጥልቀት ባለው ጥናት ላይ በመመስረት በመጠን /በቁጥር/ የሚገለፅ ውጤት ላይ የሚያደርስ ሂደት ነው፡፡ የዜጎች እርካታ ደረጃ ምዘና /ልኬት/ በሚቀርበው አገልግሎት በተወሰደው ናሙና /Sample/ መሰረት አጠቃላይ የዜጎች እርካታ ያለበትን ደረጃ ለማወቅ የሚያስችል ለዜጎች መጠይቅ በማቅረብ ላይ የተመሠረተ ጥናታዊ አሰራር ነው፡፡

በመሆኑም የዜጎችን /የተጠቃሚዎችን/ የእርካታ ደረጃ መለካት በዋነኛነት ዜጎችን ማዕከል ያደረገ የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደትን መለካት ሲሆን ቀጣይነት ባለው መልክ ተቋማዊ አፈፃፀም እንዲሻሻል የሚያደርግ ጠቃሚ የሆነ የመለኪያ ሥልት ሲሆን በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ የከፋ ችግር ያለበትን ወይም ዜጎች ሊረኩበት ያልቻሉትን በመለየት መንግሥት የአገልግሎት አሰጣጡ እንዲሻሻል ለማድረግ የቅድሚያ ትኩረት እንዲሰጥ የሚያደርግ አንዱ መንገድ ነው፡፡

### 6.2. የዜጎች እርካታ የመለካት አስፈላጊነት

የዜጎችን የእርካታ ደረጃ የመለካት አስፈላጊነት ማዘጋጃ ቤቶች /አገልግሎት ሰጪ የሥራ ክፍሎች/ ለዜጎች ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽና ተደራሽ አገልግሎት በፍትሃዊነትና በተጠያቂነት መንፈስ ስለመስጠታቸው ማረጋገጥ ከሚቻልባቸው ከተለያዩ ሥልቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ከሥልቶቹም መካከል ትልቁን ድርሻ የሚወስደው ዜጎች በሚቀርብላቸው አገልግሎት ምን ያህል እንደረኩ ራሳቸው የሚሰጡትን ምስክርነት /መረጃ/ በመተንተን ማረጋገጥ ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም የዜጎችን እርካታ ደረጃ የመለካት አስፈላጊነት፡-

- ሀ/ ዜጎች ከመንግሥት ጥራቱን የጠበቀ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት እንደሚጠብቁ ለመረዳትና ምላሽ ለመስጠት ስለሚያስችል፣
- ለ/ ዜጎች ለአገልግሎቶች ያላቸውን ተደራሽነትና የአገልግሎቱንም ጥራት ደረጃ በዳሰሳ ጥናት ለማረጋገጥ ስለሚያስችል፣

ሐ/ መንግሥት በአገልግሎት አቅርቦት ቅድመ-ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በቅደም-ተከተል አስቀምጦ ለመተግበር ስለሚያስችል፤

መ/ ዜጎች በመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋም አመራሩና አገልግሎት ሰጪው በአጠቃላይ ለመንግሥት ያላቸው አመኔታ ከፍ እንዲል ስለሚያደርግ /ስለሚያጠናክር/፤

ሠ/ የግልፀኝነትና የተጠያቂነት አሠራር እንዲሰፍን ስለሚያደረግ፤

ረ/ በዜጎች እርካታ ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ የመጣውን መሻሻል /እመርታ/ ለመለካት እንደመነሻ /benchmark/ ስለሚያገለግል፤

ሰ/ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና ቅልጥፍና መሻሻል ያለባቸውን የአገልግሎት ዓይነቶችን ለመለየትና የአሰጣጡንም ሁኔታ ከግኝቶቹ አንፃር ለማስተካከል ስለሚያስችል፤

## 6.3. በከተሞች በማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አቅርቦት የዜጎች እርካታ ደረጃ ያለበት ሁኔታ

የዜጎች የእርካታ ደረጃ የመልካም አስተዳደር መስፈን አንዱና ዋነኛአመላካች ነው፡፡ በመሆኑም በ2012 በጀት ዓመት የዜጎች እርካታ ደረጃ /Citizene satisfaction survey/ በናሙናነት በተወሰዱ 10 ከተሞችና 2 የአዲስ አበባ ክ/ከተሞች በ4 አገልግሎቶች /የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ዘርፍ፣ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣አሰባሰብና አወጋገድ፤ የህዝብ እና የጋራ መጸዳጃ እና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት/ በሶስተኛ ወገን /በአማካሪ/ እንዲጠና ተደርጎ በአማካይ 44% እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚሁ መሠረት፡-

### 6.3.1. የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ዘርፍ አገልግሎት፤



### 6.3.2. የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ አገልግሎት፤




### 6.3.3. የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ አገልግሎት፤




### 6.3.4. የህዝብ መጸዳጃ እና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት፤



## 6.4. የአራቱም አገልግሎቶች አማካይ የእርካታ ደረጃ




# 7. በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

**ተግዳሮቶችን ለመፍታት /ለመቅረፍ/ በቀጣይ በየደረጃው መወሰድ የሚገባቸው ዕርምጃዎች**

## ሀ/ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚና አንፃር፤

- በአገልግሎት ስታንዳርዶቹ ላይ ለባለሙያዎቹ በቂና ወቅቱን የጠበቀ ሥልጠና መስጠት፤ ለአመራሩም ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ቢሰጥ፤
- በየደረጃው ካለው አመራሩ ጋር በሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀደቁ የአገልግሎት ስታንዳርዶች ስለሚተገበሩበትና የአገልግሎት አቅርቦቱም ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ቀጣይነት ያላቸው የጋራ የምክክር መድረኮች እንዲኖሩ ቢደረግ፤
- በማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አቅርቦት ረገድ ከተሞችን በመመዘንበፌዴራል ደረጃ በማወዳደር እውቅና የመስጠት እና በከተሞች መካከል ጤናማ ውድድር እንዲኖር የማድረግ ስራ ቢሰራ፤
- የአገልግሎት አቅርቦቱን ለማሻሻል ብሎም ለማዘመን ለከተሞች ሁለንተናዊ ድጋፍ /የቴክኒክ፣ የቴክኖሎጂ፣ የፋይናንስ/ ቢሰጥ፤ Online service system /E-service/ አገልግሎት እንዲጀምር ጥረት ቢደረግ፤
- የእሳት አደጋና የቄራ አገልግሎት ሙያዎች በዩኒቨርሲቲዎች ደረጃ ትኩረት እንዲያገኙ ግፊት ቢደረግ፤

## ለ/ ከክልል ቢሮዎች ሚና አንጻር፤

- በከተሞች አገልግሎት አሰጣጡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በጸደቁ የአገልግሎት ስታንዳርዶች መሠረት እንዲሆን ለከተማ አመራር ግንዛቤ ማስጨበጥ ቢቻል፤ ለከተሞቹ ያልተቋረጠ ክትትልና ድጋፍ ቢደረግ፤
- የአገልግሎት አሰጣጡበቴክኖሎጂእንድታገዝ /እንዲዘምን/ ድጋፍ ቢደረግ፤
- የአደረጃጀት /የመዋቅር/ ችግር ላለባቸው የአገልግሎት ዘርፎች፡-
  - ✓ የእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎት ፣ የቄራ አገልግሎት ተገቢው ጥናት ተደርጎላቸው ለህብረተሰቡ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት በሚችሉበት ደረጃ በመስኩ ልምድ፣ ክህሎትና ዕውቀት ባለው የሰው ሃይልና በአስፈላጊዎቹ ቴክኖሎጂዎች እንዲደራጁ ቢደረግ፤
  - ✓ በአብዛኞቹ ከተሞች ባለቤት የሌላቸው የአገልግሎት ዘርፎች ለምሳሌ /የህዝብ መፀዳጃና የገላ መታጠቢያ አገልግሎት/ ባለቤት እንዲኖረው ቢደረግ፤
- በአገልግሎት አቅርቦት ማሻሻል እና የዜጎችን እርካታ ከፍ በማድረግ ረገድ ከተሞችን ያሳተፈ የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በስፋት ማካሄድ ቢቻል፤
- የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት ለማስያዝና የአካባቢን ብክለት ለመከላከል የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት፣ ማጽደቅና መተግበር ቢቻል፤ በአካባቢ ላይ ብክለትየሚያስከትሉአካላት ለፈጸሙት ጉዳት ክፍያ የሚፈጽሙበት ሥርዓት ቢዘረጋ /Polluter pay principle/ በተለይም ትልልቅድርጅቶች /ፋብሪካዎች/ ወዘተ.፤
- በየከተሞቹ የህዝብ መጸዳጃ እና የገላ መታጠቢያ ቤቶች መሠረተ ልማት እንዲገነባ ልዩ ትኩረት ቢሰጥ፤ ከተሞችን በበጀት መደገፍ ቢቻል፤
- የቄራ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲሻሻልና ዜጎች ንጽህናውን የጠበቀ ሥጋ እንዲመገቡ፤ እንዲሁም የመኖሪያ አካባቢዎች ከብክለት እንዲጠበቁ ለማድረግ የቄራዎች መሠረተ ልማት ግንባታ ድጋፍ ቢደረግ፤
- ቀደም ሲል የተገነቡ ቄራዎችን የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በጥናት የመለየትና ግኝቱን መነሻ በማድረግ ድጋፍ የመስጠት ሥራ ቢሰራ፤

## ሐ/ ከከተማ አስተዳደሮች ሚና አንጻር

- በአገልግሎት ስታንዳርዶቹ ላይ በፌዴራል እና በክልል ደረጃ የሚሰጠውን የአሰልጣኞች ሥልጠና የተሰተፉ አካላትን በመጠቀም በከተማ ደረጃ ሰፋ ባለ መልኩ ሁሉንም አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞችን ያሳተፈ ሥልጠና በመስጠት ቀልጠፋና ውጤታማ አገልግሎት እንድሰጡ የማድረግ ሥራ ቢሰራ፤

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የጸደቁ የአገልግሎት ስታንዳርዶች ሁሉም /7ቱም/ አገልግሎት ማቀላጠፊያ አጋዥ የሥራ መሣሪያዎች እንጂ ተጨማሪ አስገዳጅ ሸክም /extra ordinary burden/ አድርጎ አለማየት፤
- በፌዴራል ደረጃ በሚሰጠው ሥልጠና የሚሳተፉ አካላት እግረመንገዳቸውን የሚሳተፉ አካላት ባይሆኑ፤ የኮታ ጉዳይ ተደርጎ ባይታይ፤ በትክክል የሚመለከታቸው እና ከሥልጠና በኋላ በመስኩ አገልግሎት የሚሰጡ ቢሆኑ፤ የሥልጠናው ተሳታፊዎች ፕሮፋይላቸው /የተሟላ መረጃ ቢያዝ/፤
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ጸድቀው የወረዱት የአገልግሎት ስታንዳርዶች ሁሉም /7ቱም/ ከፈንድ ማግኘት አለማግኘት ጋር ማያያዝ ሳያስፈልግ እኩል ትኩረት እንዲያገኙ ቢደረግ፤ ሁሉም ባለቤት የሆነ ተቋማዊ አደረጃጀት ተፈጥሮላቸው ዜጎች እንዲገለገሉ ቢደረግ፤
- በየከተሞቹ የህዝብ መጸዳጃ እና የገላ መታጠቢያ ቤቶች መሠረተ ልማት በተገቢው ቦታ ላይ እንዲገነቡ በፀደቀው ስታንዳርድ መሠረት ተገቢ የሆነ መሬት ማዘጋጀት ቢቻል፤
- ከእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎት አንጻር ከባለድርሻ አካላት ጋር /ከኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ከውሃና ፍሳሽ ተቋማት፣ ወዘተ/ በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል አስገዳጅ የሆነ የህግ ማእቀፍ ቢኖር፤
- በሰፋፊ ከተሞች የሚታየውን ደረቅ ቆሻሻን የማጓጓዝ የአቅምና የተደራሽነት ፈተናን ለመቅርፍ የግልዘርፉን በማሳተፍ አገልግሎቱን ማቀለቀጠፍ ቢቻል፤

## 8. ማጠቃለያ

ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽ፣ ተደራሽ አገልግሎትን በፍትኃዊነትና በተጠያቂነት የማቅረብ ግቡ የዜጎችን እርካታ ደረጃ ከፍ በማድረግ መልካም አስተዳደርን ማስፈን ነው፡፡



## ምዕራፍ ሁለት፡- የከሚሴ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት የአገልግሎት አቅርቦት መልካም ተሞክሮ

### 1. መግቢያ

የይዞታ ማህደር በአግባቡ ማደራጀት እና ማስተዳደር በከተሞች ቀልጣፋ አገልግሎትን ለመስጠት፣ የነዋሪውን (የባለመብቱን) የይዞታ ደህንነት ለማጋገጥ፣ የኪራይ ሰብሳቢነትን አስተሳሰብና ተግባር ለመከላከል እና ለማስወገድ፣ የከተሞችን የገቢ አቅም ለማሳደግ እና የተገልጋዩን እርካታ ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህ ቁልፍ ተግባር በከተሞች በኩል በአግቦቡ ባለመከናወኑ የይዞታ ማህደሮች በተገቢው መንገድ የማይጠበቁበት እና የሚጠፉበት፣ ህገ-ወጥ የይዞታ ማህደሮች በህገ-ወጥ አግባብ ተደራጅው የሚመዘገቡበት፣ ማህደሮች እና ጠቃሚ ሰነዶች ተቀደው የሚጠፉበት፣ በአያያዝና አጠቃቀም ጉድለት ከአገልግሎት ውጭ የሚሆኑበት አግባብ በስፋት ይስተዋላል፡፡ በዚህም የተነሳ ህብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት የማያገኝ እና ለእንግልት ከመዳረጉም በላይ ይዞታውን በሚያስተዳድረው ተቋም እና በመንግስት አካላት ላይ እምነቱን በመጣል ረገድ በከፍተኛ ስጋት ውስጥ የወደቀበት ሁኔታ በስፋት ይስተዋላል፡፡ ይህንን ከፍተኛ ችግር ለመከላከል እና ለማስቀረት እንዲቻል አመለካከትን በመቅረፍ ረገድ የሚሰራው ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ በከተሞች የይዞታ ማህደር በአግባቡ የሚደራጅበትን እና የሚተዳደርበትን ዝርዝር ማኑዋል በማዘጋጀት እና ለፈጻሚው እና ለአመራሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት ብሎም አፈጻጸሙን መደገፍ እና መከታተል ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ይህ የመሬት ይዞታ ማህደር አደረጃጀት 1 እና አስተዳደር ማኑዋል ተዘጋጅቷል፡፡

በሁሉም ከተሞች ወጥነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት የይዞታ ማህደር አደረጃጀት እና አስተዳደር የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በይዞታ ፋይሎች አደረጃጀት፣ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ የሚታየውን ክፍተት በዘላቂነት መፍታት ነው። የዚህ የዳታቤዝ ሶፍትዌር ጥቅል አላማ የመሬት ይዞታ ማህደርን እና አስተዳደርን ወጥነት እና ግልጽነት ባለው ሥርዓት በአዲስ መልክ እንዲደራጅ በማድረግ የይዞታ ማህደር ደህንነት እንዲጠበቅ፣ በይዞታ ማህደር ላይ የሚፈፀም ህገወጥ ድርጊት እንዲወገድ እና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዩን እርካታ ከፍ ማድረግ ነው፡፡

i. የይዞታ ማህደሮች ወጥነት ባለው መልኩ በአግባቡ የሚደራጅበትን አሰራር ስርዓት በመዘርጋት በአዲስ መልክ እንዲደራጅ ለማስቻል፣
ii. የይዞታ ማህደሮች ደህንነት በተገቢው መንገድ እንዲጠበቅ ለማስቻል፣
iii. የማይፈለጉ የይዞታ ማህደሮች የሚመክኑበት እና የሚወገዱበትን ግልጽ አሰራር ለማስቀመጥ፣

iv. የይዞታ ማህደሮች ለአገልግሎት ሲፈለጉ ስርዓት ባለው መልኩ ወጭና ገቢ የሚሆኑበት ግልጽ አሰራር ለመዘርጋት፣

v. ቀልጣፋ እና ውጤታማ የሆነ የይዞታ ፋይሎች አደረጃጀትና አስተዳደር በመፍጠር ለተሻለ ቴክኖሎጅ ትግበራና ዘመናዊ የይዞታ አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ መነሻ/መሰረት ለመጣል እንዲቻል፣

## 2. የመሬት ልማት ማኔጅመንት የስራ ሂደት የአገልግሎት አቅርቦት ነባራዊ ሁኔታ

በማንዋል አሰራሩ ጊዜ የነበረውን ሁኔታ በተመለከተ፡-

- ባለጉዳይ ለአገልግሎት ፈልጎ ወደ መስሪያ ቤቱ በመጣ ገዜ ባለጉዳዩ ምን መረጃ አሟልቷል፣ ማን ባለሙያ አስተናግዶታል፤ እንዴትስ ተስተናግዷል፤ ለምን ያክል ጊዜ ቆይቶ ነበር የሚሉትን ነገሮች ለመለየት አስቸጋሪ ሁኔታን ፈጥሮ ተስተውሏል፡፡
- አገልገሎት ሰጪ ባለሙያው እነማን ባለጉዳዮች እንዳሉት፤ ምን አገልግሎት ፈልገው እንደመጡ፤ ባለጉዳዮችን በምን ሁኔታ እና በምን አይነት መልኩ ማስተናገድ እንዳለበት፤ እና የባለጉደዮችን መረጃ ለማግኘት ከፍተኛ የሆነመጨናነቅን ፈጥሮ እንደነበር ተስተውሏል፡፡
- አንድ ባለጉዳይ አገልግሎት ፈልጎ በመጣ ጊዜ ከማን ባለሙያ አገልግሎቱን ማግኘት እንደሚችል፤ ምን ቅድመ ሁኔታዎችንና መረጃዎችን ማሟላት እንዳለበት ከፍተኛየሆነ እንግልት በባለጉዳዮች ላይ ሲስተዋል ቆይቷል፡፡
- ባለሙያ ከባለሙያ የነበረው የእርስበርስ ግንኙነት በከፍተኛ ሁኔታ ሻክሮ እንደነበር ተስተውሏል፡፡
- አገልግሎት አሰጣጡ በጠቅላላ ህግና ስርአት ያልተከተለ እንደነበር እና ባለጉዳዮች በዘፈቀደ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ጉዳያቸው እንዲታይላቸው ከማይመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር ግብግብ ሲፈጥሩ ይስተዋሉ ነበር፡፡
- በጽ/ቤቱ የነበረው የአገልግሎት መስጫ የግዜ ስታንዳርድ እንደታፔላነት እንጂ እንደ መመሪያነት ሲያገለግል አለመታየቱ በደንበኞች ዘንድ ትችትን ሲያስተንግድ ተስተውሏል፡፡

## 3. የአገልግሎት አቅርቦቱን ለማዘመን /ለማሻሻል/ መነሻ የሆኑ ምክንያቶች

- ከግዜ ወደ ገዜ እየመጣ የነበረው የተገልጋይ ቁጥር መጠን መጨመር ተከትሎ የፈጠረው በመስሪያ ቤቱ ላይ የስራ ጫና እነደ ዋና ምክኒያት ይጠቀስ ነበር፤

- የባለጉዳይ መረጃ ለብልሽት እና መጥፋት መዳረጉ በመስሪያ ቤቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ የስራ መስተጓጎል ፈጥሮ ስለነበር ወደተሻለ የመረጃ አያያዝ እንዴት መሸጋገር እንዳለባቸው በመስሪያ ቤቱ በከፍተኛ የስራ ሀላፊዎች መሳ መዘየድ መጀመሩ፤
- ለባለጉዳዮች የተለያዩ ግልፅና ተአማኒነታቸው የተረጋገጠ እዉነተኛ የሆኑ ግብረመልሶችን (feed back) ለማዘጋጀትና ለመስጠት እየተፈጠረ የመጣው የስራ ውስብስነት ተጠቃሽ ምክኒያቶች ነበሩ፤

## 4. የአገልግሎት አቅርቦቱን ለማዘመን በተደረገው ሂደት ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የዘልማድ አሰራሩ በአንዳንድ ባለሙያዎች እና በተወሰኑ አመራሮች ዘንድ ተጽእኖ ፈጥሮ ስለነበር ለችግሩ ምን የተሻለ አማራጭ መፍጠር ይቻላል ችግሩንስ ምን ያክል ይታደገዋል በሚለው ላይ የተለያዩ ተግዳሮቶች ገጥመውናል፡፡ ከነዚህም መካከል፡-

### ሀ/ ከአመለካከት አንጻር

- የማንዋል አሰራሩ በከፍተኛ ሁኔታ ውስብስብ ከመሆኑ የተነሳ በቀላሉ ባቀራቢያው በሚገኙ ባሙያዎች ለችግሩ መፍትሂ መስጠት ይቻላል ተብሎ አለመታሰቡ፡፡
- የማንዋል አሰራር መመሪያው ከፌደራል ወይም ከክልል ይመጣላቸው ስለነበር በአንዳንድ የስራ ሀላፊዎችም በሶፍትዌር የታገዘ አሰራሩንም እንደዛው ማሰባቸው፡፡
- ከተጣያቂነት እና ከግልጸኝነት አንጻር ተያይዘው የሚመጡ ነገሮችን ሃላፊነት ከመውሰድ ጋር ተያይዞ በባለሙያዎች ዘንድ ፍራቻ መፍጠሩ፡፡

### ለ/ ከክህሎት አንጻር

- ብቁ የሆነ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሀይል ያስፈልጋል ተብሎ ይታሰብ ነበር፡፡
- ብዙሀኑ የነበሩት ባለሙያዎች የቴክኒካል ባለሙያ ባለመሆናቸው የተነሳ ስራዉ/የሚለማው የሶፍትዌር ቴክኖሎጅ ችግሩን ከስር መሰረቱ ይቀርፈዋል ብለው ለማሰብ መቸገራቸውና ሀሳቡ ሲቀርብ ስራውን በበጎ ጎን አለማየታቸው፡፡
- ቴክኖሎጅውን ተግባራዊ ለማድግ በሚሰጠው የክህሎት ተኮር ድጋፍ ላይ ትኩረት ሰጥተው አለመካፈል እና
- ባለሙያዎች በለማው ሶፈትዌር ተጠቅመው አገልግሎት በመስጠት ክህሎታቸውን ለማጎልበት/ለማሳደግ አለመሞከራቸው የመሳሰሉት ነበሩ፡፡

## ሐ/ ከግብአት አንጻር

- በመስሪያ ቤቱ የነበሩት ኮምፒውተሮች የተበላሹ በመሆናቸው፤ እና በባለሙያው ልክ እና የስራ ጫና ሁኔታ በቁሳቁስ ግብአት ደረጃቸውን የጠበቁ መሳሪያዎች ባለመኖራቸው ሲስተሙን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ተጽእኖ ፈጥሮብን ነበር፡፡
- ከዚህም ጋር ተያይዞ ቢሮዎችን እና ኮማፒውተሮችን ለማገናኘት የሚረዳ የኔትወርክ ገመድ ዝርጋታ አለመኖር፡፡
- ከዛ በፊት ስራውን ለማቅለል /ለማዘመን መሰል ስራዎች/ ቴክኖሎጅዎች አለመተግበራቸው እና ከሌሎች ከተሞች የተሻለ ተሞክሮ አለማየትና ልምድ ልውውጥ ለማድረግ ጥረት አለማድረጋቸው፡፡
- ሲስተሙን ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠይቃቸውን ግብአቶች በግዜና በወቅቱ አለማቅረብ ናቸው፡፡

## 5. ተግዳሮቶቹን ለመቅረፍ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- በመጀመሪያ ደረጃ ስለመስሪያ ቤቱ የአሰራር ስርአት ምን እንደሚመስል በጥልቀት ተገቢውን ጥናት በማካሄድ ልናለማው ላሰብነው ሶፍትዌር ባለሙያዎችን በማሳተፍ በስራ መደባቸው በመገኘት የሥራ እንቅስቃሴያቸው የሚፈልገውን አሰራር ለመተግበር በሀሳብ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ በባለሙያዎች ዘንድ አይነኬ ተደርገው ይታሰቡ የነበሩ ሃሳቦችን ማቃለል እንደሚቻል በተግባር ያሳየንበት ሁኔታ በባለሙያዎች ዘንድ ለስራው ያለቸው ፍላጎት እንዲጨምር ረድቶናል፡፡
- በተለያዩ ጊዜያት እየለማ ያለውን ሶፍትዌር ያለበትን ደረጃ እና እንዴት እየለማ እንደሆነ ለባለሙያው ገለፃ በማድረግ የተሰማቸውን ሀሳብ እንደግብአት በመጠቀም ረገድ የአመለካከት እና የፍላጎት መጠን እንዲጨምር በመስራት ተፈጥሮ የነበረውን የአመለካከት ችግር ለመቅረፍ ሞክረናል፡፡
- ከግብአት አንጻር በመስሪያቤቱ ላይ ሲስተዋል የነበሩ ችግሮች ለመቅለፍ በግላችንም ጭምር የሚያሥፈልጉ ግብአቶችን በማቅረብ ከፍተኛ ድጋፍ ለማድረግ ሞክረናል፡፡
- መረጃዎችን ከማደራጀት አንጻር ተስተውሎ የነበርውን ችግር ለመቅረፍ ከውላችን ውጭ የስካነር ማሽን በማቅረብ ተጨማሪ የሰው ሀይል በመቅጠር የወሰድነዉ እርምጃ መረጃው በአጭር ግዜ ውስጥ እንዲደራጅ እና ወደ ትግበራ እንዲገባ ለማስቻል ከፍተኛ ጥረት እና እገዛ አድርገናል፡፡
- ከክህሎት አንጻር ተፈጥሮ ለነበረው ችግር መፍትሄ ለመውሰድ እንደየትምህርት ደረጃቸው ለባለሙያዎች ተገቢውን የኮመፒውተር የክህሎት ስልጠና በመስጠት የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ተችሏል፡፡

## 6. አገልግሎት አቅርቦቱ አሁን ያለበት ደረጃ/ሁኔታ

- በዋናነት የባለ ይዞታ የፋይል ማህደር በዳታቤዝ ሶፍትዌር ታግዞ ተደራጅቷል፡፡
- ባለጉዳይ ከመረጃ ደስክ እስከ ስራ አስኪያጅ ድረስ የሚያደርገው የአገልግሎት እንቅስቃሴ በኮምፒውተር የታገዘ እንዲሆን ተችሏል፡፡
- ባለጉዳይ በወጣው የዜጎች የአገልግሎት የጊዜ መስጫ ቻርተር አገልግሎት እያገኙ ይገኛሉ፡፡
- ባለሙያዎች በሰሩት የስራ መጠን መሰረት ተገቢውን የBSC ውጤት እያገኙ ይገኛሉ፡፡
- ባጠቃላይ በመስሪያቤቱ ይስተዋሉ የነበሩ የተዝረከረኩ የአሰራር ስርአቶች ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ ተቀርፈው ይስተዋላሉ፡፡

### ሀ/ የፊትለፊት አገልግሎት የደንበኞች መስተንግዶን በተመለከተ (የደንበኞች አቀባበል፣ የወረፋ አያያዝ የማረፊያ ቦታ ዝግጅት) ጋር ተያይዞ

- መረጃ ደስኩ ራሱን ችሎ እንዲደራጅ በማድግ ለደንበኞች ምቹ የሆነ የመቀበያ ቦታ እንዲኖ እና ለደንበኞች ምቾትን በሚፈጥር ሁኔታ መረጃን እንዲያገኙ አስችለናል፡፡
- የወረፋ አያያዙን በተመለከተ ባለጉዳዩ በያዘው መረጃ መሰረት እና በሚፈልግው የአገልግሎት ፍላጎት በመነሳት ለሚመለከተው ባለሙያ የባለጉዳይ መልዕክት በመላክ ወረፋ የሚይዝበትን ሁኔታ አመቻችተናል፡፡
- ለደንበኞች ማረፊያ የሚሆኑ ደረጃቸውን የጠበቁ ወንበሮች በማቅረብ ባለጉዳዩ ወረፋ እስኪደርሰው ድረስ በትእግስት የሚጠብቅበት ሁኔታ እንዲፈጠር አስችለናል፡፡

### ለ/ የመረጃ ዴስኩ ቁልፍ ተግባራት የሚባሉት

- በዋናነት በመስሪያቤቱ ዉስጥ የሚሰሩ ተግባራትን ለይቶ እንዲያውቅ ይፈለጋል።
- በየሂደቱ ለሚሰሩ ተግባራት ለባለጉዳዮች የሚያሥፈልጉ መረጃዎችን እንዲያውቅ ይፈለጋል።
- የባለገዳዮችን እንቀስቃሴ ከሲስተም ውሰጥ ሆኖ እንዲከታተል ይፈለጋል።
- ወደ ስራ ገበታቸው የገቡና ያልገቡ ባሙያዎችን ኦንላየን ሆኖ በመለየት መከታተል ይኖርበታል።

### ሐ/ የተገልጋዮች እና የአገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎች የቀጥታ ግንኙነትን በተመለከተ

- ደንበኞች ለአገልግሎት ፈልገው በመጡ ጊዜ በመረጃ ዴስኩ ምዝገባ ከተካሄደላቸው እና ጉዳዩን ወደሚመለከተው ባለሙያ ሲመሩ /ሲላኩ/ ሲተላለፉ ደንበኛው ከመድረሱ በፊት ባለሙያው የተላከለት ባለጉዳይ ምን መረጃዎች አሉት በደንበኛው መረጃዎች ላይ ምን ተግባራቶች ተከናውኖ ያውቃል የሚሉትን የደንበኛውን መረጃ ምልከታ በማድረግ

ደንበኛው ለምን አገልግሎት ፈልጎ መጣ የሚሉትን አሁን ከተመዘገበበት የአገልግሎት ፍላጎት በመነሳት ከደንበኛው ጋር በቀላሉ እንዲግባቡ ረድቷቸዋል።

- ደንበኞች የያዙትን መረጃ እና በዳታቤዝ ሶፍትዌር ያሉትን መረጃዎች በማመሳከር ለደንበኞች ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት አስችሏል።

### መ/ የአገልግሎት አቅርቦቱን ለማቀላጠፍ ጥቅም ላይ የዋሉ ቴክኖሎጅዎች/ሶፍትዌሩን ጨምሮ

- Miccrosoft excel
- Microsoft word
- Customer handling and land administration system

## 7. የለማበት ሁኔታ

የከተማ መሬት ይዞታ ፋይል አደረጃጀትና አስተዳደር ማኑዋሉን ለማዘጋጀት እንደመነሻ የተወሰደው የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ፖሊሲው ሲሆን በፖሊሲው ላይ እንደተመላከተው የይዞታ አስተዳደር ማህደር ተገቢው ምዝገባ ተደርጎለት እና በአግባቡ ተደራጅቶ ደህንነቱ አስተማማኝ በሆነ አኳኋን መቀመጥ ያለበት እና የይዞታ ማህደር ለአገልግሎት ሲፈለግም ግልጽ፣ ቀልጣፋ እና ተጠያቂነት ባለበት መንገድ መከናወን እንዲችል የአሰራር ስልት ሊቀመጥለት እንደሚገባ ያስቀምጣል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት የህግ ማዕቀፎች ላይ የተቀመጡ የመሬት ባለቤቱንና የተጠቃሚዎችን መብትና ግዴታ በተገቢው መንገድ ለመወጣት እንዲቻል ወጥነት ያለውና ተጠያቂነት ያለው የይዞታ ፋይሎች አደረጃጀትና አስተዳደር ወሳኝነት አለው፡፡ ከዚህም አንፃር በከተሞች በተግባር እየታየ ያለው የይዞታ ማህደር በከፊል ወይም በሙሉ መዛባት፣ መሰወር እና መጥፋት ከተገልጋዮች በተደጋጋሚ የሚሰማ እሮሮ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡

ይህም የሆነው ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ብቃት ያለው የሰው ኃይልና የአሰራር ስርዓት ያለመፈጠር በመሆኑ የፋይሎቹ አስተዳደርና አጠቃቀም ለኪራይ ሰብሳቢነት እና ህገ-ወጥ ድርጊት እንዲጋለጡ አድርጎታል፡፡ በዚህ በከተሞች የአልግሎት አሰጣጥ ስርዓቱን የሚያቃውስ ብቻ ሳይሆን ዜጐች በያዙት ሰነድ እና ባላቸው ማህደር ህጋዊነት እና ደህንነትን በተመለከተ በተቋማቱ ላይ እምነት እንዳይኖራቸው በማድረግ እየፈጠረ ያለው ተጽዕኖ በቀላሉ የሚገመት ባለመሆኑ ችግሩን ለማስቀረት እንዲቻል ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

## 8. የአገልግሎት አሰጣጡ ከማዋል ወደ ሶፍተዌር ኔትዎርኪንግ /አውቶሜሽን/ የተሸጋገረበት ሁኔታ

- በስርአቱ ያልተመዘገቡና ተበታትነው ያሉ መረጃዎችን የመሰብሰብ ተግባር፤
- መተግበሪያውን ከመጠቀማችን በፊት የነበሩ ይዞታ ማህደሮችንና ተያያዥ መረጃዎችን ወደ ሶፍትኮፒ የመቀየር ተግባር ተከናውኗል፤
- ኮምፒውተችን በኔትወርክ ሲስተም የማገናኘት ተግባር፤
- መተግበሪያውን ባሉት ኮምፒውተሮች ላይ የመጫን ተግባር፤
- የመረጃ ቋት ማስተካከልና ኮምፒውተሮችን የማገናኘት ተግባር፤
- በሶፍትኮፒ የነበሩና የተዘጋጁ መረጃዎችን ወደ መተግበሪያው የመረጃ ቋት የማስገባት ተግባር፤
- ለየባለሙያው አካውንት በመክፈት ለተመደበበት የስራ መደብ አገልግሎት እንዲሰጥ ስልጠና የመስጠት ተግባር፤

## 9. የአገልግሎት የግዜ ስታንዳርድ አመዘጋገብን በተመለከተ

ደንበኞች ለአገልግሎት ተመዝግበው ጉዳዩን ወደሚመለከተው ባለሙያ ከተላኩ በኋላ ባለሙያው ለባለጉዳዩ አገልግሎት ለመስጠት ካስጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ጨረሰበት ያለውን የጊዜ ልዩነት በመቁጠር በዳታቤዙ ከተመዘገበው ጊዜ ጋር በማወዳደር ለባለሙያው የማስታወሻ ደውል/ምልክት በመስጠት የተቀናጀ ነው።

## 10. የአገልግሎት አሰጣጡ ከማንዋል ወደ አውቶሜሽን በመሸጋገሩ የሚጠበቁ ውጤቶች

### ሀ/ ከኪራይ ሰብሳቢነት እና አመለካከት ከማስወገድ አንጻር

- በአንዳንድ ባለሙያዎች ከደንበኞች የተለየ ፍላጎት በማሳደር ከአንዳንድ ባለሙያዎች ጋር በመመሳጠር ፋይላችሁ ጠፋ፣ ያልተሟላ መረጃ ነው ያቀርባችሁት፣ እንዲሁም ምንም አይነት ስራ ሳይዙ ራሳቸውን በስራ የተጠመዱ በማስመሰል ደንበኞችን ያመላልሱ የነበሩ ባለሙያዎችን ከተግባራቸው እንዲታረሙ መንገድ ፈጥሯል፡፡
- እነማን ባለሙያዎች በስታንዳርዱ መሰረት ባለጉዳዮችን እያስተናገዱ ነው የሚለውን በቀላሉ ለመረዳት በማስቻሉ ከዚህም ጋረ ተያይዞ ይፈጠር የነበረዉየባለሙያዎች የእርስበርስ አለመግባባትን ለመፍታት ሁኔታዎች ተመቻችተዋል፡፡
- ደንበኞች በያዙት መረጃ መሰረት በቅድሚያ ማግኘት ያለባቸውን እንዲያገኙ አስችሏል፡፡
- ባለጉዳዮች ለመስሪያ ቤቱ እንግዳ ከመሆናቸዉ ጋር ተያይዞ ማን ባለሙያ ምን አገልግሎት ይሰጣል የሚለውን ስለማያውቁ ይደርስባቸው የነበረውን እንግልት ማስወገድ ተችሏል፡፡

- ፋይላችሁ ያልተሟላ ነዉ/ለጊዜው አተገኘም እየተባሉ ይደርስባቸው የነበረውን እንግልት ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ ተቀርፏል ማለት ይቻላል፡፡

### ለ/ የአገልግሎት አቅርቦቱን ቀልጣፋ/ውጤታማ እና ግልጽ ከማድረግ አንጻር

- በመስሪያቤቱ የሚሰሩ ተግባራትን በማን ተሰሩ መቼ እና እንዴት ተሰሩ የሚለውን በቀላሉ ከሪከርድ ማህደር በማየት ግልጽ የሆነ አሰራር እንዲሰፍን መንገድ ፈጥሯል፡፡
- ለዜጎች አገልግሎት ለመስጠት በሚወጣዉ የጊዜ ስታንዳርድ መሰረት ለደንበኞች ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ አይተኬ ሚና ተጫውቷል፡፡
- ለባለሙያዎች የባለጉዳዮችን መረጃ ለአገልገሎት መስጠት በሚያስችል ሁኔታ በመደራጀቱ በፍጥነት አገልገሎት ለመስጠት በማስቻሉ ቀልጣፋ አገልግሎት ተፈጥሯል፡፡

### ሐ/ የሰው ሀይሉን በአግባቡ ከመጠቀም አንፃር /የስራ ጫና ከመቀነስ አንጻር

- ማን ባለሙያ ወደስራ ገበታው ሰአቱን ጠብቆ ለስራ ወደሲስተም ገብቷል በምን ሰአት ከሲስተም ወጥቷል የተላኩለትን ባለጉዳዮች በምን ሁኔታ እያስተናገደ ነው የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ አስችሏል።
- በተመሳሳይ የስራ መደብ ላሉ ባለሙያዎች ተመሳሳይ ጉዳይ ያላቸውን ደንበኞች በቀላሉ በመረጃ ጠቋሚው መሰረት በመመራት እና ለባለሙያዎች እኩል የባለጉዳይ ፍሰት እንዲፈጠርና የስራ ጫናው ሚዛናዊ እንዲሆን በማስቻል ከፍተኛ ውጤት አስመዝግቧል።

## 11. የአገልግሎት አሰጣጡ ከማንዋል ወደ ሶፍትዌር ኔትዎርኪነግ/አውቶሜሽን በመሸጋገሩ በመጡ ለውጦች ያሉ አስተያየቶች

### 11.1. የዜጎች ግብረመልስ ምን ይመስል ነበር?

ያለማነውን ሶፍትዌር የሙከራ ትግበራ ለማድረግ ባዘጋጀነው የምረቃ መድረክ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጋባዥ በማድግ ከተሳታፊዎች የተለያዩ አስተያየቶችን በመስማት ለቀጣይ ስራዎቻችን ስንቅ የሚሆኑን ሀሳቦችን በመቀበል፤ አሁን ባለማነው ሶፍትዌርም የተለያዩ አስተያየቶችንም ሰጥተውናል፡፡

- አሁን የተሰራው ስራ ከበፊቱ የተሻለ አገልግሎት እንድናገኝ በተደረገው ጥረት እያመሰገንን ወደፊት በሚሰሩ የልማት ስራዎች ህብረተሰቡን ተሳታፊ እንዲያደርጉችው እና አሁን ለተሰራው የቴክኖሎጂ ስራ የሚያስፈልጉትን የቁሳቁስ ድጋፎች እንደሚያበረክቱ አስተያየት ሰጪዎቹ ተናግረዋል።

- የለማው ሶፍትዌር ይደርስባቸው የነበረውን እንግልት እንደቀረፈው በመግለጽ የለማው ሶፍትዌሩ ለመረጃዎቻቸው የሚሰጠውን ጥበቃ ምን ያክል እንደሆነ ስጋታቸውን በመግለጽ በቀጣይ እንደነዚህ አይነት ወጣቶችን በመጠቀም ብዙ የከተማችንን ችግር ለመፍታት ተባብረው እንደሚሰሩ ሀሳባቸውን ሰጥተዋል።
- ስራው በአካባቢው ወጣቶች ተሰርቶ በመበርከቱ እንደ ታሪክ በመያዝ በቀጣይ እንደነዚህ አይነት የፈጠራ ባለቤት ወጣቶችን በምጠቀም በተለያዩ መስሪያ ቤቶች የሚስተዋሉ የአሰራር ግድፈቶችን በጋራ በመሆን ችግሮችን ለመቅረፍ የበኩላቸውን ድጋፍ በማድረግ እንደሚወጡ አስተያየት ሰጪዎቹ ተናግረዋል፡፡

## 11.2. የተጠቃሚ ተቋም ግብረመልስ

- አይነኬ ተደርገው ታስበው የቆዩ የአሰራር ስርአቶች በቀላሉ በአካባቢው በሚገኙ የስራ እድል ተጠቃሚዎች በሆኑ ወጣቶች የቴክኖሎጅው ስራ ለትግበራ በመብቃቱ ያላቸውን ምስጋና እና አክብሮት በመግለጽ በቀጣይ ደንበኞች በከፍተኛ ሁኔታ ቅሬኔ እና እንግልት በሚፈጥሩባቸው መስሪያ ቤቶች በኛ መስሪያቤት ያስለማነውን የቴክኖሎጂ ስራ እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመመልከት/በመውሰድ አሰራራቸው በዘመናዊ የቴክኖሎጅ ሥራ እንዲደግፉ ለማድረግ ከፈጠራ ባለቤቶቹ/ባለሙያዎቹ ጋር በቅረበት በመስራት ለደንበኞቻቸው ቀልጣፍ አገልግሎት በመስጠት እንዲሁም ዘመኑ የቴክኖሎጂ በመሆኑ አሰራራቸውን በቴክኖሎጂ በመታገዝ ለደንበኞቻቸው የተሻል አገልግሎት እንዲሰጡ በአቻዎቻቸው የከተማው ሴክተሮች ልምድ እንዲወስዱ በማስቻል አሰራራቸውን እንዲያዘምኑ ጥረት እንደሚያደርጉ አጽንኦት ገልጸዋል።
- የለማው ሶፍትዌር የነበረውን የአሰራር መዝረክረክ እና መጓተት በመታደጉ ለስራችሁ ከሚገባው ዋጋ በታች ከፍለን እንዲህ የዘመነ ስራ ስላበረከታችሁልን በቀጣይ ስራችሁን እንደ መልካም ጅማሮ በመያዝ ወደ ሌሎች ከተሞች ለማሸጋገር እና ለማስተዋወቅ በምታደርጉት የሽግግር ሂደት የበኩላችንን ድጋፍ እንደምናደርግላችሁ ቃል እንገባላችኋለን በማለት ገልጸዋል።
- አሁን በለማው ሶፍተዌር በመታገዝ ለባለሙያዎች ምቹ የስራ ሁኔታን ከመፍጠር ባሻገር ግልጽ የሆነ አሰራር እንዲኖር ከፍተኛ ዋጋ እንደከፈለላቸው የሂደት መሪ ባለሙያዎች አክለው ተዘናግረዋል፡፡
- በሰራችሁልን የቴክኖሎጂ ስራ ተቋማችንን የመልካም ተሞክሮ መቀመሪያ እንዲሆን በማስቻላችሁ ስራችሁ ደምቆ እንዲታይ በተቋማችን ሙሉ በሙሉ ተገባራዊ በማድረግ ግንባር ቀደም ደንበኞቻችሁ በመሆን በቀጣይ በምንሰራው ስራ ድጋፋቸው እንደማይለይ ገልጸውልናል፡፡

## 12. የለማው ሶፍትዌር በቀጣይ የአገልግሎት አቅርቦቱን እና የመረጃ አያያዙን ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ግልጽ ከማገረግ አንጻር ለከተሞች የሚኖረው ፊይዳ

### 12.1.1. የአገልግሎት አቅርቦቱን ቀልጣፋ ውጤታማ እና ግልጽ ከማድረግ አንጻር የሚኖረው ፋይዳ

- በመስሪያቤቱ የሚሰሩ ስራዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ስታንዳርድ መሰረት ለመስጠት በማስቻሉ ለደንበኞች ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙ አስችሏል፡፡
- የሚሰሩ ስራዎችን በማን ባለሙያ፣ በምን ሰአት፣ እንዴትስ ለባለጉዳዩ አገልግሎቱ ተሰጥቱቸዋል የሚለውን በቀላሉ ለመረዳት በማስቻሉ ግልጸኝነት የተሞላበት አገልግሎት ለመስጠት አስችሏል፡፡

### 12.1.2. የመረጃ አያያዙን ቀልጣፋ ውጤታማ እና ግልጽ ከማገረግ አንጻር ለከተሞች የሚኖረው ፊይዳ

- በአንዳንድ ስነምግባር ብልሹ በሆኑ የመዝገብ ቤት ባሙያዎች ከደንበኞች የተለየ ፍላጎት ከመያዝ ጋር በተያያዘ ይደርስባቸው የነበረው እንግልት ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ ችግሩን በመቅረፍ ግልጽ የሆነ አሰራር እንዲኖር አስችሏል፤
- ደንበኞች ለአገልግሎት ፈልገው በመጡ ጊዜ መረጃችሁ ከመዝገብ ቤት ይምጣ /ይፈለግላችሁ ተብለዉ ይወስድ የነበረው የጊዜ መጉተት መቶ በመቶ በሚባል ሁኔታ ችግሩ እንዲቀረፍ በማስቻል ፈጣን ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት ለደንበኞች እንዲያገኙ አስችሏል፤
- አንድ ደንበኛ ለአገልግሎት በመረጃ ደስኩ ተመዝግቦ ወደሚመለከተው ባለሙያ ተመርቶ/ተልኮ አገልግሎት ሲያገኝ የተደረገለትን መስተንግዶ በማን ምን አገልግሎት ተሰጥቶታል ለምን ያክል ጊዜ አገልግሎት እየተደረገለት ቆይቱል የሚሉትን ሁነቶች በግልፅ ለመረዳት በማስቻሉ ግልጽ የሆነ አሰራር እንዲኖር አስችሏል፡፡
- በጠቅላላ በመስሪያቤቱ ይስተዋሉ የነበሩ የአሰራር ግግፊቶችን በማስወገድ የተሻለ የደንበኛ አገልግሎት እና የመረጃ አያያዝ እንዲኖር አስችሏል፤

## 13. ማጠቃለያ

**የከሚሴ ከተማ አስተዳደር እና** የከሚሴ ከተማ ኢንተርፕራይዝ ቢሮ በጋራ በመሆን በፈጠሩልን የስራ እድል ተጠቃሚነት መሰረት የመጀመሪያችን የሆነውን የፈጠራ ስራችንን በማበርከት የተሻለ የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲዘረጋ እና የደንበኞች ፋይል/መረጃ ዘመኑ በደረሰበት ቴክኖሎጂ ታግዞ እንዲደራጅ በማስቻል ደንበኞች ሳይንገላቱ ተገቢውን አገልገሎት እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ እና ሀገራችን ኢትዮጵያ በምታደርገው የቴክኖሎጂ ሽግግር የበኩላችንን አስተዋጽኦ ለማበርከት ተግቶ በመስራት እና የማህበረሰባችንን ችግር በማየት ለችግሩ መፍትሄ የሆኑ ሀሳቦችን በቴክኖሎጂ

ታግዘው መፍትሄ እንዲያገኙ በማስቻል ራሳችንን እና ማህበረሰባችንን ለማገልገል ተግን እየሰራን እንገኛለን፡፡

## 13.1. በቀጣይ ሶፍትዌሩን /ቴክኖሎጂውን/ ካለማው አካል ጋር ሊኖረው የሚችለው የግንኙነት እና የድጋፍ አግባብ

- ሶፍተዌራችንን ለመጠቀም ለሚፈልጉ ለማኛውም ሕጋዊ ድርጅቶች ህጉ በሚፈቅደው አግባብ ከባለመብቶቹ ህጋዊ ፈቃድን በማግኘት ህጋዊ ውል ፈጽሞ ማስተግበር ይቻላል፤
- ማንኛውንም የምንሰራቸውን ስራዎች በውላችን እና በተጠቃሚ ተቋሙ ትእዛዝ መሰረት በባለሙያዎች ተገምግሞ በማስረከብ ሙሉ የአገልግሎት ዋስትናዎችን እንሰጣለን፤
- የተለያዩ የአሰራር ዘይቤዎች በሚፍጠሩ ጊዜ ለደንበኞቻችን ተገቢውን የአሰራር ማንዋል ማሻሻያ በማደረግ ድጋፍ እንሰጣለን፡፡

## 13.2. የሲስተሙ ክፊል ገጽታዎች በፎቶ



































## 13.3. ስለ ድርጅታችን አጠር ያለ ገለጻ

መሀመድ አሚን አባቡ እና ጓደኞቻቸው የሶፍትዌር ዲዛይን ልማትና ትግበራ ህብረት ሽርክና ማህበር በሚል መጠሪያ ስም በጥር-2009 ዓ.ም በሶፍትዌር ስራ እናተያያዥ የኮምፒውተር ስራዎች የስራ ዘርፍ በመደራጀት መቀመጫችንን ከሚሴ ከተማ በማድረግ ወደ ስራ የገባን ሲሆን ከስራዎቻችንም መካከል በከሚሴ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ከአገልግሎት አሰጣጡ እና ከፋይል አደረጃቱ ጋር በተያያዘ  ይስተዋሉ የነበሩ የአሰራር ግድፈቶችን ለመቅረፍ በተደረገው ሂደት ላይ የአገልግሎት ጽ/ቤቱን የአሰራር ሂደት በማጥናትና ለስራው መፍትሄ ሊሆን የሚችል ሶፍተዌር በማጎልበት ለችግሩ መፍትሄ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ በማስገባት የአገልግሎት አሰጣጡን እና የመዝገብ አያያዙን እንዲዘምን በማስቻል በከተማችን ብሎም በሀገራችን ኢትዮጵያ እወቅናን አግኝተን ስራችንን እያስተዋወቅን እንገኛለን፡፡

ሆኖም ግን በከተሞች በኩል የባለ መብቱን (የባለ ይዞታውን) ማህደር ወጥነት ባለው መልኩ እና በአግባቡ በቴክኖሎጂ ታግዘው ባለማደራጀታቸው የይዞታ ማህደሮች በተገቢው መንገድ የማይጠበቁበት እና የሚጠፉበት፤ ህገ-ወጥ የይዞታ ማህደሮች በህገ-ወጥ አግባብ ተደራጅው የሚመዘገቡበት፤ ማህደሮች እና ጠቃሚ ሰነዶች ተቀደው የሚጠፉበት፤ በአያያዝና አጠቃቀም ጉድለት ከአገልግሎት ውጭ የሚሆኑበት አግባብ በስፋት ይስተዋላል፡፡ በዚህም የተነሳ ህብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት የማያገኝ እና ለእንግልት ከመዳረጉም በላይ ይዞታውን በሚያስተዳድረው ተቋም እና በመንግስት አካላት ላይ እምነቱን በመጣል ረገድ በከፍተኛ ስጋት ውስጥ የወደቀበት ሁኔታ በስፋት ይስተዋላል፡፡

ይህንን ከፍተኛ ችግር ለመከላከል እና ለማስቀረት እንዲቻል አመለካከትን በመቅረፍ ረገድ የሚሰራው ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ በከተሞች የይዞታ ማህደር በአግባቡ የሚደራጅበትን መንገድ ለማመቻቸት እና ከተሞች ዘመኑ በደረሰበት ቴክኖሎጂ ታግዘው ስራቸውን የሚከዉኑበትን አማራጭ በመፍጠር ወደተሻለ የአደረጃጀት እድገት ደረጃ እንዲሸጋገሩ የበኩላችንን ድጋፍ እያበረከተን እንገኛለን።

## ምዕራፍ ሶስት፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር አገልግሎቶች ስታንዳርድ ትግበራ ተሞክሮ

### 1. መግቢያ /Introduction/

#### 1.1. ታሪካዊ ዳራ /Background Statement/

ከኢትዮጵያ ከተሞች መካከል ትልቋና አንዷ አዲስ አበባ ከተማ ስትሆን የአፍሪካ ህብረት መቀመጫና የአህጉሪቱ መዲና፣ የአፍሪካ ትልቁ የንግድ ወይም ገበያ የሚገኝባት፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማቶች ማስፋፊያ፣ የዓለም አቀፍ ዲፕሎማቶች መቀመጫ፣ በሀገራችን ከ5 ሚሊዮን ህዝብ በላይ የሚኖሩባት ከተማ እንደመሆኗ መጠን የአደጋ ስጋት ደህንነቷ የተጠበቀ መሆን የግድ ይሆናል፡፡

ከተማዋ የጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ለተለያዩ የሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች የተጋለጠ በመሆኑ አስቀድሞ የአደጋ ስጋት መቀነስ፣ አደጋዎች ሲከሰቱም የምላሽ የመስጠት፣ የቅድመ ሆስፒታል ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት፣ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታና መልሶ ማቋቋም አገልግሎቶችን መስጠት ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም የሚሰጡ አገልግሎቶች ከጥራትና ከተደራሽነት አንጻር አለማቀፍ ስታንዳርዶችን በ5 ኪሎ ሜትር ሬዲዩስ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ሳይንሳዊ ዑደቶችን የተከተለ እና ዘመናዊና ወቅታዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ከአለም አቀፍና ከተማዋ ተጨባጭ ሁኔታ የተገናዘበ የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ምላሽ፣ የአደጋ ተጎጂዎችን በአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታን መስጠት እና በዘላቂነት መቋቋም የሚገባቸውን የማቋቋም ሂደታዊ ተግባሮችን መፈጸም ይገባል፡፡ ከተማው ሊከሰቱ የሚችሉ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ክስተቶችን ለመቀነስ መጠነ ሰፊ የአደጋ ስጋት ቅነሳና ዝግጁነት፣ አደጋዎች ሲከሰቱም በቦታው ፈጥኖ በመድረስ በህይወትና በንብረት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የአደጋ ምላሽ እና በአደጋዎች ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ለሚፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታን መልሶ የማቋቋም ወይም መልሶ መገንባት አገልግሎቶችን በአደጋ ስጋት ስራ አመራር ሳይንሳዊ ዑደት እና አደረጃጀት መሰረት እንዲሰጥ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህም ምክንያት የከተማዋን ነባራዊ ሁኔታ፣ ከዕድገቷና ከህዝብ ፍላጎት ጋር የተመጣጠነ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓትና አደረጃጀት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ በ1926 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ስሞችና አደረጃጀቶች ለ87 ዓመታት አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶ ከተማ አስተዳደሩ በየጊዜው በሚያደርጋቸው የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትና አወቃቀር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእሳትና የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽንን በከተማው የአስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ 64/2011 ማቋቋም ችሏል፡፡ ኮሚሽኑ ካለው የከተማው የቆዳ ስፋት፣ የህዝብ ብዛት፣ የኢንቨስትመንት መስፋፋትና ፈጣን የልማት ዕድገት

እና የኢኮኖሚያዊ ማዕከላዊነት አንጻር የአደጋ ስጋቶችን መቋቋም የሚያስችል አቅም በመፍጠር የከተማዋን የልማትና የእድገት ጉዞ ደህንነትና ዘላቂነትን ለማረጋገጥ በየወቅቱ የሚታዩትን የአደረጃጀትና የአሰራር ክፍተቶችን፣ የተግባርና ሃላፊነት መደራረብን፣ የስራ ባህሪይ ተመጋጋቢነትን፣ የስልጣንና ተግባር ግልጽነትን፣ የጥቅም ግጭትን፣ የበጀት/ሀብት ቁጠባን፣ የቁጥጥር አድማስን፣ የከተማዋን ነባራዊ ሁኔታ እና ስትራቴጂ በጠበቀና የተቋሙን ልዩና አለማቀፋዊ የሥራ ባህሪ እና ዲሲፕሊን ከግምት ውስጥ ያስገባ የከተማዋን ነዋሪ ህዝብ እርካታ ሊጨምርና ተጠያቂነትን ሊያረጋግጥ የሚችል አልፎ ተርፎም ብቃት ያላቸው የአደጋ ሰራተኞችንና ባለሙያዎችን በማበራከት ውጤታማና ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት የሚያስችል የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር አገልግሎቶች ስታንዳርድ ትግበራ ተሞክሮ መነሻ ሰነድ ለኢትዮጵያ ከተሞች ትብብር መድረክ እንደሚከተለው ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

## 1.2. መነሻ ሁኔታዎች /ቀደም ሲል የነበሩ ችግሮች/

የተቋሙ ውስጣዊ ችግሮች ከአደረጃጀት፣ ከአሰራር፣ ከግብዓትና ከሰው ሀይል አንጻር እና ውጫዊ ችግሮች ከፖለቲካ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከማህበራዊ፣ ከከባቢያዊ፣ ከህግ ማቀፍና ከቴክኖሎጂ አንጻር በተቋሙ አገልግሎቶችና ስታንዳርድ እና በተገልጋዩ ፍላጎትና እርካታ በመጨመር ላይ ያሳደሩትን ተጽዕኖ የቃኘ ወቅቱ የሚጠይቀው ዋና ዋና ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ነበሩ፡፡ የእሳት አደጋ ስጋት ስራ አመራር መገለጫ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 92 እና 93 የሚመነጭ ብሄራዊ የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ሆኖ መነሻና መድረሻው የህብረተሰቡ ከአደጋ መጠበቅ እና የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ የዝግጁነትና ምላሽ፣ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታና በቋሚነት መልሶ መቋቋም ፍላጎት መኖር ነው፡፡ ስለሆነም ከአዲስ አበባ ከተማ እድገት ጋር ተያይዞ የሚመጡ በርካታ የአደጋ ደህንነት ስጋቶች ያሉ ሲሆን ለችግሮቹ ደረጃውንና ወቅቱን የጠበቀ ፈጣን ምላሽ ካልተሰጠ በስተቀር የህብረተሰቡ ደህንነት ለአደጋ እንደሚጋለጥ አያጠራጥርም፡፡ አደጋዎች ከመከሰታቸው በፊት ለመከላከልና በየጊዜው ለሚከሰቱ አደጋዎችም ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ደረጃውን የጠበቀ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር አደረጃጀት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሰረት በተቋሙ የሚታዩትን የማስፈጸም አቅም በመገንባትና የአደረጃጀት ክፍተት በመፍታት የህብረተሰቡ ደህንነት መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ተቋም የሚታዩ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ከነባራዊ ሁኔታ በመነሳት  እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

## 1.3. የተሞክሮው ዓላማዎች

### ሀ/ ጥቅል ዓላማ

የአዲስ አበባ ከተማ የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን በአዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ኃላፊነቶች ተግባራዊ በማድረግ የተሠሩ መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመር ለተቋማችን ለሌሎች ተቋማትን ጭምር በማስተላለፍ ሥራዎቹ ከዚህ በበለጠ እንዲሠሩ መልዕክት ማስተላለፍ፣ ልምድ የሚወስዱ አካላት ጥራት ያለው ውጤታማና ቀልጣፋ አገልገሎት በመስጠት የህብረተሰቡን የእርካታ ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችለውን ዕሴት የሚጨምሩ ጊዜን የሚያሳጥሩ በአደጋ ስጋት ስራ አመራር የተቃኘ የአሰራር ስርዓት ልምድ እንዲደረግበት ነው፡፡

### ለ/ ዝርዝር ዓላማዎች

- የነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳን ትንተና መነሻ በማድረግ ሊያሰራ የሚችል ልምድ ልውውጥ ማድረግ፣ ግልጽነትን በሚፈጥር መልኩ ለይቶ ማስቀመጥ፣
- የአሰራር ማዕቀፎች ለማዘጋጀት የሚያስችል ሁኔታ ማመላከት፣
- የቴክኖሎጂ ዝርጋታና መጠቀም  ሂደትን ማመላከት፣
- የቅንጅታዊ አሰራር ስርዓቶችን ለመዘርጋት የሚያስችል አደረጃጀት ማስቀመጥ፣

## 1.4. የተሞክሮው አስፈላጊነት

በከተሞች ሊከሰቱ የሚችሉ የተፈጥሮ ወይም የሰው ሰራሽ አደጋዎችን አስቀድሞ ለመከላከል፣ ለመቀነስ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ለመስጠትና ድንገት የሚያጋጥሙ አደጋዎችን ተከትሎ ለሚፈጠረው ተጎጂና ተፈናቃይ ማህበረሰብ ሰብዓዊ አገልግሎት ለማቅረብ በቂ ዝግጅት ለማድረግ እንዲሁም በአደጋ ምክንያት ለሚፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ጊዜያዊ ድጋፍ ለማድረግና መልሶ የማቋቋም ስራውን በበላይነት ለማስተባበር እና ከተሞች በተረጋጋ ሁኔታ ዳግም ወደ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማቶች እንዲመለሱ የሚያስችል ተግባራትን በተደራጀ አግባብ ለመምራት አስፈላጊ ነው፡፡

## 1.5. ተሞክሮ ሊወሰድባቸው የተመረጡ የትኩረት መስኮች /ወሰን/

- ከአደረጃጃት አንጻር፣
- ከስታንዳርድ አንጻር፣
- ከአፈጻጸም ውጤት አንጻር፣
- ከተደራሽነት አንጻር፣

## 1.6. ተሞክሮውን ለመቀመር የተካሄደበት አግባብ

ተሞክሮውን ለመቀመር የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን መጠቀም የተቻለ ሲሆን፡-

### 1.6.1.የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች

- በመቋቋሚያ አዋጁ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች በማየት፣
- በስልጠና ወቅት የተሰጡ ጽሁፎችን መነሻ በማድረግ፣
- በየደረጃው የዕቅድ አፈጻጸም ውይይቶች ወቅት ከሰራተኛው የተገኙ ግብዓቶች በማጤን፣
- ተሞክሮ ለመቀመር የሚያስችል መርሆ ላይ በጋራ በመወያየት፣ በየደረጃው የተደረጉ ውይይቶች አስተያየቶች በመቀበል እንዲሁም በየደረጃው ከሚገኙ አስፈጻሚ ፈጻሚ አካላት ጋር በቃለ መጠይቅ እና ውይይት በማድረግ መረጃዎችን በመውሰድ፣
- ከተቋሙ የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ከስራ ኃላፊዎች፣ ከስራ ክፍሎችና ከባለድርሻ አካላት፣ የተቋሙን ዕቅድ አፈጻጸም እና አሰራሮችን በመፍተሽ፣
- ከተቋሙ 87 ዓመታት ልምድና ሪፖርቶች፣ በአፈጻጸም ግምገማ ወቅት የተሰጡ ሃሳቦችንና አስተያየቶችን በመውሰድ፣ ከተለያዩ ድረ ገጾች አግባብነትና ተዛማችነት ያላቸውን ተነባቢ ጽሁፎች በማፈላለግና በማገናዘብ ነው፡፡

### 1.6.2. የሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች

- ከመሰል አለማቀፍ አቻ ተቋማት ስለተሞክሮ ቅመራ መረጃ በመሰብሰብ አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመውሰድ፣ ስለተሞክሮ የተጻፉ ልዩ ልዩ ጽሁፎችን በመውሰድ፣
- አለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን እንዲሁም የስነ ጽሁፍ ዳራዎችን (Theoretical Framework) በመቃኘት፤
- በአጠቃላይ ከመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ የሚገኙትን ሀተታዊና አሐዛዊ (qualitative and quantitative) መረጃዎችን በመተንተን ተካሂዷል፡፡
- የተቋሙን የተለያዩ ጊዜያት መዋቅራዊ ጥናቶችን በማንበብ፣

## 2. የእሳት እና አደጋ ስጋት ስራ አመራር የቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ

### 2.1. የእሳት አደጋ ስጋት ስራ አመራር አገልግሎት ስታንዳርድ ትግበራን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በአሰራርና በአደረጃጀት የተከናወኑ ስራዎች

ውስጣዊና ውጫዊ የሆኑ ሁኔታዎች በአሰራር እና አደረጃጃት በማሳለጥ በስታንዳርድ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ሳይንሳዊ ዑደት የተከተለ የተደራሽነት፣ የቴክኖሎጂና ግብዓት ማሟላት፣ የፖሊሲና የህጎች ማቀፎች፣ የደንብ፣ የአሰራር ስርዓት፣ የአደጋ መረጃ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ባለሙያዎች ማፍራት ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ አሰራሮችና አደረጃጀቶች ተፈጥረዋል፡፡ በዚህ መሰረት የተሰሩ ስራዎች ከአደረጃጀት፣ ከአሰራር፣ ከግብዓትና ከሰው ሀይል አንጻር ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## ሀ/ ከአሰራር አንጻር

የአሰራር ቅልጥፋና እንዲመጣ፣ ስራዎችን በስታንዳርድ ለመከናወን፣ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት፣ ተገልጋዩን የሚያረካ፣ የጉዳት መጠን የቀነሰ፣ አለማቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ግብአት ለማቅረብ፣ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር በሁሉም አካላት ዘንድ ትኩረት እንዲያገኝ እና የባለሙዎች የብቃትና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዲቻል ከተማችን የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ስራዎችን ለማከናን የሚያስችል ሁሉንም የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ዑደት አቀናጅቶ የሚፈጽምና ሊያስፈጽም የሚችል ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራርን አገልግሎት ትግበራን በስታንዳርድ ለመተግበር እንዲቻል፡-

- በከተማ ደረጃ የአደጋ ስጋት ተግባሮችን ለማስፈጸም የሚያግዙ ከተማ አቀፍ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ ማኑዋል፣ መመሪያ ማዘጋጀት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የቅድመ አደጋ፣ በአደጋ ወቅት እና በድህረ አደጋ ወቅት መፈጸም የሚገባቸውን ተግባሮች አቀናጅቶ የሚመራ፣ የሚከታተል የአደጋ ስራ አመራር ካውንስል ወይም ምክር ቤት ማቋቋም፣

## ለ/ ከአደረጃጀት አንጻር

- ሁሉንም የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ሳይንሳዊ ዑደቱን (የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ዝግጁነትና ምላሽ፣ የአደጋ ጊዜያዊ ድጋፍ፣ የአደጋ ማቋቋም እና መልሶ መገንባት) ጠብቆ ሊያሰራ የሚችል የመዋቅራዊ አደረጃጃት መቅረጽ፣
- የአደጋ ስጋት ቅነሳውን ለማካተት የሚያስችል በጥናት ላይ የተመሰረተ ምቹ አደረጃጃት መፍጠር፣
- ከተማ አቀፍ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ቅንጅታዊ አደረጃጀት ሊፈጥር የሚችል መዋቅር ማዘጋጀት፣
- የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ሳይንሳዊ ዑደትን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል አስገዳጅ ህግ፣ ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዕቀፍ አዘጋጅቶ መተግበር፣
- የሚሰሩ የልማት እና የአገልግሎት ስራዎች ከአደጋ ስጋት ስራ አመራር አንጻር የተቃኘ የአደጋ ማካተት አሰራር ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፣
- የአደጋ ስጋት ስራ አመራር አገልግሎቶችን በማስገንዘብ ላይ የተመሰረተ እና ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መልኩ የአደጋ ደህንነት አስገዳጅ ህግ /ኮድ/ እና የማካተት ፖሊሲ መተግበር፣

- የአለማቀፍ ስታንዳርዶችና የከተማዋን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ተደራሽነትን ለማረጋጋጥ የሚያችል ቅርንጫፍና ንዑስ ቅርንጫፎችን ማደራጀት፣
- የአደጋ ስጋት ስራ አመራር አገልግሎቶችን በቅንጅታዊ አሰራር ለማሳለጥ የሚያችል አሰራር በማፍጠር መተግበር፣
- የከተማዋን ነባራዊ ሁኔታ እና ወቅቱ የሚጠይቀውን ግብዓት በማሟላት የአደጋ ዝግጁነትና ምላሽ መስጫ ማሽነሪዎች፣ መጋዘኖች፣ ጋራዥና ነዳጅ ማደያ እንዲሁም ዘመኑ የደረሰበትን የአደጋ የሚመራ መረጃ ማዕከል ማደራጀት እና መጠቀም፣
- የአደጋ አገልግሎቶች በስታንዳርድ ለመስጠት የሚያስችል የመሰረተ ልማት ሁኔታዎች እንዲሟሉ ጥረት ይደረጋል፣
- የአመራሩ የመምራት፣ የሙያዊ እና የቴክኒዊ ድጋፍ ስልትና አቅምን በማጎልበት ውጤታማ የአደጋ ስጋት አመራር አገልግሎት መስጠት፣
- የአደጋ ስጋ ስራ አመራ ዑደትን በመጠበቅ ስራው የሚፈለገውን የሰው ሀይል ብዛት፣ የሙያ ስብጥር፣ የስራ ልምድ፣ የትምህርት ዝግጅት፣ ደመወዝና ጥቅማጥቅም እንዲሟላ በማድረግ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣
- የአማራሩንና የሰራተኛው አገልጋይነት ስሜት በማጎልበት የተገልጋዩ ፍላጎት ተሟልቶ እርካታ እንዲጨምር መስራት፣
- የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር የአደጋ ስጋት ስራ አመራርን በቅርብ ርቀት መፈጸም፣
- በተለያዩ ተቋማት በተበጣጠሰ መልኩ ሲሰጡ የነበሩ ስራዎችን ማለትም የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታና መልሶ ማቋቋም ድጋፍ ስራዎች ወደ አንድ በማምጣት በአንድ የሥራ ክፍል እንዲደራጁ ማድረግ፣
- የአደጋ ስጋት ስራ አመራርን ዑደትን የመከላከል (Prevention)፣ የጉዳት ቅነሳ (Mitigation)፣ የዝግጁነት (Preparedeness)፣ የምላሽ (Response)፣ የሰብዓዊ ድጋፍ (Relief)፣ የመልሶ መገንባትና ማቋቋም (Recovery/Rehablitation/) ተግባሮችን በተከተለ መልኩ ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠር፣

## 2.2. የእሳትና አደጋ ሰጋት ስራ አመራር አገልግሎትን ለማሻሻል በሰው ሃይል ልማት የተከናወኑ ስራዎች

### የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ባለሙያ ከማብቃት አንጻር፡-

- የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ተግባራትን/ስራዎችን በተሻለና ብቃት ባለው ባለሙያ ለመምራት የሚስችል ውጤታማ የሥልጠና መስጫ ተቋም በማደራጀት በዘርፉ በቂ

እውቀትና ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎች ለመፍጠር የሚያስችል የሥልጠና አሰጣጥ አሰራር ስርዓት መዘርጋት፣

- በአደጋ ስጋት ስራ አመራር ዘርፍ የባለሙያዎችን የስራ ደረጃ (Career Structure) መሰረት በማድረግ የሥልጠና ካሪኩለም ወይም ማኑዋል ማዘጋጀት፣
- የሥልጠና ተቋሙን በበቂ በሰው ሀይልና ግብዓት በማደራጀት ጥራት ያለው ሙያዊ ስልጠና መስጠት፣
- ዘመናዊ የአደጋ ምላሽ መስጫ ማሽሪዎችን በቶሎ ተረድቶ በአግባቡ መጠቀም የሚችል ባለሙያ ቁጥርን ለማሳደግ መስራት፣
- በተቋሙ ያለውን የአሰራር ስርዓት በማዘመን አደጋ በመከላከል፣ ፈጣን ምላሽ በመስጠት ማህበረሰቡን፣ ተቋማትን እና ግለሰቦችን የአደጋ መከላከል አቅማቸውን የሚያሳድግ የአገሪቱ የልቀት ማእከል እንዲሆን የሚያስችሉ ስራዎችን ማከናወን፣
- የሥልጠና ተቋሙን በተለያዩ ግብዓቶች በማደራጀት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማንኛውም ተቋም ወይም ግለሰብ በሙያው ስልጠና መስጠት፣
- የአመት የሥልጠና ካላንደር ወይም ካታሎግ በማዘጋጀት ለተለያዩ ተቋማትና ህብረተሰብ የማስተዋወቅ ስራ መስራት፣
- ከመንግስት ከሚመደበው በጀት በተጨማሪ የሥልጠና ተቋሙ ከስልጠና፣ ሙያዊ ምክር፣ ከመወያያ ክፍልና አዳራሽ ኪራይ፣ እና ከሌሎችም የሚያገኛቸውን ገቢዎች ለራሱ የልማት ዕቅዶች ማሳኪያ መጠቀም የሚችልበትን አሰራር መዘርጋት፣
- በሥልጠና ተቋሙ የተለያዩ የሥልጠና ፍላጎት ጥያቄ የሚያቀርቡ ተገልጋዮች ጉዳያቸውን በአንድ ማዕከል እንዲጨርሱ ማድረግ (በተለይ የክፍያ ስርዓት)
- የአደጋ ማሽነሪዎችን ማንቀሳቀስ ወይም ኦፕሬት ማድረግ የሚችሉ ባለሙያዎችን ከአዲስ አበባ ትራንስፖርት ባለስልጣን በተሰጠው ፍቃድ መሰረት ማሰልጠን፣
- ዘመናዊ የተናበበና የተቀናጀ አደጋ ዝግጁነትና ምላሽ ተግባሮችን ለመፈጸም እንዲሁም የተማከለ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር የሚያስችል የአደጋ ማስተባበሪያ ማዕከል (EOC) ማደራጀት፣
- ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታና መልሶ ማቋቋም የሚያገለግሉ ሀብቶችን ለማሰባሰብና በመጋዘን ለመከዘን የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር፣
- የአደጋ ስጋት ቅነሳ ግንዛቤ ማስጨበጥ ተግባሮችን በተለያዩ የሚዲያ ተግባቦቶች በመጠቀም በሚፈለገው የአገልግሎት ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችል የቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ እና ማህበራዊ ሚዲያዎች ፕሮግራሞችን መረጣ፣ ይዘትና ቀረጻ ተግባሮችን የሚያከናውን አደረጃጀት መፍጠር፣

- በድንገተኛ አደጋዎች ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎትን ለማጠናከር የሚያስችል (የሺፍት አስተባባሪዎች በመጨመር) አደረጃጀት መፍጠር፣
- የአደጋ ማሽነሪዎችን ማንቀሳቀስ የሚችሉ ኦፕሬተሮችን በሥልጠና ተቋሙ በበቂ ሁኔታ ለማሰልጠን የሚያስችል አደረጃጀት በመፍጠር ልዩ መንጃ ፍቃድ እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- አደጋን በልማት ዕቅዶች ተካቶ እንዲተገበር የፖሊሲ ማዕቀፍ፣ ስትራቴጂክ ዕቅድና የትግበራ ማንዋል እንዲወጡ ማድረግ፣
- ተቋማትንና ህብረተሰቡን ስለአደጋ ደህንነት ከማስገንዘብ ባሻገር የልማት ዕቅዶችና ተግባሮች ከአደጋ ስጋት ቅነሳ ወይም ከአደጋ ደህንነት አንጻር የማካተት ስራዎችን ለማስፈጸም እንዲሁም የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስል አስገዳጅ ህግ/ኮድ ማዘጋጀትና መጽደቅ፣
- የአደጋ ስጋት ተጋላጭነት በጥናት እየተለየ መፍትሄ ማስቀመጥ የሚያስችል አሰራር በመፍጠር፣ የአደጋ ስጋት ተጋላጭ ጥናቶች ማለትም የአደጋ ስጋትና ተጋላጭነት ጥናቶች በተናጥል ተጠንተው በጥናቱ ውጤት መሰረት የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል በማደራጀት ህብረተሰቡን የቅድመ ማስጠንቀቅ ስራ እንዲሰራ ማድረግ፣
- በእጅ የሚያዙ የእሳት አደጋ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች የደህንነት ፍተሻ ተግባር በግል ተቋማት እንዲፈጸም የሚያስችል ግልጽ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ የክትትልና ቁጥጥር አሰራር ስርዓቱን ማጠናከር፣
- የአደጋ ምላሽና መቆጣጠር ኦፕሬሽን በተሻለ ደረጃ ለመፈጸም የሚያስችል  የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት በመዘርጋት፣ በአደጋ ወቅት በመቀናጀት የአደጋ ምላሽ አገልግሎት በፍጥነትና በቅልጥፍና እንዲሰጥ ማድረግ፣
- አደጋ ከመድረሱ በፊት የአደጋ ምላሽ አሰጣጥ ዕቅድና ልምምድ፣ የተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር ማኑዋል፣ አደጋ ዝግጁነት ስታንዳርድና ዕቅድ የመሳሰሉትን በማዘጋጀት የዝግጁነት አሰራር መዘርጋት፣ በተዘጋጀው ስታንዳርድ መሰረት ከአደጋ በፊት በቂ ልምምድ በማድረግ አፈጻጸም መገምገም፣
- በከተማ አቀፍ ደረጃ የአደጋ ዝግጁነት፣ ምላሽ (አስቸኳይ ጊዜ እርዳታ አቅርቦት) እና መልሶ ማቋቋም ተግባራት ለማስፈጸም የሚያስችሉ የአሰራርና የህግ ማዕቀፎች ማዘጋጀት፣
- አደጋዎችን በዓይነት፣ ስፋት እና የቆይታ ጊዜን በመተንበይና በመተንተን ለአደጋ ምላሽ መጠቀም እንዲሁም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማወጅ የሚስችል የአሰራር ስርዓት ማበጀት፣
- ለህብረተሰቡ የቅድመ አደጋ ማስጠንቀቂያ መረጃዎችን (Early Warning information) በአደጋ ወቅት ለማድረስ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ማዘጋጀት፣
- ለትልልቅ ፕሮግራሞችና ኩነቶች (Events) መነሻ በማድረግ የስጦታ ማቴሪያሎችን (ካላንደር፣ ፖስት ካርድ፣ የቡናና የሻይ መጠጫ እቃዎችና የተቋሙን መረጃ የያዘ ዕህፈት

መሳሪያዎች፣ የመማሪያ ደብተር…ወዘተ) በመጠቀም የተቋሙን አገልግሎቶችና በአደጋ ደህንነት ዙሪያ የማስገንዘብና የማስረጽ ስራ መስራት፣

- በየተቋሙ የቅድመ አደጋ ስጋት ተጠሪ (Focal Person) በመምረጥና በማሰልጠን በተቋሙ ያሉ ሁሉም የተቋሙ ተጠቃሚዎች የአደጋ ስጋት ግንዛቤ የማሳደግ ስራ ይሰራል፣
- በከተማ ደረጃ በየአመቱ ለአደጋ ስጋት ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ (የአለምና የኢትዮጵያ) የአደጋ ቀን በሚል ልዩ ፕሮግራም በማዘጋጀት የግንዛቤ ማስጨበጥና ማስረጽ ስራን መስራት ያስፈልጋል፣
- በሥልጠና ተቋሙ የተለያዩ የሥልጠና ፍላጎት ጥያቄ የሚያቀርቡ ተገልጋዮች ጉዳያቸውን በአንድ ማዕከል እንዲጨርሱ በማድረግ (በተለይ የክፍያ ስርዓት) ከመንግስት ከሚመደበው በጀት በተጨማሪ የሥልጠና ተቋሙ ከስልጠና፣ ሙያዊ ምክር፣ ከመወያያ ክፍልና አዳራሽ ኪራይ፣ እና ከሌሎችም የሚያገኛቸውን ገቢዎች ለራሱ የልማት ዕቅዶች ማሳኪያ መጠቀም የሚችልበትን አሰራር መከተል ይገባል፤
- ከአለም አቀፍ ተሞክሮዎች በመነሳት አደጋ ከመድረሱ በፊት የተሟላ ዝግጅት ለማድረግ የሚያስችል የዝግጁነትና ምላሽ ስታንዳርድና ዕቅድ በማዘጋጀት በቂ ልምምድ ማድረግ፣
- በድንገተኛ አደጋዎች ላይ የህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለመስጠት ከጤና ቢሮ ጋር በመቀናጀት መስራት፣
- የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ በፍትሃዊነት ለማድረግ አለም አቀፍ ስታንዳርዶችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣ በተዘጋጀው ስታንዳርድ መሰረት በቂ ልምምድ በማድረግ አፈፃፀሙን መገምገም፣
- በተዘጋጀው የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል መሰረት በቂ የአደጋ ጊዜ እርዳታ መስጫ የሆኑ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ፣
- በአደጋ ወቅት የአደጋውን ስፋትና ጉዳት መጠን በመተንተን የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ተጎጂዎች ለመለየት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣
- የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚያስፈልጋቸውን አደጋዎች በመጠን፣ በስፋትና በይዘታቸው መሰረት ለይቶ የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣
- ከአደጋ በፊት፣ በአደጋ ጊዜ እና ከአደጋ በኃላ የተገኙ የአደጋ መረጃዎችን የተማከለ ፍሰት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በጥቅም ላይ ማዋል፣
- ዘመናዊ የአደጋ መረጃና ቴክኖሎጂ ስርዓት በመዘርጋት ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በሲስተም የማስተሳሰር ስራ መስራት፣
- የአደጋ ስጋቶችን በመተንበይና በመተንተን አስቀድሞ የጉዳት ቅነሳና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ተግባሮችን ለመፈጸም የሚያመላክት ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፣

- የተማከለ የአደጋ ስጋት መረጃዎችን በማደራጀት ከልማት ዕቅዶች ጋር የማካተት ተግባር ለመፈፀም ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣
- በአደጋ ወቅት የአደጋ ምላሽ ኦፕሬሽኖችን ከፍተኛ አመራሮች አደጋ ቦታው ላይ መሄድ ሳይጠበቅባቸው በአደጋ ማስተባበሪያ ማዕከል (EOC) ሆነው ለመምራትና ለመከታተል የሚያስችሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፣
- የአደጋ ማሽነሪዎችና መሳሪያዎች ባላቸው ልዩ ባህሪይ በፍጥነትና በጥራት የጥገና፣ የነዳጅ፣ የዘይት፣ የመኪና እጥበትና የመለዋወጫ አገልግሎቶች በቀላሉ በማግኘት የአደጋ ማሽነሪዎችና መሳሪያዎች ለአደጋ ስራ ዝግጁ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል የሥራ ክፍል በማደረጃጀት አላስፈላጊ ወጪዎችን መቀነስ፣
- የአደጋ ማሽነሪዎችና አጋዥ መሳሪያዎችን በግል የጥገና ካምፓኒ ወይም ጋራዥ ለጥገና የሚቆዩበትን ጊዜ ለማሳጠርና ወጪ ቆጣቢ ለመሆን የሚያስችል ጥራት ያለው የጥገና የአገልግሎት በራስ አቅም እንዲሰጥ ማድረግ፣
- የአደጋ ማሽነሪዎችን ከውጭ ሀገር ለመግዛት የዲዛይንና የስፔሲፊኬሽን ማውጣት ስራዎችን በራስ አቅም መስራት፣ የሞደፊኬሽን ስራዎችን በመስራት ከውጭ ሀገር የሚገቡ መለዋወጫዎችን ማስቀረት፣
- የመለዋወጫ እና አስፈላጊ የማለስለሻና የሀይድሮሊክ ሲስተሞች ቅባትና ዘይት፣ ነዳጅ ዲፖ አገልግሎት በወቅቱ ማግኘት፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ሲሆን ተጠሪነቱ ለሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ሆኖ በስሩ 3 ዘርፎችን፣ 6 ዓላማ ፈጻሚ ዳይሬክተሬቶች፣ 2 ማዕከላት፣ 9 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ 1 ንዑስ ጣቢያ እና 6 የድጋፍ ሰጭ ዳይሬክቶሬቶች በአጠቃላይ 2365 የተለያዩ ሙያ ያላቸው ሠራተኞችን በመዋቅር አደራጅተዋል፡፡ በመሆኑም ትክክለኛ ስታንዳርዱን የጠበቀ ተቋም እንዲፈጠር፣ የአደጋ ሥራ አመራርን ለመምራት የሚያስፈልጉ ስታንዳርዶች መቀመጣቸው፣ የአደጋ ምላሽ አሰጣጥ ዝግጁነትን ለማረጋገጥ፣ እንደ ስራ በሀሪው የማዕረግና የደረጃ ስያሜ ለባለሙያው እንዲመቻች አስችሎአል፡፡ /ጀማሪ የእሳት አደጋ ተቆጣጣሪ /Junior fire fighter/፣ የእሳትአደጋተቆጣጣሪ /Fire fighter/፣ ከፍተኛ የእሳት አደጋ ተቆጣጣሪ /Senior fire fighter/፣ የቡድን መሪ /Team leader/፣ ሽፍትመሪ /Shift leader/፣ ሽፍት ኮማንደር /Shift commender/፣ የንዑስ ጣቢያ አዛዥ /Sub-station Manager/፣ የጣቢያ አዛዥ /Station Manager/፣ ምክትል ዋና አዛዥ /Deputy fire chief/፣ ዋና አዛዥ /Fire chief/፣

በዚህ መሰረት ፡-

1.የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዘርፍ

1.1 የአደጋ ስጋት ጥናትና ትግበራ ዳይሬክቶሬት፣

1.1.1 የተጋላጭና የስጋት ጥናት ቡድን

1.1.2 የግንዛቤና ስትፀት ቡድን

1.1.3 የህዝብ ተሳትፎ ቡድን

1.1.4 የሙያ ምክርና ቴክኒክ ቡድን

1.1.5 የፍተሸና ብቃት ማረጋጋጥ ቡድን

1.1.6 የአደጋ ማካተት ቡድን

1.2 የአደጋ ዝግጁነት ፈንድና ሎጀስቲክ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣

1.2.1 የሀብት ማሰባሰብ ቡድን

1.2.2 የሎጀስቲክ አስተዳዳር ቡድን

2.የአደጋ ምላሽ ዘርፍ

2.1 የእሳት አደጋ ምላሽ ቡድን

2.1. የሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች ቡድን

2.2. የድንገተኛ አደጋ እና የአደጋ ሰራተኞች ህክምና ዳይሬክቶሬት

2.2.1. የድንገተኛ አደጋዎች ህክምናና አምቡላነስ አገልግሎት ማተባበሪያ

2.2.2. የአደጋ ሰራተኞች ህክምና አገልግሎት ማስተባበሪያ

3. የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ እና የመልሶ ማቋቋም ዘርፍ

3.1. የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ እና የመልሶ ማቋቋም ዳይሬክቶሬት

3.1.1 የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ አቅርቦት ቡድን

3.1.2 የተጎጂዎች መልሶ ማቋቋም ፕሮጅክት ቀረጻና ትግበራ ቡድን፣

3.1.3 የተጎጂዎች ስነ ልቦና ቡድን

3.2. የአደጋ መረጃ ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ዝርጋታ ዳይሬክቶሬት

3.2.1. የአደጋ መረጃ ቴክኖሎጂ ማስተባበሪያ ቡድን

3.2.2. የአደጋ መረጃ ቴክኖሎጂ አቅርቦት ቡድን

3.2.3. የአደጋ መረጃ ቴክኖሎጂ ዝርጋታ ቡድን

4. የአደጋ ማሽነሪዎች ማህድስና ማዕከል

4.1 የአደጋ ማሽነሪዎች ጥገና እና መለዋወጫ ማምረቻ ቡድን

4.2 የአደጋ ማሽነሪዎች ስምሪት፣ ግብዓት አቅርቦትና ስፔስፊኬሽን ዝግጅት ቡድን

5. የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ስልጠና ማዕከል

5.1. የአደጋ ስጋት ቅነሳና መልሶ ማቋቋም ስልጠና ዲፐርትመንት

5.2. የአደጋ ምላሽና ወታደራዊ ስልጣና ዲፐርትመንት፣

5.3. የቅድመ ሆስፒታል ህክምናና አምቡላንስ ስልጠና ዲፐርትመንት

6. 9 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

6.1. የአደጋ ጥናት ትግበራ ማስተባባሪያ

6.1.1. የሙያ ምክርና ቴክኒክ ድጋፍና ፍተሻ ቡድን

6.1.2. የግንዛቤ፣ ስርጸትና ተጋላጭ ጥናት ቡድን

6.2. የአደጋ ምላሽ ማተባባሪያ

6.3. የቅድመ ሆስፒታልና ህክምና አምቡላንስ አገልግሎት ማስተባበሪያ

7. 1 ንዑስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ናቸው፡፡

## የተቋሙ ስልጣን፣ ተግባራትና ኃላፊነት

የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

- የመረጃና ቴክኖሎጂ ማዕከል በማቋቋም ከአደጋ በፊትም ሆነ በአደጋ ጊዜ እና በኋላ የተማከለ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣ በከተማ ደረጃ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤
- የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች መንስኤና የተጋላጭነት ደረጃና ትንተናት መረጃ ያሰባስባል፣ የቅድመ አደጋ ጠቋሚ ጥናቶችን በማካሄድ አስፈላጊውን የቅድመ ማስጠንቀቂያ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤
- በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን አስቀድሞ የመከላከል እና የአደጋ ጉዳት ቅነሳና የማጣጣም ስራዎችን ይሰራል፣ ሌሎች ተቋማትም እንዲሰሩ ያደርጋል፤
- በከተማዋ የሚገኙ ተቋማት የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዕቅድን በልማት ዕቅዶቻቸው ውስጥ እንዲያካትቱ ያደርጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆንኑ ይከታተላል፤
- የተቋሙ ባለሙያዎች ልዩ ልዩ ተቋማትና ህብረተሰቡ ስለ አደጋ ስራ አመራር ስልጠና የሚያገኙበት የስልጠና ማዕከል ያደራጃል፤
- በተከታታይ ወይም በዕቅድ ላይ ተመስርቶ የናሙና ልምምዶች ያከናውናል፣ እንዲከናወኑም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ በአደጋ ምላሽ ዕቅድ ላይም የማስተካከያ እርምጃዎችንም ይወሰዳል፤
- የአደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን የአደጋ ጊዜ ማምለጫ ደረጃዎች የእሳትና የጭስ፣ የነበልባል፣ እና ሌሎች አደጋ ጠቋሚ መሳሪያዎች በአገልግሎት መስጫ ልዩ ልዩ

ተቋማት መተከላቸውን በአግባቡ መስራታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

- ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ለህዝብ ለማድረስ ሁሉን አቀፍ የቅድመ አደጋ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ለህብረተሰቡ የቅድመ አደጋ ማስጠንቀቂያ መረጃዎችን በአደጋ ወቅት መውሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች እና የደረሰውን አደጋ በተመለከተ ወቅታዊ መረጃዎችን የማሰራጨት ተግባር ያከናውናል፤
- በአደጋ የተጎዱና የተፈናቀሉ አካላት የአጠቃላይ የጉዳት መጠን ፣ ክስረትና ፍላጎት መረጃ በማሰባሰብ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ለሚመለከተው አካል የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲወሰንም ተከታትሎ ይፈጸማል፣ ያስፈጸማል፤
- በከተማው የአደጋዎች ተጎጂዎችና ተፈናቃዮች ወቅታዊና ተደራሽ የሆነ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም የአደጋ ምላሽ አሰጣጥ ስራ አመራር ስርዓት ይዘረጋል፤
- በተከሰቱ አደጋዎች ምክንያት የተፈጠሩ ተጎጂዎችና ተፈናቃዮች መጠን የአፋጣኝ መረጃ ትንተና መሰረት በማድረግ በከተማ ደረጃ የአደጋ ጊዜ አስቸኳይ አዋጅ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን ለሚመለከተው አካል የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
- በአደጋ ክስተት ወቅት የሚመለከታቸውን መስሪያ ቤቶችና ነዋሪዎችን በማስተባበር ፈጣን ምላሽ ማለትም የነፍስ አድን ዕርዳታ ያደርጋል፣ ለድንገተኛ አደጋዎች የቅድመ ሆስፒታል ህክምናና የአምቡላንስ አገልግሎት ይሰጣል፤
- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የግል ድርጅቶችን እንዲሁም ሌሎች በከተማ ውስጥ በአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ አቅርቦትና መልሶ ማቋቋም ተግባራት ላይ ሚና ያላቸው ተቋማት ያስተባብራል፤
- የአደጋ ስጋት ስራ አመራር መሰረተ ልማቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤
- በአደጋ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ጊዜያዊ ድጋፍና መልሶ የማቋቋም ተግባር ያከናውናል፤
- ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ አቅርቦት ምላሽ ስራ ብቻ የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆነ ቁሳቁስ በመጠባበቂያነት ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣ ያስራጫል፤
- አደጋ ስጋት ቅነሳ ስራዎች እና በአደጋ ወቅት የአሰቸኳይ ጊዜ ምላሽ እርዳታ አቅርቦት አገልግሎቶች ላይ የሚሳተፉ በጎ ፍቃደኞችን በመመልመል በማደራጀትና ሙያዊ ስልጠናዎች በመስጠት የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ተግባራት ላይ ተባባሪ እንዲሆኑ ይሰራል፤
- በአደጋ ስራ አመራ ውስጥ ተሳታፊ በመሆን ባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ለማስፈንና ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ የጋራ መድረኮች ይመሰርታል፤

- አግባብ ባለው ህግ አደጋ በይፋ መግለፅ ተከትሎ አግባብ ባለው ሲወሰን ከተለያዩ አካላት ለምላሽ የሚውል ሀብት በማሰባሰብ ድጋፍ ያደርጋል፤
- ፓራ ሚሊተሪ ሰራተኞችን ካቢኔ በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፡፡

## 3. የእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ስታንዳርድ ትግበራ ምዕራፍ

### 3.1. የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ሂደት

የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ማለት የአደጋ መንስዔ ተጽዕኖንና የአደጋ የመከሰት ዕድልን ለመቀነስ እንዲሁም የሚከሰቱ አደጋዎችን ለመመከት የዝግጁነት፣ ምላሽ የመስጠትና መልሶ የማቋቋም/የመገንባት ተግባራትን ለመፈጸም እንዲቻል ስርዓት ባለው መልኩ የአስተዳደር ስትራቴጂዎችን፣ ተቋሞችን እንዲሁም የአሰራር ክህሎቶችንና አቅሞችን የመጠቀም ሂደት ነው፡፡

- የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ማለት አደጋ ከመከሰቱ በፊትና በኋላ ያሉትን የአደጋ ዝግጁነት ምላሽና መልሶ ማቋቋም ውስጥ ያሉ የተግባር ሂደቶች የሚያጠቃልል ንድፈ ሃሳብ ነው፡፡
- የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር በሶስት ዋና ዋና ሂደቶች ሲኖሩት እነዚህም የቅድመ አደጋ፣ በአደጋ ወቅት እንዲሁም ድህረ አደጋ ተግባራት ተብለው ይከፈላሉ፡፡

**ሀ/ የቅድመ አደጋ ተግባራት:- መከላከል /Prevention/፣ የአደጋን ማጣጣም /Mitigation/፣ ዝግጁነት /Preparednes/**

1. መከላከል፡- አስቀድሞ አደጋዎች እንዳይደርሱ ቅድመ ጥንቃቄ በማድረግ ግንዛቤና እውቀት በመገንባት፣ የህግና የአሰራር ማዕቀፎችን በመዘርጋትና በመተግበር አደጋዎችን መከላከል ማስቻል ነው፡፡
2. የአደጋን ማጣጣም (መቀነስ)፡- የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ አደጋ ቢከሰት እንኳን የአደጋውን መጠን መቀነስ ማስቻል ነው፡፡ ይህም በግንባታ ሂደት ቁጥጥሮችን በማድረግ፣ የጎርፍ መከላከያ ግድቦችን በመስራት፣ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች ህዝብ እንዳይሰፍርና የልማት ስራዎች እንዳይከናወኑ በማድረግ፣ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በመጨመር የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠትን ያጠቃልላል፡፡
3. ዝግጁነት፡- ይህ አደጋ ቀድሞ ከመድረሱ በፊት አስቀድሞ በማወቅ ወይንም በመገመት ለአደጋ ክስተት ምላሽ ሰጪ አካላትና ህብረተሰቡ አደጋውን ዝግጁ ሆኖ እንዲጠብቅ ለማስቻል የሚወሰዱ እርምጃዎችን ሲሆን እነሱም የህብረተሰቡን አደጋ የመቋቋም አቅምን ማሳደግ፣ የመጠባበቂያ እቅድና በጀት ማዘጋጀትን፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት መዘርጋትን፣ የሰው ሃልና በቂ ሎጂስቲክስ ማደራጀትን፣ አደጋ ጊዜ አቅርቦቶችን (Supplies) ሟሟላትን፣ በጎ ፈቃደኞችን ማሳተፍ፣ ስልጠናን፣ ህዝብ

ግንኙነት፣ የመሳሰሉ ተግባራት ያጠቃልላል፡፡ ስለሆነም ዝግጁነት በአጠቃላይ አደጋውን እንዲቋቋም ማስቻል ነው፡፡

### ለ/ የድህረ አደጋ ተግባራት፡- ምላሽ፣ ማገገም፣ መልሶ መቋቋም፣ መልሶ መገንባት

i. **ምላሽ** **(Relief & Response)** ይህ አደጋው በተከሰተበት ወቅትና አደጋው ከተከሰተ በጥቂት ጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ አደጋው የተከሰተባቸውን የህብረሰብ ክፍሎች ችግር የሚቀርፉ ተግባራትን ጊዜያዊ መጠለያ፣ ውሃ፣ ንፅህና፣ የሕክምና አገልግሎት እና አደጋ የሚከሰትበትን አካባቢ ማስለቀቅን (Evaculation) ያጠቃልላል፡፡

ii. **ማገገምና መልሶ ማቋቋም** (Recovery and Rehabilitation)፡- አደጋው የተከሰተበት ማህበረሰብ ከአደጋው ሙሉ ለሙሉ እንዲያገግምና መልሶ እንዲቋቋም የሚያስችሉ ተግባራት የሚከናወኑበት ነው፡፡ በዚህ ተግባር ውስጥ የፈረሱ ቤቶችንና፣ ተቋማትን፣ መሠረተ ልማቶችን መልሶ መገንባትን እንዲሁም ህብረተሰቡ ከአደጋው ሙሉ በሙሉ በማገገም ወደ ቀድሞ ተግባራቱ እንዲመለስ የሚያስችሉ የተለያዩ የመልሶ ማቋቋም ማለትም ማህበራዊ ግልጋሎቶች የሚያገኝበትን፣ ኢኮኖሚያዊ አቅሙን የሚያሳድግበት አማራጮችን በማስፋት የኑሮ መሰረቶችን የማስፋት (Livelihood creation) ተግባራትን የሚያጠቃልል ነው፡፡

## 3.2. የእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ስታንዳርድ ትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

የእሳት አደጋ ስጋት ስራ አመራር መገለጫ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 92 እና 93 የሚመነጭ ብሄራዊ የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ሆኖ መነሻና መድረሻው የህብረተሰቡ ከአደጋ መጠበቅ እና የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ የዝግጁነትና ምላሽ፣ የድጋፍና በቋሚነት መልሶ መቋቋም ፍላጎት መኖር ነው፡፡ ስለሆነም ከአዲስ አበባ ከተማ እድገት ጋር ተያይዞ የሚመጡ በርካታ የአደጋ ደህንነት ስጋቶች ያሉ ሲሆን ለችግሮቹ ደረጃውንና ወቅቱን የጠበቀ ፈጣን ምላሽ ካልተሰጠ በስተቀር የህብረተሰቡ ደህንነት ለአደጋ እንደሚጋለጥ አያጠራጥርም፡፡ አደጋዎች ከመከሰታቸው በፊት ለመከላከልና በየጊዜው ለሚከሰቱ አደጋዎችም ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ደረጃውን የጠበቀ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር አደረጃጀት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሰረት በተቋሙ የሚታዩትን የማስፈጸም አቅም በመገንባትና የአደረጃጀት ክፍተት በመፍታት የህብረተሰቡ ደህንነት መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም በእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ተቋም የሚታዩ ውስጣዊና ውጫዊ የሁኔታ ዳሰሳ ትንተና በጠንካራ ጎን፣ በደካማ ጎን፣ በመልካም ዕድልና ስጋት (SWOT) የትንተና ስልት በመጠቀም የተቋሙን የነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ ለመተንተን ተችሏል፡፡

### 3.2.1. ውጫዊ ችግሮች

#### ሀ/ ከፖለቲካ አንጻር

- የፖለቲካ አመራርና የባለድርሻ አካላት ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር መሰጠት ያለበት ትኩረት ቀጣይነት ባለው መልኩ የከተማዋን ተጨባጭ የአለም አቀፍና አህጉር አቀፍ የፖለቲካ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ እንድምታን አለመገንዘብ ሁኔታ ሊገጥም ይችላል፣ ለአብነት ከተማዊ የአለማቀፍን አህጉር አቀፍ ዲፕሎማቶች መቀመጫ እና ኢኮኖሚ ማዕከላዊነት በተነሳ የአደጋ ስጋት መኖር የፕሬስ ኮንፈረንስ፣ የቱሪዝምና የኢንቨስትመንት ወዘተ ፍሰትን የሚገድብ መሆኑ፣
- የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ተግባራት የራሳቸውን የሙያዊና ቴክኒካዊ አሰራር ተከትለው እንዳይሄዱ የአመራሩ ፓለቲካዊ ተጽኖ ማሳደር ሊገጥም ቻሉ፣

#### ለ/ ከኢኮኖሚ አንጻር

- ከአለማቀፍ የአደጋ መከላከል፣ ዝግጁነትና ምላሽ፣ ጊዜያዊ ድጋፍ እና መልሶ ማቋቋም ስታንዳርዶች አኳያ መደረስ የሚገባው ደረጃ አለመደረሱ፣ ለአብነት የአደጋ ክስተት፣ የማዳን አቅም፣ የአደጋ መቋቋም አቅም ወዘተ...ማለት ነው፤
- በአደጋ ዝግጁነትና ምላሽ ላይ የማዳን አቅማችንን በሚጠበቀው ደረጃ ለማድረስ አለመቻል፣ ለአብነት የማዳን አቅም ደረጃ /rate/ በከፍተኛ፣ በመካከለኛና በዝቅተኛ አደጋዎች ወቅት ዝቅተኛ መሆኑ፤
- በአደጋ ስጋት ቅነሳ አንጻር የአደጋ ክስተት መቀነስ በሚጠበቀው ደረጃ ለማድረስ አለመቻሉ፤
- የከተማው ነዋሪ ዝቅተኛ በሚባል የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ለአደጋ ተጋላጭነቱ የጨመረና የመከላከል፣ የመቋቋም አቅሙንና ግንዛቤው ዝቅተኛ በመሆኑ የአደጋ ክስተቱና ውድመቱ ከፍተኛ ሊሆን መቻሉ፣ ለአብነት በ10 ዓመት ውስጥ በተከሰቱ 3573 አደጋዎች የወደመ ንብረት በብር 1.4 ቢሊዮን ያህል መሆኑ ከተማዋን መልሶ ሊገነባ የሚችል ሀብት በአደጋ መውደሙን ያሳያል፤

- የአደጋ ስጋት ስራ አመራርን በተሟላ ሁኔታ ለመምራት የሚያስችል መሰረተ ልማት አለመዘርጋቱ፣ ለአብነት የአደጋ መብረሪያ ነጻ መንገድ፤
- የከተማ ነዋሪ ቁጥር መጨመሩ የከተማዋ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ፣ የአሰፋፈር፣ የግንባታ ሁኔተና ሜቴሪያል አንጻር ለአደጋ ተጋላጭነታቸው ከፍተኛ መሆኑ፣ ለአብነት በከተማዋ የተገነቡ አብዛኛው ግንባታዎች ከተራ ተቀጣጣይ ነገሮች ማለትም እንጨትና ጭቃ መገንባታቸው፣ የከተማዋ የመሬት አቀማማጥ ተዳፋታማነት መኖሩ፣ አሰፋፈሩ ፕላንንና ስታንዳርድን የጠበቀ አለመሆን፤
- በከተማዋ የሚገነቡ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች የአደጋ ደህንነትን ከግንዛቤ ያስገባ አለመሆኑ፣ ለአብነት የገበያ ማዕከላትና ሞሎች፣ ኢንዱስትሪ ፓርኮችና ፋብሪካዎች፣ የሀይል ማመንጫና ማሰራጫዎች፣ የነዳጅ ዲፖዎችና ማዲያዎች፣ ሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ህንጻዎች ግንባታ ወዘተ…
- ሀብትን በግልጽነትና በተጠያቂነት ለታለመለት ዓላማ አለማዋል ሊገጥም ይችላል፣ ለአብነት ከላጋሾች የሚገኝ ሀብትን ለታለመለት ዓላማ በትክክል ዓለማዋል፣
- ለተለያዩ አገልግሎቶች በግብዓትነት የምንጠቀምባቸውን ግብዓቶች የሚያስከትሉትን አደጋዎች ከግንዛቤ ያስገባ  ሁኔታ አለመኖር፣ ለአብነት ለህክምና የምንጠቀምባቸው ጊዜ ያለፈባቸው መድሀኒቶችና ሪኤጀንቶች፣ የጨረር አመንጪ ቁሶች፣ ለህንጻዎች ማስዋቢያ የምንጠቀምባቸው መስታወቶች፣ የማይበሰብሱ ቁሶች፣ ወዘተ…
- ለየብስና ለአየር የምንጠቀምባቸው የትርንስፖርት አገልግሎቶች ከአደጋ አንጻር የሚያስከትሉት አደጋ በሚገባ ከግንዛቤ አለመግባት፡- ለአብነት በከተማዋ የአየርና የምድር ባቡር  እና ሌሎች የማስ ትራንስፖርት አገልግሎት ወቅት አደጋ ቢከሰት ለአደጋው የሚሰጠው ምላሽና ዝግጁነት ከሰለጠነ የሰው ሀይልና የቴክኖሎጂና የግብዓት ሁኔታ ወዘተ ናቸው፡፡

## ሐ/ ከማህበራዊ አንጻር

- የሀገራችን ማህበራዊ፣ ሀይማኖታዊና ህዝባዊ አደረጃጀቶች የአደጋ ስጋት ቅነሳን ለማስረፅ በቅንነትና በተነሳሽነት ውጤታማ በሆነ ሁኔታ አለመስራት ሊያጋጥም ይችላል፣
- የከተማው ማህበረሰብ ከኢኮኖሚ የአቅም ውስንነት በመነሳት የአከታተም ዘይቤ፣ የአኗኗርና የጥግግት መጠኑ የአደጋ ስጋትን ከግንዛቤ ያስገባ አለመሆን፣
- የከተማዎ የእኮኖሚ ሁኔታ በመነሳት የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በየዕለቱ የሚገቡና የሚወጡ በመሆኑ ወጥ የሆነ የአደጋ ስጋት ግንዛቤ አለመኖር አደጋ ሊከሰት መቻሉ፣
- የከተማዋ ህዝብ ቁጥር በተለያዩ ምክንያቶች መጨመር ለአደጋ ተጋላጭ  ስለሚያደርገው ሌላኛው የስጋት ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡

### መ/ ከከባቢያዊና ከህግ ማዕቀፍ አንፃር

- የከተማው የህዝብ አሰፋፈር ማስተር ፕላኑን ያልጠበቀ መሆን በአደጋ ምላሽ መስጠት ላይ የራሱ የሆነ ተጽኖ ማለትም የአደጋ ተሽከርካሪ ለመስገባት አለመቻል ሽራ ለመዘርጋት የሚፈጀው ጊዜ ረጅም መሆንና የአደጋው ሁኔታ ሊስፋፋ መቻሉ፣
- የህብረተሰቡ የግንባታና ሌሎች ማህበራዊ ግብዓቶችን በመንገድ ላይ ማኖር አደጋን ለመከላከልም ሆነ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ሊፈጥር መቻሉ፣
- የተቀላጠፈና የተቀናጀ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የቅንጅታዊ አሰራር የህግ ማዕቀፎች በማዘጋጀት ተጠያቂነትን በሚያመጣ መልኩ እንዲተገበር በማድረግ የማስፈጸም ውስንነት፣ የህብረተሰቡ ፍላጎትና ህዝብ ቁጥር መጨመር እንዲሁም ከከተማዋ ዕድገት ጋር የተመጣጠነ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአለማቀፍ የአደጋ ስጋት አመራር ስታንዳርዶች ለማሟላት አለመቻል፣
- የአየር ንብረት መዛባትና ሙቀት መጨመር ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ ያልተጠበቁ ከፍተኛ አደጋዎች ሊደርስ ይችላል፣

### ሠ/ ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም አንጻር

- ተቋሙ ከአለማቀፍ ስታንዳርዶች አንጻር በቴክኖሎጂ የታገዘ የአደጋ ስራ አመራር አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችል አቅም ላይ አለመድረሱ ውጤታማ ላይሆን ይችላል፤
- በአደጋ ስጋት ስራ አመራር ዑደት ላይ ህዝቡ ከሚፈልገው የአገልግሎት ቅልጥፍናና ፍጥነት አንፃር የሚቀሩ ጉዳዮች ያሉት መሆኑ በስጋት የሚገለፅ ሊሆን ይችላል፤
- በከተማዋ አደጋን ለመከላከል የሚያስችሉ ዘመናዊና በቴክኖሎጂ የታገዙ አሰራሮችንና የአሰራር ስርአቶችን መተግበር ላይ በርካታ ክፍተቶች ሊኖሩ መቻላቸው፤
- ለአደጋ ክስተቶች ምላሽ መስጫ የምንጠቀምባቸው ቴክኖሎጂዎች፤ የአደጋ ደህንነት መቆጣጠሪያ ስልቶቻችን ደካማ ሊሆን መቻሉ፤
- ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር የምንጠቀምበት የአደጋ ጊዜና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ካሜራዎችና ቴክኖሎጂዎች አለመኖር በቴክኖሎጂ የታገዘ ውሳኔ መስጠት አለመቻል፤
- በአዲስ አበባ ደረጃ ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር ተግባር በጥራት ለመፈጸም የሚየስችል ከባቢያዊ ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል፡፡
- ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የፈሰሰባቸው መሰረተ ልማቶች (ለምሳሌ ማሳለጫ መንገድ፣ የኤሌክትሪክ ማሰራጫዎች፣ የውሃ ፋሲሊቲዎች፣ ትልልቅ ተቋማት ወ.ዘ.ተ) በቴክኖሎጂ (Arificial Intellegence) የተደገፈ የእይታ ካሜራዎች ያልተገጠመላቸው መሆኑ ለአደጋ የተጋለጡ መሆናቸው፤

- በከተማችን የተቀናጀ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈና የተማከለ የመረጃና የአደጋ ማስተባበሪያ ማእከል ባለመኖሩ የተቀናጀና ፈጣን የአደጋ ምላሽ በመስጠት የሰው ህይወትና ንብረት በተሻለ አሰራር ከአደጋ ለመታደግ አለመቻል ሊያጋጥም ይችላል፤

ተቋሙ በዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለውና በሀገራችንም ሆነ በከተማዋ ተመሳሳይ ተቋምና አገልገሎቶችን የሚሰጥ አለመኖሩ፡፡ አገልግሎቶቹም በስራ ደህንነትና ጤንነት አስጊ ከሆኑ ስራዎች የሚመደብ በመሆኑ ከሌሎች ሀገሮች አቻ ተቋማት የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ዝግጁነትና ምላሽ፣ በአደጋ ምክንያት ለሚፈናቀሉ ሰዎች ሰበአዊ ድጋፍና የማቋቋም አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን በሀገራችን አንጋፋውና የ86 ዓመታት ተሞክሮ ያለው እንደመሆኑ መጠን በቀጣይ በአገሪቱ ለሚቋቋሙ ተመሣሣይ ተቋማት በአርአያነት ስለሚጠቀስ ዓላማና ተግባራቱን በአግባቡ መፈፀም የሚጠበቅበት በመሆኑ በከተማ አስተዳደሩ የተሰጠውን ተልዕኮ መፈጸም በሚንቀሳቀስበት ወቅት በስራ ላይ በተለያዩ ተጋላጭነቶች ውስጥ ይሆናሉ፡፡

### በአደጋ ስራ ወቅት የሚገጥሙ የደህንነት ተጋላጭነቶች፡-

- ሰራተኞቹ በአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ በአደጋ ዝግጁነትና ምላሽ፣ ጊዛዊ ድጋፍና መልሶ ማቋቋም ወቅት የአካል መቃጠል፣ በጭስ መታፈን፣ በኬሚካሎች መመረዝ፣ በትነቶችና ሽታዎች መበከል፣ ለራዲዮ አክቲቭ ጨረሮች መጋለጥ፣ በፍንዳታዎችና በአደጋ ምላሽ መስጫ ማሽነሪዎች የሚወጣ ኬሚካል መመረዝ፣ በድምፅ ጆሮ ታምቡር መቀደድ፣ ጋዞችና ሌሎች አደገኛ ቁሳቁሶች መጋለጥ እና እንደ ካርቦንሞኖኦክሳይድ፣ ሃይድሮጅንሲያናይድ፣ ናይትሮጅን ኦክሳይድ እና ሰልፈር ዳይኦክሳይድ ያሉ በመተንፈሻ አካላት ላይ ከባድ ጉዳት በማድረስ ለሞት የሚያበቁ ኬሚካሎች ወይም ለሌሎች ንጥረ-ነገሮች በመጋለጥ በዓይንና በጆሮ ላይ ጉዳት የሚያደርሱና ለአጭርና ረጅም ጊዜ በመቆየት ለጤና መታወክና ለሞት የሚያደርሱ ወይም የአስም፣ የልብ በሽታ፣ የካንሰር ህመም (የብልት ካንሰር፣ የፊኛ ካንሰር፣ የሊንፍ ካንሰርና የአጥንት ካንሰር፣ የሳንባ ካንሰር)፣ የጉበት መብገን (hepatitis) እና በጊዜ ሂደት የሥነ-ልቦና ችግርና የአዕምሮ መረበሽ፣ ጭንቀት፣ ከፍተኛ ሙቀትና ውጥረት እንዲሁም በጭንቀት ብዛት ለሚመጣ ደም ብዛት (stress-Induced hypertension) በከፍተኛ ሁኔታ የተጋለጠ ነው፡፡
- በተጨማሪም ስራው ከፍተኛ ጉልበት፣ ቴክኒክና ሙያ ጥበብን የሚጠይቅና የአካል ጉዳትና ሞት የሚያስከትል ከመሆኑ አንጻር የደመወዝ ክፍያውና ጥቅማጥቅም በሌሎች ሀገሮች አንጻርና በሀገራችን በደህንነታቸው አስጊ ሆነው ከፍተኛ ተከፋይ ተቋማት ጋር የተስተካከለ አለመሆኑ፡፡

- የቅድመ ሆስፒታል ባለሙያዎች ከታካሚው ለሚተላለፉ አደገኛ በሽታዎች ተጋላጭ መሆናቸው ወዘተ ናቸው፡፡

### 3.2.2. ውስጣዊ ችግሮች

የአደረጃጀትና የአሰራር ክፍተት በኮሚሽኑ የሚታዩ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች የተገልጋዩን ፍላጎትና እርካታ በመጨመር ወቅቱ የሚጠይቀው ዋና ዋና የአደረጃጀትና የአሰራር ክፍተቶች በድክመቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

#### ሀ/ ከአደረጃጀት አንጻር

- የአደጋ ስጋት ስራ አመራርን ከአለም አቀፍ የአደራጃጀት ስታንዳርዶች መነሻነት ውጤታማና ተገልጋይን የሚያረካ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል አደረጃጀት አለመኖር፡- ለአብነት ከህዝብ ቁጥር፣ መሰረተ ልማት፣ ቴክኖሎጂና ተደራሽነት አንጻር በንጽጽር በቴክኖሎጂ የታገዘ የአደጋ ማስተባበሪያ ማዕከል /EOC/፣ የትራፊክ፣ የክሬን፣ የስካይ ሊፍት፣ የአምቡላንስ፣ የስካቬተር፣ ጀልባ፣ ሂሊኮፕተር፣ ፓምፕ፣ ኮምፕሬሰር፣ ሀይድሮሊክ ቴስተር፣ የጅምር እሳት ማጥፊ መሳሪያዎች መፈተሻና መጠገኛ ወርክ ሾፕና ላቦራቶሪ፣ ቅ/ጽ/ቤቶች እና ንዑስ ቅ/ጽ/ቤቶች፣ ጄኔሬተርስ፣ ኤልሲዲ፣ ራውተርስ፣ ባካፕስ፣ ማፕንግ ሞኒተርስ፣ ጂፕኤስና ጂአይኤስ፣ ሀይደራንት፣ የአደጋ ማሽነሪዎች መጠገኛ ጋራዥ፣ ለተጎጂዎች ድጋፍ የሚሆኑ ግብዓቶች ማከማቻ፣ ወዘተ…ቁጥር ማነስና አለመኖር በምንሰጣቸው አገልግሎቶች ውጤታማነት እና የአደጋ ክስተት እንዲሁም የማዳን አቅማችን እና መልሶ መቋቋም ላይ ጫና መፍጠሩ፡፡
- የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ተግባራትን ሳይንሳዊና ወቅታዊ በሆነ መልኩ እንዲሁም ሁሉንም የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ዑደቶች የተከተለ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የመዋቅርና አደረጃጀት አለመፈጠሩ፡- ለአብነት የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ዑደት ማለትም የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ምላሽና ኦፕሬሽን፣ በአደጋ ምክንያት ለተጎዱ ዜጎች የሰብአዊ ድጋፎችን በአግባቡና በወቅቱ ለመስጠት የሚያስችል እንዲሁም በዘላቂነት መልሶ የማቋቋም ተግባሮችን ለመፈፀም የሚያስችል የመልሶ ማቋቋምና መገንባት ተቋማዊ አደረጃጃት አለመኖር፡፡
- በአደጋ ለተጎዱ ዜጎች የጊዜያዊ ድጋፍና መልሶ ማቋቋም ተግባርና ሃላፊነት በተለያዩ ተቋማት የሚሰራ በመሆኑ የስራና የተግባር መደራረብ መኖሩ የተነሳ አገልግሎቶቹን

የተበጣጠሰና ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎት መቆየቱ፣ ለአብነት ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ እና ለእሳት አደጋ ተሰጥቶ ስራው ውጤታማ ሳይሆን መቆየቱ፡፡

- አደጋ ሊከስት ይችላል ተብሎ በጥናት በተለየበት አካባቢ ሰብአዊ ድጋፎችን (ምግብ፣ ውሃ፣ ድንኳን፣ አልሚ ምግቦችን ወ.ዘ.ተ. አስቀድሞ ለመያዝ እንዲሁም በአደጋ ወቅት ከሚመለከታችው የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ከማህበረሰቡ ግብአቶችንና ልገሳዎችን ለይቶ መሰብሰብ የሚያስችል አደረጃጀት አለመኖር፣ ለአብነት ከቆሼ፣ ከቡራዩና ከሱማሌ ክልል ለተፈናቀሉና በከተማዋ የሰብዓዊና መልሶ ማቋቋም አገልግሎቶችን የሚፈልጉ ሰዎች ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ድጋፍ ማግኘት አለመቻላቸውና በኮሚቴ እየተመራ መቆየቱ፡፡
- የተቋሙን አገልግሎቶች ለማቀላጠፍ የሚያስችል የጋራዥና ነዳጅ ማደያ  አደረጃጀት አለመኖር፣ ለአብነት የአደጋ ምልሽ መስጫ ማሽኖችን በአስመጭና በሌሎች ጋራዦች ማስጠገኑ የአደጋን አንገብጋቢ ሁኔታ ከግምት ያስገባ ፈጣንና ጥራት ያለው የጥገና አገልግሎት ማግኘት ባለመቻሉ ያሉንን ውስን ማሽነሪዎች በአደጋ ወቅት በውጤታማ በሆነ ሁኔታ መጠቀም አለመቻሉና የምላሽ መስጠትና የማዳን አቅማችን ላይ ክፍተት ፈጥሮብናል፡፡
- በማልጠኛ ማዕከል የወታደራዊና አካል ብቃት እንዲሁም የማሽነሪ ኦፐሬተሮችና አሽከርካሪዎች ዲፓርትመንት አለመኖር፣ ለአብነት የአደጋ ምላሽ የሚሰጡ ባለሙያዎች የሚሰሩት ስራ ከሙያ ባሻገር የአካል ብቃት፣ ጉልበት ወታደራዊ አቋም፣ ቁመና እና ስልት ከሌላቸው የሚፈለገውን ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት ማዳን አይችሉም በመሆኑም በማዕከሉ ይሄንን የሚያሰለጥን አካል ያስፈልጋል፡፡ በሌላም በኩል የአደጋ ማሽነሪዎች ከሌሎች ተሽከርካሪዎች የተለየ በርካታ ተጨማሪ ማሽኖችን፣ ኤሌክትሮኒክ ቴክኖሎጂዎችን፣ ጂኦግራፊካል ኢንፎርሜሽንና ፖዚሽንግ ሲስተሞችን እንዲሁም ማፒንግ ሞኒተሮችን መጠቀምን ስለሚያካትት ለዚህ ብቁ ባለሙያ ለማግኘት በማዕከሉ ይህንን የሚያሰለጥን አካል ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡
- የድንገተኛ አደጋዎች መቆጣጠር አገልግሎት ላይ የዋናተኞች እና የልዩ ማሽን ኦፐሬተሮች መደቦች አለመኖር፣ መገለጫ የድንገተኛ አደጋዎችን በከተማዋም ሆነ እንደ ሀገር አገልግሎት እየሰጠ ያለ ተቋም እንመሆኑ በተቋሙ የዋናተኛ መደብና ደረጃ ባለመኖሩ ባለሙያውን በዚህ መደብ ላይ በዚህ ሂደት አገልግሎት ስጡ ብሎ ማስገደድ ላይ ክፍተት መፍጠሩ፡፡
- የቅድመ ሆስፒታል ህክምናና አንቡላንስ አገልግሎት አሰጣጥን በተሻለ ለመምራት የሚያስችል የስራ አደረጃጀትና መደብ ያለመኖር፣ ለአብነት ለድንገተኛ አደጋዎች የሚሰጡ የቅድመ ሆስፒታል ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት 24 ሰዓት እንደመሆኑ በየቅርንጫፉ

በየሽፍቱ የዚህን አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን የሚመራና የሚያስተባብር ሽፍት ጠርናፊ ባለመኖሩ ስራው ላይ ክፍተት ፈጥሯል፡፡

- የተቋሙን የህግ አገልግሎቶች ለማቀላጠፍ የሚያስችል መደብ አለመኖር፣ ለአብነት በተቋሙ የሚፈጸሙ አገር አቀፍና አለማቀፍ ውሎች፣ የፍትሀ ብሄርና የወንጀል ክሶች ጠበቃ ባለመኖሩ በብዙ ጉዳዮች ላይ ክፍተቶች መፈጠራቸው የሰው ሀይል ፍላጎት እንዳለ ያሳያል፡፡

## ለ/ የአዲስ አበባ ህዝብ ብዛት፣ የቆዳ ስፋት እና የእሳት አደጋ ማቢያ ብዛት አንጻር

አዲስ አበባ ከተማ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የአፍሪካ መዲና፣ የበርካታ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ኤምባሲዎች መቀመጫ ከተማ ነች፡፡

- አዲስ አበባ በ1889 ዓ.ም የተቆረቆረች ስትሆን ከተማዋ በየጊዜው እየሰፋች፤ በኢንቨስትመንትና የተለያዩ ግንባታዎች መስፋፋት፤ የኢንዱስትሪዎች ብዛት ዓይነት በፍጥነት እየጨመረ መጥቷል፡፡
- ከዚህ አንጻር የእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች ሥጋትና ክስተት እየጨመረ የመጣበት ሁኔታ እንዳለ ማየት ተችሏል፡፡
- በከተማዋ እየተከናወኑ የሚገኙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ቀጣይነትና ደህንነታቸው ተጠብቆ ዘላቂነት እንዲኖራቸው ከማድረግ አኳያ፣ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎች ለመቀነስ ሰፊ የቅድመ አደጋ መከላከል ስራዎች ሊሠሩ ይገባል፣ ከዚህ አልፎ አደጋዎች ሲከሰቱ ፈጥኖ በመድረስና መቆጣጠር በንብረትና በህይወት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መቀነስ ሌላው ዋና ተግባር ይሆናል፡፡

## ሐ/ ለአደጋ ምላሽ አሰጣጥ ተግባር ሂደት

አንድ የስልክ ጥሪ ስልክ መቀበል፣ በ5 ሴኮንድ የተዘጋጅ ደውል ማሰማት፣ በ30 ሴኮንድ ዝግጁነቱን ከአረጋገጠበት ቦታ ወደ አደጋ ቦታ በፍጥነት መንቀሳቀስና ከጊቢ መውጣት፣ በዝቅተኛ በመካከለኛና በረጅምር ርቀት ኪ.ሜ. በስታንዳርድ አደጋ ቦታ መድረስ፣ 2 ኪ.ሜ. 3 ደቂቃ፣ 4-6 ኪ.ሜ በ5 ደቂቃ፣ 8-10 ኪ.ሜ 15 ደቂቃ፣ 11-30 ኪ.ሜ 20 ደቂቃ የአደጋ ምላሽ ሰጪ ባለሙያዎች የሚጠቀሙበትን የጉዳት መከላከያ አልባሳት ደረጃው የጠበቀ እንዲሆን አስችሎአል፣ ለአደጋ ምላሽ መስጫ ማሽነሪዎች እና አቡላስ ለተፈለገው አላማ እንዲውል አስችሏል፡፡

በተለያዩ ድንገተኛ አደጋዎች ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የቅድመ ሆስፒታል ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት ለመስጠት በፍጥነት እያደገ የመጣው የከተማዋ የቆዳ ስፋት፣ የህዝብ ቁጥርና ልማት እድገት ሲነጻጸር እነዚህን አገልግሎቶችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ እንቅፋት ሆነው የቆዩ በርካታ ምክንያቶች ይኖራሉ፡፡

- የቅርንጫፎች ቁጥር በተፈለገው መጠን ያለመስፋፋት፣
- በሰለጠነ የሰው ሀይልና ግብዓት አለመሟላት፣

በመሆኑም የኮሚሽኑን የዝግጁነት ደረጃ ከከተማዋ ፈጣን የዕድገት ጋር አጣጥሞ ለማስኬድ የሚታዩ ችግሮች እንደሚከተለው ተለይተው ቀርበዋል፡፡

- ህዝብ ብዛት 5.06 ሚሊዮን፣ ቆዳ ስፋት 550 ኪ.ሜ ካሬ፣ የህዝብ ጥግግት /population density/ 5560፣ የቅርንጫፎች ብዛት 10 ክ/ከተሞች 9፣ የአገልግሎት ሽፋን/በኪ.ሜ ካሬ ከ8.5 እስከ 12.1ኪሎ ሜትር፣ ወይንም 1 ጣቢያ 61.1 ካሬ ኪ/ሜ፣ 1 ጣቢያ ለ562,000 ህዝብ ይሸፍናል መለት ነው፡፡
- የሌሎች አገሮች አሰራርና አደረጃጀት በአብዛኛው 1 ጣቢያ እስከ 4ኪ.ሜ ካሬ፣ ጣቢያ ለ20,000 ነዋሪዎች ህዝብ ይሸፍናል፡፡
    - ይህ የሚያመለክተው የአደጋ ጣቢያዎች በተቀራረበ ሁኔታ ማደራጀት አደጋዎችን አስቀድሞ ከመከላከልና ሲከሰቱም ከመቆጣጠር አንጻር ለህብረተሰቡ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ጥራት ባለው መልኩ ለመስጠት አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡
    - ለዚህም እንደመፍትሔ ተደርጎ የተወሰደው አሰራር የ10 ክ/ከተሞች የአገልግሎት ጥያቄዎች በ9ኙ ቅንጫፎች ሙሉ በሙሉ በመሸፈን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ቀልጣፋና ተደራሽ ማድርግ ሲሆን በአንፃሩ ግን ይህ አሰራር ከፍተኛ ከከተማው ቆዳ ስፋትና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አነስተኛ መሆን ጫና እየፈጠረ መሆኑ እንደችግር መውሰድ ይቻላል፡፡
    - ይህም የከተማችን የእድገት ደረጃ፣ የልማት ፍጥነት፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦት መጠን፣ አይነት፣ ጥራት በየጊዜው በተሻሻለ ደረጃ ላይ ብትገኝም በቅድመ አደጋ ስጋት ቅነሳና ምላሽ ዙሪያ የአደጋ ክስተት ለመቀነስ፣ የጉዳት መጠን ለመቀነስና ፈጣን የህይወት አድን እርዳታ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ለመዘርጋት ወሳኝ ስራ ከመፈጸም ረገድ ከሌሎች መሰል የውጪ ከተሞች ጋር ሲነጻጸር የኮሚሽኑ አደጋ ጣቢያ/የአደጋ መኪና እና ከከተማው የህዝብ ብዛት፣ የልማት ደረጃ ጋር ሲነጻጸር በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

### መ/ የግብዓት ክፍተቶችና በአፈጻጸም የሚታዩ ውስንነቶች

- የቅ/ጽ/ቤት ብዛት 9፣ የአደጋ ተሽከርካሪ ብዛት 58፣ የአንቡላንስ ብዛት 33፣ የሃይድራንት ብዛት 416፣ የመሰላል ተሸካሚ ተሽከርካሪ 3፣ የሪስኪ ተሽከርካሪ 1፣ ኮማንድ ካር 6፣ ብረሽ ትራክ 10፣
- በኛ ከተማ 1 የአደጋ ምላሽ ተሽከርካሪ ለ87,241 ያህል ህዝብ የሚያገለግል ሲሆን የሌሎች ሃገሮች ተሞክሮ 1 የአደጋ ምላሽ ተሽከርካሪ ከ20,000-50,000 ያህል የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ስለሆነም ለ87,241 ያህል የአዲስ አበባ ህዝብ በእኛ ተጨባጭ ሁኔታ አንድ የአደጋ ምላሽ ተሽከርካሪ 50000 ህዝብ ለማገልገል ሲሰላ አጠቃላይ የአደጋ ምላሽ ተሽከርካሪ 101 የሚያስፈልግ ሲሆን አሁን ካለን የአደጋ ምላሽ ተሽከርካሪ በተጨማሪ 27 (101-74) ተሽከርካሪ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡
  - የሃይድራንቶች አንዱ ከአንዱ ያለው ርቀት ከሌሎች አገሮች ስታንዳርድ አንጻር ሲታይ ከ100-200 ሜትር ርቀት መሆን ያለበት ቢሆንም በከተማችን ተጨባጭ ሁኔታ የሃይድራንቶች ርቀት በአማካይ በየ1,032 ሜትር ርቀት ላይ የተተከሉ መሆኑ መረጃችን ያሳያል፡፡ የሌሎች አገሮች ስታንዳርድ መጠበቅ ባይቻልም ቢያንስ በየ500 ሜትር ርቀት ላይ ለመትከል ከ1040 ወይም 584 ተጨማሪ ሃይድራንት በላይ ያስፈልጋሉ፤
  - 33 አምቡላንሶች ያሉ ሲሆን በዚህም መሰረት 1 አንቡላንስ ለ151,515 ነዋሪዎች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ከሌሎች ሃገሮች ጋር ሲነጻጸር ተጨማሪ 32 አንቡላንስ መጨመር እንዳለበት መረጃዎች ያሳያሉ፤ ነገር ግን የሌሎች ሃገሮች ተሞክሮ እንደሚያሳየው አንድ አንቡላንስ ከ20-50 ሽህ ያህል ህዝብ አገልግሎት እንደሚሰጥ ማየት ተችሏል፡፡ በእኛ አቅም ቢያንስ አንድ አምቡላንስ ለ70 ሺ ህዝብ አገልገሎት ቢሰጥ 55 አምቡላንስች የሚያስፈልጉ ሲሆን አሁን ያለው 33 ብቻ በመሆኑ ይህንን ጋፕ ለማስተካከል 22 ተጨማሪ አምቡላንሶች ያስፈልጋሉ ማለት ነው፡፡

### ሠ/ አደጋ ስጋት

- ከተማዋ 9 አይነት የከፍታ ዞኖች ያላት እና ከሰሜን ወደ ደቡብ እስከ 1000 ሜትር የሚደርስ የከፍታ ልዩነት (እንጦጦ 2912-3010 ሜትር፣ አቃቂ 2050-2158 ሜትር) በመኖሩ ለአፈር መናድ፣ ለጎርፍ መጥለቅለቅ፣ ለድንጋይ ናዳ ተጋለጭ የደርጋታል፣
- ከተማዋ 11 በመቶው ጠፍጣፋ፣ ከ2 እስከ 35 በመቶ ቁልቁለታማ፣ ከ2-15 በመቶ ተዳፋታማ መሆኑ ለጎርፍ፣ ለናዳ፣ ለአፈር መሸርሸር፣ የተቀረው ከፍታማ በመሆኑ ለግንባታ፣ ለመንገድ ልማትና ለቤቶች ልማት ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ያለው በመሆኑ ለአደጋ ስጋት ይሆናል፣ የከተማዋ የአፈር ሁኔታ እንደ የቦታው የተለያየ በመሆኑ ወጥነት

ያለው የህንጻ ስታንዳርድና ከፍታ እንዳይፈጠር በማድረጉ እና ግንባታዎችን የመሸከም አቅም አናሳ በመሆኑ ለአደጋ ስጋት ይሆናል፣

- በከተማዋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ የመሰረተ ልማት ግንባታ (ከፍተኛ ድልድዮች፣ የባቡር ሃዲዶች፣ በኤሌክትሪክ ሃይል መስመሮች፣ ከፍተኛ የፍሳሽ ማስተላለፊያ ቦይ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ የመሰረተ ልማት የቅንጅት ችግር በመኖሩ የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋ፣ የኤሌክትሪክ ፖል መውደቅና የኤሌትሪክ ቃጠሎና የመሰረተ ልማት ቦታዎች መደርመስ አደጋዎች ስጋት መኖር፣
- በከተማዋ የአውቶብስ ተርሚናሎች መሃል ከተማ ውስጥ በብዛት እየተሰሩ መሄድ እና ከዛው እኩል አብሮ እየተሰራ ያለ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ወይም ቅድመ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ስራዎች ትኩረት አለመስጠት የከተማዋን የአደጋ ተጋላጭነት ደረጃ የሚያሳዩ መሆኑ፣
- በህዝብ ትራንስፖርት የመጠቀም ልምድ በከተማዋ እየጨመረ መምጣት በትራፊክ አደጋ ክስተት ወቅት ብዙ ሰው ለአደጋ አጋላጭ መሆኑ፣
- ለልማቶች የሚጠቅሙ የሃይል ምንጮች ዘወትር እየተፈተሹና ቀጣይነት ባለው የደህንነት መረጃ ክትትል ካልተደረገ ለአደጋ ተጋላጭ ያደርጋሉ፣
- የአድራሻ ስርዓት /የህዝብ መረጃ/ (ውልደት፣ ሞትና ስደት ምጣኔ) በሁሉም አካባቢ ወጥ ሆኖ አለመተግበሩ አደጋን ከመከላከል እና ከመቆጣጠር አንጻር ጫና መፍጠሩ፣
- የከተማዋ ግማሽ ክፍል የተጎሳቀለና የውስጥ ለውስጥ መተላለፊያ መንገድ የሌለው በመሆኑ ለአደጋ ተጋላጭ ይሆናል፣
- የከተማዋ የህዝብ ጥግግት መጠን በአማካይ እስከ 6000 ሰው በኪ.ሜትር ስኩዌር ሲሆን ከዚህም ደግሞ በተለይ ማዕከል ባሉ ክፍለ ከተሞች ማለትም (አራዳ፣ ቂርቆስ፣ ልደታ እና አዲስ ከተማ) የበለጠ የህዝብ ጥግግት መጠን መኖር፣ ለሰው ሰራሽና ለተፈጥሮ አደጋ ተጋላጭ መሆኑ፣
- በከተማዋ የመኖሪያ ሰፈሮች የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማቶች አየር ላይ በብዛት የተሰቀሉ መሆን ለእሳት አደጋ መንስኤ መሆናቸው፣
- የፍሳሽና የጎርፍ መስመር በውል አለመለየት ለጎርፍ አደጋ፣ ለትራፊክ አደጋ፣ የሰው ሰራሽ አደጋዎችና ለውሀ ወለድ በሽታ ተጋላጭነት ማድረጉ፣
- የገበያ ማዕከላት መስፋፋት እና የቅዳሜ ገበያዎች በላስቲክና እንጨት እየተሰሩ በስፋት ስራ ላይ መግባት ለተለያዩ አደጋዎች ተጋላጭ ያደረጋቸዋል፣

ኮሚሽኑ ስራዎቹን ለማሳለጥ ይመች ዘንድ የቅድመ ዝግጁነት ሁኔታዎች መሟላት ማለትም የሰው ሃይል አቅምና አደረጃጀት፣ ግብአቶች፣ የቴክኖሎጂ ወዘተ... ማሳለጥ ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም በአሁኑ ወቅት ኮሚሽኑ ያለበት አደረጃጀትና የሰው ሃይል ብዛት ስናይ በ1 ዋና ማዕከል፣ በ4 ዋና ዋና

ዘርፎች፣ 9 ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፣ በ8 ዳይሬክቶሬቶች ዓለማ ፈጻሚና 5 ደሃፊ ዳይሬክቶሬቶች፣ በ1ማሰልጠኛ ተቋምና ንዑሳን ስራ ክፍሎች ተደራጅቶ በስሩ ጥቅል 2,365 ሰራተኞችን በመያዝ እየሰራ ይገኛል፡፡ ስራዎችን ለመፈፀምና ለማስፈፀም የሚያገለግሉ የተለያዩ የአደጋ ምላሽና አደጋ ስጋት ቅነሳ ተሽከርካሪ ማሽነሪዎችና መኪኖች ያሉ ሲሆን በዝርዝር ሲታይ፤ 14 አውቶሞቢል መኪና፣ 33 ፒካፕ መኪና፣ 33 አምቦላንስ፣ 52 ከባድ መኪና፣ 10 አውቶብስ፣ 10 ብረሽ ትራክ እና 6 ኮማንድ ካር ባጠቃላዩ 159 ያክል ይገኛሉ፡፡

ስለዚህ የከተማውን ህብረተሰብ ያለምንም ችግር ለማገልገል ከተፈለገ ያሉን መኪኖች በቂናቸው ብሎ መውሰድ አያስደፍርም፡፡ ስለዚህ ግብአቶችን ለማሟላት ገና ብዙ ጥረትና በጀት እንደሚጠይቅ ያሳያል፡፡ ሌላው የቴክኖሎጂ አደረጃጀትና አጠቃቀም ያለበት ሁኔታ ሲታይ ፕሮጀክቱ ተይዞ ገና በጨረታ ላይ ስለሆነ ስራ ገባን ተብሎ ለማውራት አያስደፍርም ስለሆነም በቀጣይ የአይ ሲ ቲው ስራ ዘርፍና ኮሚሽኑ በመረባረብ የተጀመረውን የአይሲቲ ስራ የጨረታ ፕሮጀክት ዳር ለማድረስ ርብርብ ያስፈልጋል፡፡

## ረ/ የአደጋ ምላሽ አሰጣጥ ስታንዳርድ አፈጻጸም ውስንነት መሻሻል ማስፈለጉ

ከህብረተሰቡ በየወቅቱ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለማሻሻልና በቂ ምላሽ ለመስጠት አገልግሎት አሰጣጣችንን በስታንዳርዱ መሰረት መከናወን ተገቢ ይሆናል፡፡ አገልግሎት አሰጣጣችንን ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ከማድረግ አኳያ መሻሻሎች ያሉ ቢሆንም አሁንም ሕዝቡ በተደጋጋሚ የሚያነሳቸው ቅሬታዎች ቀላል አለመሆናቸውን በመውሰድ ለቀጣይ ለመሻሻል ግብዓት ይሆናል፡፡ የሚነሱ ቅሬታዎችም በዋናነት የ939 ስልክ በሚፈለገው ፍጥነት ቶሎ አይነሳም፣ አደጋ ስፍራ ቶሎ አትደርሱም፣ ከደረሳችሁ በኋላም በፍጥነት ሥራ አትጀምሩም፣ የሚለው የሕዝብ ቅሬታ አሁንም ሙሉ በሙሉ አለመቀረፉ ተስተውሏል፡፡ የ2011 ዕቅድ አፈጻጸሙም በስታንዳርድ መድረስ 79% መሆኑን ያሣያል፡፡

ሕብረተሰቡ በራሱ ተቋሙ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ አለማወቁ ሌላው የሚታይ ክፍተት ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተቀመጡት መልካም አፈፃፀሞችና ውጤታማ የሆኑ ጥረቶች ቢታዩም አሁንም መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች እንዳሉ ተቋሙ ተመልክቷል፡፡ የቅሬታ ምንጮችን በደንብ በመፈተሽና በመለየት አፋጣኝ ምላሽ መስጠት የተጠናከረ የሕዝብ ንቅናቄ በመፍጠር የህዝብ ክንፉን ተሳትፎ ማስፋትና ማጠናከር ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ትስስር በተሻለ ደረጃ ላይ ማድረስ ሕብረተሰቡ ተቋሙ ስለሚሰጠው አገልግሎት ሙሉ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ የሕዝብ ግንኙነት ሥራውን አጠናክሮ ማስቀጠል ሕብረተሰቡ የሥራው ባለቤት የሚሆንበት አሰራር አጠናክሮ መከወን ውሣኝ ይሆናል፡፡

## ሰ/ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ አቅርቦትና መልሶ ማቋቋም ፍልጎት ከፍተኛ መሆንና የመፈጸም አቅም ውስንነት መኖሩ

በሰኔ 16/2010 ዓ.ም በቦምብ አደጋ ላይ ለተጎዱ ዜጎች እርዳታ ለ126 ሰዎች 14,690,000 (አስራ አንድ ሚሊያን አምስት መቶ ሀያ ሺህ) የጉዳት ክፍያ ተፈጽሟል፡፡ ከቡራዩ የተፈናቀሉ **15,086** ያህል ዜጎች ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመቀናጀት ለድጋፍና እለት እርዳታ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ማለትም ፍራሽ፣ ብርድልብስ፣ አንሶላ፣ አልሚ ምግቦች፣ የሴቶችና የህፃናት የንፅሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶች፣ ብስኩቶች፣ ሳሙናዎችና ሌሎች የጽዳት እቃዎች እንዲሁም የሰውና የእቃ ማጓጓዣ የትራንስፖርት አቅርቦቶች ግዢ በመፈጸም በአጠቃላይ ከ14 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከፌዴራል ብሄራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የእርዳታ ቁሳቁሶች ማለትም የማረፊያ ሸ.ት፣ የህጻናት አልሚ ምግብና ብስኩቶች እንዲደርሱ በማድረግ ማሰራጨት ተችሏል፡፡ በኦሮሚያና ከኢትዮ-ሶማሌ የተፈናቀሉ ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም በተደረገው ጥረትም አጠቃላይ 5,863 ለሚሆኑት የእለት እርዳታዎች ማለትም ምግብ፣ መጠጥ ፣ የንፅህና የመጠለያ አገልግሎቶችን ሪፍት ቫሊ ዩኒቨርሲቲ በጊዜያዊነት በሰጠው መጠለያ ውስጥ የቀረበላቸው ሲሆን ለ647 አባወራ ለቤት ግንባታ ማስጨረሻና ኪራይ ብር 52,000,000 ብር ገቢ መደረጉ፣

የቆሼ አደጋ 16ቱ ህጋዊ ባለይዞታ ልጆች የመኖሪያ አፓርታማ ግንባታ ዲዛይን ተጠናቆ ወደ ኮንስትራክሽን እንዲገባ በተደረገው ክትትል የመጨረሻውን ዲዛይን ግንባታ እንዲያከናውን ውል ለተሰጠው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን በኮንስትራክሽን ቢሮ በኩል እንዲተላለፍ የተደረገ ሲሆን የግንባታ ዝርዝር ኳንቲቲና ውል ለመፈጸምና ወደ ስራ ለማስገባት በክትትል ላይ ይገኛል፡፡ የመኖሪያ ቤቶቻቸው ግንባታዎቹ እስኪያጠናቅቁ ድረስ ተጨማሪ የአንድ ዓመት ከስድስት ወራት የቤት ኪራይ ለ16ቱ ህጋዊ ባለይዞታዎች እና ለ13ቱ የህጋዊ ባለይዞታ ልጆች ለ1 ዓመት ከግማሽ ዓመት ኪራይ እና የቤት ግንባታ ማስጨረሻ ብር 19,642,000 ተከፍሏል፡፡

ክረምትን ተከትሎ በአቃቂ ቃሊቲ፣ በንፋስ ስልክ፣ በልደታና አራዳ ክፍለ ከተሞች በጎርፍ አደጋ የተጎዱ ከ4,000 በላይ ሰዎች ከቢሮው ጋር በመቀናጀት የእለት የምግብ እርዳታ፣ የብርድልብስ፣ የአንሶላና ፍራሽ አቅርቦቶች በተቀመጠው የግብዓት ስርጭት መጠን ስታንዳርድ መሰረት ተሰራጭቷል፡፡ ይሁን እንጂ ከከተማዋ ለአደጋ ተጋላጭነት ደረጃ አንጻር ሲታይ ሊፈናቀሉ የሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ለእነዚህ ህብረተሰብ ክፍሎች ሊሆን የሚችል አስፈላጊውን ግብዓቶችን ዝግጁ ማድረግ ስለሚያስፈልግ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ግን ሰፊ ውስንነቶችን መቅረፍ ይጠበቃል፡፡

## ሸ/ የቅድመ አደጋ ስጋት ቅነሳ ሥራዎች ያለበት ሁኔታ

ተቋሙ የቅድመ አደጋ መከላከል ተግባርን ቅድሚያ በመስጠት የአደጋ ክስተትን ለመቀነስ በበጀት ዘመኑ በስፋት ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ ተቋሙ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኝና ለከተማው ሕብረተሰብ ብቻ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ ቢሆንም ከሌሎች ተቋማት ጋር በመሆን በሀገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች በመገኘት ለአደጋ መከላከል ስራዎች ድጋፍ በመስጠትም የበኩሉን ድርሻ ተወጥቷል፡፡ በአጠቃላይ በተቋሙ በተያዘው የቅድመ አደጋ መከላከል ዕቅዶችና ግቦች አንፃር በበጀት ዘመኑ ውጤታማ የሆነ አገልግሎት በመስጠት ተግባሩን ሲያከናወን ቆይቷል፡፡ የሴፍቲ መሣሪያዎች መሟላትና አለመሟላታቸው የኢንስፔክሽን ስራ በመሥራት የተቋሙ የቅድመ አደጋ መከላከል ባለሙያዎች የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ችለዋል፡፡ በዚህም መሰረት የአደጋ መከላከል ለተለያዩ ተቋማት አቅምን ከመገንባት አንጻር፡-

ለተቋማት የሙያ ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ እንዲሁም ፍተሻ ለ4859 ተቋማት አገልግሎቱን ለመስጠት ታቅዶ ለ3407 ተቋማት ተሰጥቷል፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 70% መሆኑ ያሣያል፡፡

- በበጀት ዘመኑ ፍተሻ በማድረግ ለ310 ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት ታቅዶ ለ18 ተቋማት ብቃታቸው በመረጋገጡ የብቃት ምስክር ወረቀቱን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ይህም የዕቅዱ 6% መከናወኑን እና የፋየር ኮድ ወይንም አስገዳጅ ህግ አለመኖር ዋናኛ መነቆ መሆኑንም ያሣያል፡፡

## ቀ/ የአደጋ ስጋት ቅነሳ አገልግሎቶች አፈጻጸምና ውስንነቶቹ

ከተቋማት አንጻር በከተማው ካሉት ትላልቅ ተቋማት ማለትም፡-

- ከተለዩት 559 ሆቴሎች ውስጥ የተፈተሸ 502 የደህንነት ብቃት ያረጋገጠ 95 ብቻ
- ከተለዩት 904 ኢንዱስትሪዎችና ፋብሪካዎች ውስጥ የተፈተሸ 519 የደህንነት ብቃት ያረጋገጠ 4 ብቻ
- ከተለዩት 94 የነዳጅ ማደያዎችና ዲፖዎች ውስጥ የተፈተሸ 93 የደህንት ብቃት ያረጋገጠ 12 ብቻ
- ከተለዩት 527 ጋራዦች ውስጥ የተፈተሸ 249 የደህንት ብቃት ያረጋገጠ 8 ብቻ
- ከተለዩት15 ጤና ተቋማት ውስጥ የተፈተሸ የለም የደህንንት ብቃት ያረጋገጠ የለም፣
- ከተለዩት 5 ከፍተኛ ት/ተቋማት ውስጥ የጠፈተሸ የለም የደህንነት  ብቃት ያገኘ የለም፣
- ከተለዩት 7 ቲያትር ቤቶች ውስጥ  የተፈተሸ 7 የደህንት ብቃት ያረጋገጠ የለም፣
- ከተለዩት 144 የገበያ ማዕከላት ውስጥ የተፈተሸ 144 የደህንነት ብቃት ያረጋገጠ 3 ብቻ

- ከተለዩት 935 መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ውስጥ የተፈተሸ 401 የድህንነት ብቃት ያረጋገጠ 11 ብቻ
- በግንባታ ላይ ካሉት ከ139 ትላልቅ ህንፃዎች ውስጥ 139 መፈተሹ ብቃት ያረጋገጠ የለም፣
- ከተለዩት 141 ሌሎች ተቋማት ውስጥ 141 መፈተሽና የድህንት ብቃት ያረጋገጡት 2 ብቻ መሆኑ
- በአጠቃላይ ከ3469 ውስጥ የተፈተሸ 2160 ብቃት ማረጋገጫ ያገኙ 105 ሲሁኑ ስለ ጉዳዩ አሳሳቢነት በማሳመን በተቻለ መጠን ተደራሽ መሆን መቻልና አልፎ አልፎ ፍቃደኛ ላይሆኑት የተለያዩ ህጎችን በማጠቀስ የማስገንዘብ ስራ መስራት እንደተጠበቀ ሆኖ ከመከሰቱ በፊት አስቀድሞ የአደጋ ደህንነት መስፈርቶችን አሟልተውና የጥንቃቄ ህጎችን ጠብቀው እንዲሠሩ ለማስገደድና ካላከበሩብም በህግ ለመጠየቅ የአደጋ ደህንነት አስገዳጅ ህግ (Fire Safety Code) ጸድቆ ተግባራዊ እንዲሆን ለማድርግ መጣር ነው፣
- የተወሰኑ ተቋማት የአደጋ ደህንነት ብቃት መስፈርቶችን በከፊል አሟልተው ብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው የመፈልግ ሁኔታ መኖርና የአመራርና ሰራተኛ ቁርጠኝነትና ተጠያቂነት መጠናከር እንዳለበት፣

## በ/ የአዲስ አበባ ከተማ የጎርፍ አደጋ ተጋላጭነት ስጋቶችና ችግሮች

የአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ስፋት ባላቸው የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በተደጋጋሚ የምትጠቃ ሲሆን ከዚህም ውስጥ አንዱና ዋነኛው የጎርፍ አደጋ ተጋላጭነትና ክስተት ስጋት ነው፡፡ በዚህ የአደጋ ክስተት ምክንያትም በህይወትና በንብረት ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት አሳሳቢ እንደሆነ በየጊዜው በሚካሄዱ የአደጋ ተጋላጭነት ጥናቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም ጥናቶቹ የሚያሳዩት በከተማችን በርካታ የተለያዩ ቦታዎች ለጎርፍና ከጎርፍ ጋር ተያያዥነት ባላቸው አደጋዎች በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ በመሆናቸው ነው፡፡ ለምሳሌ በቅርብ ጊዜ የተካሄዱ ጥናቶች መረጃ የሚያሳየው

- 47 ቦታዎች በወንዞች ተፋሰስ ምክንያት፣ 10 ቦታዎች በመልካአ ምድራዊ አቀማመጥ (በመሬት ተዳፋነት) ምክንያት፣ 23 ቦታዎች በጎርፍ ምክንያት ለአፈርና መሬት መንሸራተትና መደርመስ፣ 66 መስመሮች በጎርፍ መውረጃ ቦዮች፣ ቱቦዎችና ዲቾች አለመኖር፣ ጥበትና በቆሻሻ መደፈን፣ ወዘተ፣ ምክንያት ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ መሆናቸው ታውቋል፡፡ እነዚህ ቦታዎች ለጎርፍና ተያያዥነት አደጋዎች ተጋላጭ የሆኑበት መንስኤዎችና ምክንያቶች፡-
    - የህብረተሰቡ አኗኗር፣ አሠፋፈር፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሁኔታ፣ የከተማችን ጂኦግራፊካል አቀማመጥ ወጣ ገባ መሆን፣ በወንዝ ዳርጃዎች በርካታ ቤቶችና ተቋማት መገንባት፣

በወንዝ ዳርጃዎች በርካታ ሰዎች በጊዜያዊነትና በቋሚነት ሰፍረው መኖር፣ በከባድ ዝናብ ምክንያት የወንዞች መሙላት፣ የጎርፍ ማስወገጃ ቦዮች፣ መስመሮችና ዲቶች አለመኖር፣ የጎርፍ መከላከከያዎች አለመሠራት፣ የተሠሩትም በመደፈናቸ፣ ወዘተ ናቸው፡፡ በእነዚህ የአደጋ ተጋላጭ ቦታዎች 20,955 የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ወደ 1000 የሚጠጉ የተለያዩ ተቋማት፣ ወደ 4.32 ቢልዮን የሚገመት ንብረት ላይ ጉዳት እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ በአጠቃላይ በእነዚህ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎች አደጋዎች ቢከሰቱ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችና አሉታዊ ተጽዕኖዎች ፡-

- በበርካታ የአካባቢው ነዋሪ ህብረተሰብ ላይ ከፍተኛ የህይወት መጥፋትና የአካል ጉዳት የንብረት ውድመት ሊደርስ ይችላል፣
- የአካባቢው ነዋሪ ህብረተሰብ ከቄው ሊፈናቀል ይችላል፣
- በነዋሪው ህዝብ ላይ የስነልቦናና የኢኮኖሚ ቀውስ ሊከሰት ይችላል፣
- በከተማው የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል ይችላል

## ተ/ ችግሮችን ለመፍታት ኮሚሽን መ/ቤቱ እያደረገ ያለው ጥረት

- ለጎርፍ አደጋ ክስተት መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ የሚገመቱ ቦታዎችን በጥናት እየለየ ይገኛል፣
- በጎርፍ አደጋ ተጋላጭ ቦታች ላይ ህብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲያገኝና ጥንቃቄ እንዲያደርግ በየጊዜው ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎችን እና የቅድመ መስጠንቀቅ ስራ እየሰራ ይገኛል፣
- ከሁሉም ከሚመለከታቸው ባለደርሻ አካላት ጋር በየጊዜው የጋራ ምክክሮችን በማካሄድና መግባባት መፍጠርና በተናጠልና በጋራ ሚናዎችን እንዲወጡ ማድረግ፣
- በጥናት ውጤቱ መሠረት የሚመለከታቸው አካላት የቦታዎችን የአደጋ ተጋላጭነትና ስጋት ተረድተው በወቅቱ አስፈላጊውን የመፍትሔ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ የማሳወቅና የመከታተል፣ የአደጋ ስጋት እና ተጋላጭ ጥነቶችን በማሰጥናት በሞዴል በፕሮጀክቶች ችግሮች እንዲፈቱ ጅምር ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡

## ከተለያዩ የባለድርሻ እና አጋር አካላት ጋር በቅንጅት መወሰድ ያለባቸው የመፍትሔ እርምጃዎች ማለትም፡-

- በቦታዎቹ የጎረፍ፣ የመሬት መንሸራተትና መደርመስ አደጋ እንዳይከሰት በወንዞችና በወንዝ ዳርቻዎች የተለያዩ የመከላከያ ሥራዎችን መስራት፣
- የፍሳሽና የጎርፍ መውረጃ ቦዮች፣ መስመሮችና ቱቦዎች በየጊዜው ማጽዳት፣
- በተለያዩ ቆሻሻና ሌሎች ነገሮች የተዘጉ የውሃና የጎርፍ መውረጃ ጉድጓዶች፣ ቦዮችና ቱቦዎች እንዲከፈቱ ማድረግ፣
- የጎርፍ መውረጃ ቦዮችና ቱቦዎች የሌላቸው ቦታዎች እንዲሠራላቸው ማደረግ፣

- ከዚህም ባለፈ ከሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው ህብረተሰቡ ከቦታዎቹ የሚነሱበት ሁኔታ ላይ አስቸኳይ መፍትሔ መወሰድ፣
- የአደጋ ስራ የባለዘርፍ ብዙና ተሻጋሪ እንዲሁም የተለያዩ ተቋማት ቅንጅታዊ ስራ የሚጠይቅ ሆኖ የሰው ህይወትና ንብረት የማዳን ሰብዓዊ ስራ ነው፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ በዋናነት ክፍለ ከተሞች፣ ወረዳዎች፣ መንገዶች፣ መሬት፣ ኮንስትራክሽን፣ ውሃና ፍሳሽ፣ ፖሊስ፣ ጽዳት አስተዳደር፣ አካባቢ ጥበቃና ወንዞች ዳርቻ የየበኩላቸውን እንዲወጡ አጋጣሚ በማሳወቅ አቅጣጫ እንዲሰጣቸው የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡ እነዚህም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ10ሩም ክፍለ ከተሞች የሚገኙ 25 ለጎርፍ አደጋ ለከፍተኛ ደረጃ የተጋለጡ ቦታዎች ማለትም፡-
- አቃቂ ወረዳ 3 እና 8፣ የካ ወረዳ 9,7,12,5,11 እና 2፣ ቦሌ ወረዳ 13,1,9,6፣ ቂርቆስ ወረዳ 8,5፣ ን/ስልክ ወረዳ 7፣ ኮልፌ ወረዳ 11፣ ልደታ ወረዳ 3,5፣ አ/ከተማ ወረዳ 4,6፣ ጉለሌ ወረዳ 6,1,2፣ አራዳ ወረዳ 7, 10 እና 9 መሆናቸውን ከ2004 እስከ መጋቢት 2011 ዓ/ም ድረስ ባደረግናቸው የአደጋ ተጋላጭ ዳሰሳ ጥናቶች ለማየት ተችሏል፡፡

**እነዚህም፡-**

1. የወንዙን፣ ጥልቀትና ስፋት በመጨመር መያዝ የሚችለውን የውሃ መጠን እንዲይዝ ማድረግና አቅጣጫ ማስቀየር፣
2. የወንዙን ውሃ ፍሰት የሚገቱ ነገሮችን ማስወገድ ማለትም የአቃቂ ወንዝ ከተለያዩ አካባቢዎች በሚመጣ ደለልና ደረቅ ቆሻሻዎች በመሞላቱ ወንዙ መያዝ የሚችለውን የውሀ መጠን መያዝ የማይችል በመሆኑ ጎርፉ ከወንዙ ማፋሰሻ በመውጣት ወደ መንደርና ፋብሪካው እየገባ ስለሆነ በወንዙ ማፋሰሻ ውስጥ ያለውን ደለልና ደረቅ ቆሻሻ መጥረግና የወንዙ ጥልቀትና ስፋት ወደነበረበት እንዲመለስ በማድረግ ወንዙ መያዝ የሚችለውን የውሀ መጠን እንዲይዝ ቢደረግ፣
3. የወንዙን ዳርቻ በአፈርና ጠጠር ማስደገፍና ውሃ እንዳይወጣ ማድረግ፣
4. በወንዝ ዳርቻ የሰፈሩትን ነዋሪዎችና ተቋማት በፊር ዞን ጠብቀው እንዲሰፈሩ ማድረግ፣
5. የወንዝ ማፋሰሻውን ተከትሎ የውሀውን መጠን ታሳቢ ያደረገ የውሃ መመከቻ የድጋፍ ግንብ መገንባት፣
6. በመንገድ ልማት ምክንያት እየተነሳ የሚከመር አፈር የወንዙን የውሀ ፍሰት እንዳያስተጓጎልና የጎርፍ ውሀ ወደ መኖሪያ ቤቶች እንዳይገባ ማድረግ፣
7. የለገዳዲ ግድብ የሚለቀቅን የውኃ መጠን ከወንዙ የውሀ መጠን መጨመር ጋር በማገናዘብ ሃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ተመጥኖ ቢለቀቅ፣

8. የአቃቂ ወንዝ ዳር የሚኖሩ ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ ነዋሪዎችንና ተቋማትን በማማከር በዘላቂነት ከቦታው የሚነሱበትን ሁኔታ ቢመቻች፣
9. በዘላቂነት የወንዙን ዳርቻ በፕላን ማልማት ናቸው፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው ሁሉ የበኩሉን ያላሰለሰ ጥረት እንዲያደርግ እናሳውቃለን፡፡

**አጠቃላይ የተቋማት የአደጋ ደህንነት ብቃት ማረጋገጫ ሁኔታ ትንተና** በአጠቃላይ 3444 ትላልቅና መካከለኛ ተቋማትን መለየት የተቻለ ሲሆን እነዚህም፡- 559 ሆቴሎች፣ 144 ሞሎችና ገቢያ ማዕከላት፣ 94 ነዳጅ ማዲያና ዲፖዎች፣ 526 ጋራገሮች፣ 904 ኢንዲስትሪና ፋብሪካዎች፣ 139 በግንባታ ላይ ያሉ ህንጻዎች፣ 935 መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ሀይማኖታዊና ሌሎች ተቋማት፣ 141 ሌሎች የንግድ ተቋማት ናቸው፡፡ ከዚህ ውስጥ ለ2153 ተቋማት የሙያ ምክርና ቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎትን ከተሰጣቸው በኋላ የአደጋ ደህንነት ፍተሻ በማድረግ ለ92 ሆቴሎች፣ 3 ሞሎችና ገቢያ ማዕከላት፣ 4 ኢንዱስትሪዎች፣ 1 በግንባታ ላይ ያለ ህንጻ፣ 2 መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ሀይማኖታዊና ሌሎች ተቋማት በአጠቃላይ 102 የሚሆኑት ተቋማት የአደጋ ደህንንት ብቃት ማረጋገጫ ማግኘት ችለዋል፡፡

- የብቃት ማረጋገጫ ጋገኙት ተቋማት ውስጥ ትልቁን ቁጥር የያዘው ደግሞ የሆቴሎች ሲሆን ይህም በአብዛኛው ከሆቴሎች የደረጃ ምደባ ጋር ተያይዞ የተሰራ ነው፡፡
- ከአደጋ ስጋታቸው አንጻር ከተለዩት 3444 ትላልቅ ተቋማት ውስጥ የአደጋ ደህንነት ብቃት ፍተሻ የተደረገላቸው 2153 ወይም 62.5% ብቻ መሆናቸው የተደራሽነትና የተቋማት ፍላጎት ውስንነት እንዳለበት ያሳያል፣

ከአደጋ ስጋታቸው አንጻር ከተለዩትና ከተመዘገቡት 3444 ተቋማት ውስጥ ኢንዱስትሪና ፍብሪካዎች፣ ሆቴሎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ሀይማኖታዊና ሌሎች ተቋማት ፣ጋራገሮች እንደ ቅደም ተከተላቸው በስርጭት ከፍተኛውን ቁጥር የያዙ በመሆናቸውን ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባው ያሳያል፡፡ ተቋማቱ የደህንነት መስፈርቶችን ከማሟላት አንጻር ያሉበት ሁኔታ ፍተሻ ከተደረገላቻ 2153 ተቋማት ውስጥ ለ92 ሆቴሎች፣ 3 ሞሎችና ገቢያ ማዕከላት፣ 4 ኢንዱስትሪዎች፣ 1 በግንባታ ላይ ያለ ህንጻ፣ 2 መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ሀይማኖታዊና ሌሎች ተቋማት በአጠቃላይ 102/4..7% የሚሆኑት ተቋማት ብቻ የአደጋ ደህንንት ብቃት ማረጋገጫ መሰጠቱ አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

## ቸ/ የድንገተኛ አደጋዎች ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት

የተቋሙ ተልዕኮ ከሆነው አንዱ የድንገተኛ አደጋዎች ህክምናና አምቡላንስ አገልግሎት መስጠት ሲሆን ተቋሙ ለሕብረተሰቡ የሚሰጠውን አገልግሎት ከዓመት ዓመት እያሳደገ የመጣ ሲሆን ሕብረተሰቡም ተቋሙ የሚሰጠውን አገልግሎት እየተረዳ በመምጣቱ ተጠቃሚነቱ እያደገ

መጥቷል፡፡ በየበጀት ዘመኑም የአገልግሎት መጠኑን እቅድ በመንደፍ ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በዚህም መሰረት በ2011 ዓ.ም ቁጥራቸው 43,050 ለሚሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎቱን ለመስጠት ታቅዶ ለ25,043 /58.2%/ የሕብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎቱን መስጠት ተችሏል፡፡ አጠቃላይ ከቀረቡት 25,365 ጥሪዎች ውስጥ 25፣043 98.7 % ወይም 322 አገልግሎት 42 ድንገተኛ ጢሪ ባለመሆን፣ 236 አማራጭ በመጠቀም፣ 22 በጤና ጣቢያ በመውለድ፣ 22 አገልግሎት ባለመስጠት እንዲሁም በስታንዳርድ አገልግሎት መስጠት 79 % መሆኑ በቀጣይ 2012 ዓ.ም በጀት አመት የአገልግሎቱን አድማስ በማስፋት ከፍተኛ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ አስፈላጊው ሁሉ የሚከናወን ይሆናል፡፡ በ2011 በጀት አመት አጠቃላይ 527 አደጋዎች የተከሰቱ ሲሆን ከተከሰቱት አደጋዎች ውስጥ 365 የእሳት አደጋዎች ሲሆኑ 162 ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች ናቸው፡፡

### 3.2.3. ያጋጠሙ ችግሮች የተፈቱበት አግባብ

ከላይ እንደተመለከተው በከተማችን የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ስራዎችን ለማከናን የሚያስችል ሁሉንም የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኡደት አቀናጅቶ የሚፈጽምና የሚያስፈጽም ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የሚከተሉት ዝርዝር የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማስቀመጥ ተችሏል፡፡

- በተጨማሪም በከተማ ደረጃ የአደጋ ስጋት ተግባሮችን ለማስፈጸም የሚያግዙ ከተማ አቀፍ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ ማኑዋል፣ መመሪያ ማዘጋጀት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የቅድመ አደጋ፣ በአደጋ ወቅት እና በድህረ አደጋ ወቅት መፈፀም የሚገባቸውን ተግባሮች አቀናጅቶ የሚመራ፣ የሚከታተል የአደጋ ስራ አመራር ካውንስል ወይም ምክር ቤት ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡
- ሁሉንም የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ሳይንሳዊ ዑደቱን (የቅድመ አደጋ መከላከል፣ የአደጋ ዝግጁነትና ምላሽ፣ የአደጋ ጊዜያዊ ድጋፍ፣ የአደጋ ማቋቋም እና መልሶ መገንባት) ጠብቆ ሊያሰራ የሚችል የማዋቅራዊ አደረጃጃት መቅረጽ፣
- የአደጋ ስጋት ቅነሳውን ለማካተት የሚያስችል በጥናት ላይ የተመሰረተ ምቹ አደረጃጃት መፍጠር፣
- ከተማ አቀፍ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ቅንጅታዊ አደረጃጀት ሊፈጥር የሚችል ማዋቅር ማዘጋጀት፣
- የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ሳይንሳዊ ዑደትን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል አስገዳጅ ህግ፣ ፖሊስና ስትራቴጂ ማዕቀፍ አዘጋጅቶ መተግበር፣
- የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ምክር ቤት በማቋቋም የሚተገብራቸውን ዝርዝር ተግባራት በማዘጋጀት ወደ ስራ ማስገባት፣

- የሚሰሩ የልማት እና የአገልግሎት ስራዎች ከአደጋ ስጋት ስራ አመራር አንጻር የተቃኘ የአደጋ ማካተት አሰራር ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፣
- የአደጋ ስጋት ስራ አመራር አገልግሎቶችን በማስገንዘብ ላይ የተመሰረተ እና ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መልኩ የአደጋ ደህንነት አስገዳጅ ህግ /ኮድ/ እና የማካተት ፖሊስ መተግበር፣
- የአለማቀፍ ስታንዳርዶችና የከተማዋን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የሚያችል ቅርንጫና ንዑስ ቅርንጫፎችን ማደራጀት፣
- የአደጋ ስጋት ስራ አመራር አገልግሎቶችን በቅንጅታዊ አሰራር ለማሳለጥ የሚያችል አሰራር በማፍጠር መተግበር፣
- የከተማዋን ነባራዊ ሁኔታ እና ወቅቱ የሚጠይቀውን ግብዓት በማሟላት የአደጋ ዝግጁነትና ምላሽ መስጫ ማሽነሪዎች፣ መጋዘኖች፣ ጋራዥና ነዳጅ ማደያ እንዲሁም ዘመኑ የደረሰበትን የአደጋ የሚመራ መረጃ ማዕከል ማደራጀት እና መጠቀም፣
- የአደጋ አገልግሎቶች በስታንዳርድ ለመስጠት የሚያስችል የመሰረተ ልማት ሁኔታዎች እንዲሟሉ ጥረት ይደረጋል፣
- የአመራሩ የመምራት፣ የሙያዊ እና የቴክኒዊ ድጋፍ ስልትና አቅምን በማጎልበት ውጤታማ የአደጋ ስጋት አመራር አገልግሎት ይሰጣል፣
- የአደጋ ስጋ ስራ አመራ ዑደትን በመጠበቅ ስራው የሚፈለገውን የሰው ሀይል ብዛት፣ የሙያ ስብጥር፣ የስራ ልምድ፣ የትምህርት ዝግጅት፣ ደመወዝና ጥቅማጥቅም እንዲሟላ በማድረግ ግልፅነትና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣
- የአማራሩንና የሰራተኛው አገልጋይነት ስሜት በማጎልበት የተገልጋዩ ፍላጎት ተሟልቶ እርካታ እንዲጨምር መስራት፣
- የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር የአደጋ ስጋት ስራ አመራርን በቅርብ ርቀት መፈጸም፣

## 3.3. የተገኙ ውጤቶች /ተሞክሮዎች/

- የአደጋ ስጋት ደረጃ ቦታዎችና ተቋማትን የአደጋ ፕሮፋይል ተለይተው መረጃ ለማደራጀት ተሞክሯል፣ ጥናቶች ተጠንተዋል፣ የማጠንቀቅ ስራ ተሰርተዋል፣
- የሀይድራንት መትከያ ቦታዎች መለየትና መትከል መጠገንን መከታታል ስራዎች ተሰርተዋል፣
- ተቋማትን በዓይነታቸውና ብዛታቸው መለየት ተሞክሯል፣
- የተለዩ ተቋማትን በአደጋ ስጋታቸው አንጻር የሙያ ምክርና ድጋፍ አገልግሎት፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ተሰጥቷል፣

- በአደጋ ተጋላጭ ተቋማት ላይ የአደጋ ስጋት የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ ግንዛቤ የማስጨበጥና ክትትል የማድረግ ስራዎች ተሰርተዋል፣
- ተቋማትን በመፈተሽ የአደጋ ደህንነት መስፈርት ያሟሉ ተቋማትን ብቃት ማረጋገጫ መስጠትና የመደገፍ ስራዎች ወዘተ ተሰርዋል፡፡
- ከተለያዩ ባለድርሻ አካት ጋር ለምሳሌ ንግድና ኢንደስትሪ፣ ባህልና ቱሪዝም…ወዘተ ጋር በመቀናጀት ተቋማት የደህንነት መስፈርትን እንዲያሟሉ በጋራ ጥረት ተደርጓል፣
- የተቋማትና ተገልጋዮቻቸው የአደጋ ደህንነት ስጋት ቅነሳ ዙሪያ ግንዛቤ መጨመሩ፣
- የተወሰኑ ተቋማት የአደጋ ደህንነት መስፍርቶች ለማሟላት ጥረት ማድረግ መጀመራቸው፣
- የተወሰኑ ተቋማት የአደጋ ደህንንት ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ፍላጎት ማሳየት መጀመራቸው፣
- የተቋማት የአደጋ ደህንንት ስታንዳርድ በማሟላታቸው የተቋማቸውን፣ የተጠቃሚያቸውን እና የከተማዋን ህዝብ ከአደጋ ስጋት መጠበቃቸውን ግንዛቤ መያዝ መጀመራቸው፣
- የአደጋ ደህንንት ብቃት ያረጋገጡ ተቋማት የአደጋ ስጋታቸውን መቀነሳቸው እና በራስ መተማመንናቸው መጨመሩ፣
- ተቋማት የአደጋ ስጋት ቅነሳ ስልጠናዎችን ለማግኘት ፍልጎት ማሳየት መጀመራቸው፣
- የተቋማት የአደጋ ደህንነት ሲረጋገጥ የሚሰጡት አገልግሎቶች ውጤታማነት እያደገ መምጣቱ፣
